# ኢየሱስ ላይ ትኩረት ያደረገ የወጣቶች አገልግሎት

ቤሪ ሴንት ክሌር

ኢየሱስ - ሳይ ትኩረት ያደረገ የወጣቶች አገልግሎት

ኮፒ ራይት © 2010 በሪች አውት ሚኒስትሪስ፣ ኢንክ. እና ቤሪ ሴንት ክሌይር

በሪች አውት ዩዝ ሶልዩሽንስ የተዘጋጁ ደብሊው ደብሊው ደብሊው ሪች. አውት. ኦርግ

የደራሲው መብት የተጠበቀ ነው:: ከሪች አውት ሚኒስትሪስ ኢንክ የተጻፈ ፈቃድ ካላገኙ በቀር ይህ ጽሁፍ በማንኛውም መልክ ሊባዛ፣ በተሻሻለ መንገድ ሊቀመጥ ወይም ሊተላለፍ አይችልም::

የመጀመሪያ እትም፣ 2002

የሽፋን ዲዛይንና ግራፊክስ፡ ማይክ ዴቪስ

የህትመት ሥራ፡ ሪቨርስቶን ግሩፕ፣ ኤል ኤል ሲ

አዘጋጅ፡ ባርባራ ኤል. ታውንሴንድ

በተለየ ሁኔታ ካተገለጸ በቀር ሁሉም የቅዱሳት መጽሐፍት ክፍል ከኤን አይቪ. መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው:: ኮፒ ራይት © 1973፣ 1978፣ 1984 በአለም አቀፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ማህበር:: ከዞንደርቫን በፈቃድ ጥቅም ላይ የዋለ:: ሁሉም መብቶች የተጠበቁ ናቸው::

መልእክቱ የሚሉት የቅዱሳት መጽሀፍት ክፍሎች ከ መልእክቱ የተወሰዱ ናቸው::

ኮፒ ራይት © 1993፣ 1994፣ 1995፣ 1996፣ 2000፣ 2001፣ 2002:: ከናቭ ፐብሊሺንግ ግሩፕ በፈቃድ የተወሰደ::

አር. ኤስ፣ ቪ. በመባል ምልክት የተደረገባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ከ አር. ኤስ፣ ቪ. መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው:: ኮፒ ራይት © 1946፣ 1952፣ 1971፣ በዩናይትድ ስቴትስ በክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናት ብሔራዊ ምክር ቤት የክርስቲያን ትምህርት ክፍል::

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| መግቢያ | 6 |
| ክፍል 1፡ ትልቁን ስእል ተመልከት | 11 |
| ክፍል 2 ወደ ክርስቶስ ውስጠኛ ነገር ሂድ | 24 |
| ክፍል 3 በፍላጎት ጸልይ | 38 |
| ክፍል 4 መሪዎችን መገንባት | 52 |
| ክፍል 5 ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር አድርግ | 71 |
| ክፍል 6 ባህሉን ዘልቀህ ግባ | 87 |
| ክፍል 7 በወንጌል የመድረስ እድሎችን ፍጠር | 103 |
| ማጠቃለል | 117 |
| ብዙ ጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎች | 131 |

# ሪች አውት ዩዝ ሶልዩሽንስ

ሪች አውት ዩዝ ሶልዩሽንስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላሉ ለእያንዳንዱ ወጣት ትውልድ ኢየሱስ ላይ ትኩረት ያደረገ የወጣት አገልግሎትን ለመፍጠር የሚያስፈልገውን የማሰልጠንና ዘመናዊ ማቴርያሎችን ይሰጣል።

*መጋቢ *የወጣት መጋቢ *ወላጆች *የልጆች አገልጋይ *የበጎ ፈቃድ አገልጋዮች *ተማሪዎች

## ራእያችን

ኢየሱስ ለሚቀጥለው ትውልድ!

## ተልዕኳችን

ኢየሱስን ለመከተል ወጣቱ ትውልድ ላይ ተጽኖ የሚያደርጉ በአለም ዙሪያ ያሉ መሪዎችን ለማሰልጠንና ለማብዛት

## ስልታችን

ኢየሱስ ላይ ትኩረት ያደረገ የወጣቶች አገልግሎት የሚከተሉትን ነገሮች ወደማድረግ የሚወስድህን ወጣቱን ትውልድ ለማገልገል የፓራዳይም ሺፍት ይሰጣል

- በክርስቶስ ወደ ጠለቀ የቅርብ ግንኙነት ለመግባት
- ለእግዚአብሄር ህልውናና ሀይል በፍላጎት መጸለይ
- መሪዎችን በጥልቀትና በረጅም ጊዜ አገልግሎት መገንባት
- ተማሪዎችን ወደ ክርስቶስ በሙላት እንዲያድጉ ደቀ መዝሙር ማድረግ
- በግንኙነት ባህሉን ዘልቆ መግባት
- ተማሪዎችን በክርስቶስ ለመድረስ የወንጌል ስርጭት አጋጣሚዎችን መንደፍ

## አድማሳችን

በአለም አቀፍ ደረጃ ከ30 ከተማዎች በላይ ሪች አውት የወጣት ትውልድ መሪዎችን ያሰለጥናል።

በብሄራዊ ደረጃ ሪች አውት በአንድ ቤተ ክርስቲያን ወይም ኔት ወርክድ በሆኑ ቤተ ክርስቲያኖች ውስጥ ለከተማዎች፣ ለመካከለኛ ከተሞች እና ለገጠር የወጣት ትውልድ መሪዎች ስልጠናና ሪሶርሶችን ይሰጣል።

ለተጨማሪ ሪች አውት ዩዝ ሶልዩሽንስ ደብሊው ደብሊው ደብሊው ሪች አውት . ኦርግ ግባ

# መግቢያ

## በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ ወጣት ትውልድ አለ!

በአንተ ልብ ውስጥም አስቀምጧቸዋል!

ለኢየሱስ ክርስቶስ ወጣቱን ትውልድ መድረስ፣ ማስታጠቅና መንቀሳቀስ ለቤተ ክርስቲያን ከፍተኛውን ቅድሚያ እንደሚይዝ እውቃለን::

ነገር ግን ያንን የኢየሱስን አገልግሎት እንደምሳሌ በሚያንጸባርቅ መልኩ ማድረግ የምችለው እንዴት ነው?

ኢየሱስ ላይ ትኩረት ባደረገ የወጣቶች አግልግሎት አማካኝነት!

---

ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፥ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።
1 ቆሮ 3፡11

እንዲዳስሳቸውም ሕፃናትን ወደ እርሱ አመጡ፤ ደቀ መዛሙርቱም ያመጡአቸውን ገሠጹአቸው። ኢየሱስ ግን አይቶ ተቈጣና፦ ሕፃናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተዉ አትከልክሉአቸው፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደነዚህ ላሉት ናትና።እውነት እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባባትም አላቸው። አቀፉቸውም እጁንም ጭኖ ባረካቸው።

ማር 10፡13-16 (መልእክቱ)

---

# የመጨመር መንገድ

ኢየሱስ ላይ ትኩረት ያደረገ የወጣቶች አገልግሎትን ስትጨርስ፣ አገልግሎትህ ፍጹም የተለየ እንደሚሆን ተስፋ እናደርጋለን። መሻታችን ኢየሱስ ላይ ትኩረት ያደረገ የወጣቶች አገልግሎት ውስጥ ያሉ አገልግሎቶች ያው እንዳይሆኑ ነው። በርግጥ፣ ህልማችን የዚህ ተቃራኒ ነው።
አግልገሎትህ የትም ያለ ሌላ አገልግሎትን እንዳይመስል የእግዚአብር ልዩ መንካት እንዲኖረው ተስፋ እናደርጋለን። ለምን? ምክንያቱም በአንተና በቤተ ክርስቲያንህ አማካኝነት የአግዚአብሄር ልዩ መገለጫ ስለሆነ።

ኢየሱስ ላይ ያተኮረ የወጣቶች አገልግሎት ኢየሱስ አገልግሎትን እንዴት እንዳደረገና አንተም እርሱ ያደረገውን ነገር በአገልግሎትህ እንዴት እንደምታዛምድ የ "ትልቅ ስእል" እይታን ይሰጥሀል።

በመሠረቱ ጡንቻ የምትጨምርለት አጥንት ነው። የምታስጌጠው ቤት ነው። መላውን አገልግሎት ልታንጠለጥልበት የምትችል ሜንጦ ይኸውልህ።

የእኛን ማቴርያሎች ፍጹም ተጠቅመህ የማታውቅ ከሆነ፣ ወይም ከዚህ ዘዴ ጋር የማትተዋወቅ ከሆነ ይህንን እንደ መግቢያ ቁጠረው። ለመጀመር የሚያስፈልግህን ነገር ሁሉ ታገኛለህ።

የእኛን ማቴርያል ተጠቅመህ ከሆነ ወይም በስልጠና ፕሮግራሞች ላይ ተሳትፈህ ከሆነ፣ ይህንን መጽሐፍ ስራ ላይ ለማዋል ተጠቀም። ቅድሚያዎችህን እንድታስተካክል፣ ስራህን እንድታጠነክርና አገልግሎትህን እንድታጠራ ይረዳሀል።

ሌሎች ወጣት መሪዎችን ለማስታጠቅ ያለውን ተግዳሮት ከልብህ ካየኸው፣ ይህን የሚተላለፍ የሥልጠና መሳሪያህን ከግንዛቤ አስገባ።

# በግል በዚህ ስልጠና የሚታለፍበት መንገድ

1. በጊዜ ማቀጃህ እያንዳንዱ አንድ ሰአት የያዘ የስምንት ሰአት የጊዜ ርዝመቶችን ለይ። ይህንን በሳምንት አንዴ፣ በቀን አንዴ መመደብ ትችላለህ፤ ወይም በፍጥነት ላይ ከሆንክ በሁለት ወይም በሶስት ቀናት ይህን ለማድረግ ትሞክር ይሆናል።

2. እያንዳንዱን ክፍለ ጊዜ ተጠቀም። በተመደበው ሰአትህ ጊዜ ስልክህን ዝጋ። የሚረብሹ ነገሮችን አስወግድ። ከዚያም እያንዳንዱን ክፍል ከግቡ ጀምሮ እስከ ድርጊቱ እቅድ ድረስ በጸሎት መንፈስ ሆነህ አንብብ። እግዚአብሄር ምን እያለህ እንደሆነ ስማ። ማስታወሻ ውሰድ። ሀሳቦችህንና ጸሎቶችህን ጻፍ።እዚህ ሂደት ላይ በፍጥነት አትጓዝ።

3. ሲዲዎችን ከ ደብሊው ደብሊው ደብሊው ሪች. አውት. ኦርግ ላይ በነጻ አውርድ። ደጋግመህ አዳምጣቸው።

4. የስራ እቅድን በመጠቀም ተገቢ የስራ እርምጃዎችን ውሰድ። ይህ ማቴርያል ለጭንቅላት ስፖርት የታቀደ አይደለም። ይልቁን ራዕይህን እንድትከተል ራእይንና በተጨባጭ ሊለኩ የሚችሉ ርምጃዎችን ይሰጣል።

5. በጣም አስፈላጊ ነው ብለህ በምታናምናቸው አንድ ወይም ሁለት ቅድሚያዎች በፍጥነት ተግብር።

# በዚህ ስልጠና አማካኝነት ሌሎች መሪዎችን የምታሰለጥንበት መንገድ

ኢየሱስ ላይ ትኩረት ባደረገ የወጣቶች አግልግሎት ከሌሎች ጋር ስትሰራ ለአገልግሎትህ አስፈላጊው መሠረት የአመራር ቡድን እድገት እንደሆነ ቶሎ ትረዳለህ። ይህንን ስልጠና በበጎ ፈቃድ ሰራተኞችህ ራእይንና አቅጣጫን ለመፍጠር በቀላሉ አዳፕት ማድረግ ትችላለህ።

ራዕህን ለመግለጽና ከወጣቱ ትወልድ ጋር የራሳቸውን የአገልግሎት ራዕይ እንዲያገኙ መሪዎችህን ለማበረታታት ይህንን ስልጠና በተለዩ ወይም በበርካታ በተመደቡ ክፍለ ጊዜአት መጠቀም ትችላለህ። ይህንን ለበጎ ፈቃደኞችህ፣ ለወላጆች እና ለተማሪ መሪዎችህ ለማቅረብ የሚከተሉትን ነጥቦች ልብ በል፦

1. ከዚህ ማቴርያል ጋር ተላመድ:: ማስታወሻዎችን ያዝ ደግሞም ይህንን ትምህርት በራስህ ታሪኮችና ምሳሌዎች አዳብር::

2. የሥልጠናውን ቦታ ወስን:: ከተቻለ ስብሰባውን በቤትህ ወይም ከአባላት በአንዱ ቤት ውስጥ ለማድረግ አቅድ:: በመኖሪያ ቤቱ መደበኛ ባልሆነ ስፍራ ወይም በምግብ ጠረጴዛው ዙሪያ መሰብሰብ ዘና ያለ ሁኔታን ይፈጥራል::

3. ለእያንዳንዱ ስብሰባ ሰአት ወስን:: ለእያንዳንዱ ጊዜ ከአንድ ሰአት እስከ 1 ½ አቅድ፤ 15 ደቂቃ ለጸሎት፣ ለክለሳና ለማካፈል፣ 45 ደቂቃ ለማቅረብና ለውይይት፣ ከዚያም 15 ደቂቃ ለተማሪዎቹ ለመጸለይ::

4. ማቴርያሎችን ስጥ:: ለቡድንህ ኢየሱስ ላይ ትኩረት ያደረገ የወጣቶች አገልግሎት ቅጂዎችን ግዛ:: ከደብሊው ደብሊው ደብሊው. ሪች. አውት. ኦርግ ይህንን ኖት ቡክና የሌሎች ማቴርያሎች ቅጂዎችን እዘዝ::

5. በሚገባ ተዘጋጅ:: በክፍለ ጊዜዎቹ በሚገባ ለመምራት ዝግጅትህን አስቀድመህ ጀምር::

6. በጊዜ ጀምር:: መሪዎችህ ያደረጉትን መሠጠት አክብር::

7. ውይይቶችን በመስመር ላይ ቀጥል:: ጥያቄዎችን በግልጽና በአጭሩ ግለጽ::የእያንዳንዱን ሰው አስተያየት አክብር:: ከቅዱሳት መጻህፍት ጋር በቅርበት ቆይ:: የተለመዱ ወይም የማስመሰል መልሶችን ተገዳደር:: ጥያቄዎችን ጠይቅ:: እያንዳንዱ ሰው መሳተፉን አረጋግጥ::

8. ተዛምዶ ላይ አጽኖት አድርግ:: በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ መጨረሻ ላይ ቡድንህ አስተያየት እንዲሰጥና በስራ እቅዱ ላይ እንዲጽፍ ብዙ ጊዜ ስጥ:: የጻፉትን ነገር ለመወያየት እድል ስጣቸው:: በሳምንቱ የሚወስዱትን አንድ ድርጊት እንዲመርጡ ጠይቃቸው:: በክፍለ ጊዜዎቹ መካከል እርስ በርስ እንዲበረታቱ ተጠያቂ ጓደኞችን መድብላቸው::

በአመራር ቡድንህ ኢንቨስት ለማድረግ ቀጣይ ርምጃ ለመውሰድ ገንቢ መሪዎች ሲሪስ 3 የመጽሐፍ ስብስቦችን እዘዝ፡- ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የግል ምልልስ፣ ስህይወትና ስአገልግሎት ራእይ እና ተማሪዎችን ስመምራት አስፈላጊ መሳሪያዎች። ወደ ደብሊው ደብሊው ደብሊው. ሪች. አውት. ኦርግ ግባ።

# የእኔ ጸሎት ለአንተ

የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ ጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ። ይህም የልባችሁ ዓይኖች በሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለ ግነት ምን እንዲሆን ለምናምን ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው፤

ኤፌ 1፡17-19ሀ

# ትልቁን ስእል ተመልከት

## ግብ

ኢየሱስ ላይ ትኩረት ያደረገ
ራዕይን ለመጨበጥ

ክፍለ ጊዜ 1

# ትልቁን ስእል ተመልከት
ክፍለ ጊዜ 1

## ኢየሱስ ላይ ትኩረት

ወንጌሎን ስንመለከት፣ የአገልግሎት ተለዋዋጭ ዘዴን ኢየሱስ እንደተከተለ ማየት ትችላለህ:: ይህን የገለጸው በሰንበት ቀን በመፈወሱ ፈሪሳውያን ከከሰሱት በኋላና እራሱን ከእግዚአብሔር ጋር ካስተካከለ በኋላ ነው::

> እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ ወልድ ከራሱ ሲያደርግ ምንም አይችልም፤ ያ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ይህን እንዲሁ ያደርጋልና።
>
> ዮሐ 5፡19

ከአባቱ ጋር በጣም ቅርብ በሆነ ግንኙነቱ ኢየሱስ መመሪያዎችን ከእርሱ ተቀበለ ደግሞም ተከተላቸው:: ያም በየለቱ የሚያደርገውን ነገር ሀይለኛ ብቻ ሳይሆን ልዩም አደረገ:: ስለ አገልግሎታችን አንድ ነገር በእርግጠኝነት መናገር እንችላለን:: ከእርሱ ጋር በቀረበ ህብረት ላይ የተመሠረቱ ሀይኛና የተለዩ እንደሆኑ ይፈልጋል:: ኢየሱስ ላይ ትኩረት ባደረገ የወጣቶች አገልግሎት የማሰልጠን ሂደት ውስጥ የማለፍ ውጤት እንደማንኛውም ሰው አገልግሎት የሚመስል አገልግሎት ለመፍጠር ሳይሆን በኢየሱስ በተመራ የፍላጎት መከተል የተለየና ብርቱ ነገርን ለመገንባት ነው እንጂ:: ያ ደግሞ የሚመጣው አብ ምን እያደረገ አይቶ እንደዛው ማድረግን ከሚፈልግ ልብ ነው::

ኢየሱስ አባቱን ይመለከት ነበር:: እኛም ኢየሱስን እናያለን:: ስንመለከት ምን እናያለን? ኢየሱስ ባደረገው ነገር ተደጋግሞ የተካሄደን አካሄድ እንመለከታለን:: አገልግሎታችንን እንዴት ማካሄድ እንዳለብን አቅጣጫ የሚሰጠንን ኢየሱስ ያደረገበትን መርሆች እናገኛለን:: የማይለወጥ ወይም ልማድን የሚደግም በፍጹም ባለመሆን፣ አባቱን በፍጹም ሳጥን ውስጥ ሳይከት፣ ኢየሱስ ስልቱን አደረገ:: ምንድን ነው የሚመስለው?
**ኢየሱስ አባቱን ታዘዘ።** በጌቴሴማኔ የአትክልት ስፍራ የኢየሱስ የሀዘን ተሞክሮ ለአባቱ ያለውን መታዘዝ ያመለክታል:: የኢየሱስ ተሞክሮ እንድንታዘዝዝ ይረዳናል::

**ኢየሱስ በደቀ ቀመዛሙርቱ ላይ ኢንቨስት አደረገ።** በተራ ምልከታ ብቻ፣ ኢየሱስ በአስራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ላይ ያደረገውን ኢንቨስትመንት ማየት እንችላለን:: ከሦስት አመት በላይ እስከዛሬ ተቀይሶ በማያውቅ ጥልቅ በሆነ የመሪነት ስልጠና ውስጥ አሳለፋቸው:: አገልግሎትን እንዲለማመዱ ከርሱ ጋር ወሰዳቸው እጃቸውንም ሲያፍታቱ ደገፋቸው:: ይህንን በማድረግ፣ የምስራቹን እንዲሰብኩ፣ የተሰበሩ ልቦችን እንዲፈውሱና የታሰሩትን ነጻ እንዲያወጡ መራቸው:: በስተመጨረሻም፣ በእርሱ ያዩትን አገልግሎት በራሳቸው በተለየ ሁኔታ እንዲያካሂዱ ሀይልን ሰጣቸው:: በውጤቱም፣ አለምን የገለበጠ የመሪዎች ቡድንን አፈራ::

**የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት በተራቸው ህይወታቸውን በሌሎች ላይ ኢንቨስት አደረጉ።** በደቀ መዝሙርነት አማካኝነት በሌሎች ህይወት ላይ ኢንቨስት የማድረግ የሀይለኛ መባዛት ውጤት የኢየሱስ አገልግሎት ማእከል ነበር ስለዚህም የጥንቷ ቤተ ክርስቲያንም የአገልግሎት ማእከል ነበር:: ለእግዚአብሄር መንግስት ሰዎች በሰዎች ላይ ኢንቨስት አደረጉ:: ያም በዙረያ ያሉትን ሰዎች በለወጠ በስተመጨረሻም አለምን በለወጠ በብርቱ ሀይል ቤተ ክርስቲያንን ወደፊት ገፋ:: “የኢየሱስ አገልጋዮች” እንዲሆኑ “የኢየሱስ ተከታዮች” ትንሽ ቡድን ላይ ኢንቨስት ማድረግ ሊደረጉ ከሚችሉ አገልግሎቶች ሁሉ የላቀው ነው:: ደግሞም፣ ኢየሱስ ባደረገው መንገድ ከተደረገ፣ አለማችንን ይለውጣል::

ለኢየሱስ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ስለተመለከቱ በጥንቷ ለነበሩ ደቀ መዛሙርት በወንጌል መልካም ዜና አለማቸውን መቀየር ህይወትን የገዛ ቅድሚያ ነበር:: ሁሉንም አጥሮች አፈረሰ ደግሞም ከሴተኛ አዳሪዎች፣ ከለምጻሞች፣ ከደሆች፣ ከአንካሶችና ከእውሮች ጋር አብሮ በመሆን የተስተካከለ የጨዋታ ሜዳን ፈጠረ:: ለእኛ እንደ ኢየሱስ ሌሎችን ደቀ መዝሙር ማድረግ ሰዎችን ወደ ብስለት ይመራል ፤ ከብስለት ደግሞ ከቤተ ክርስቲያን አጥር ውጪ ወዳለ አገልግሎት ይመራል::

ለኢየሱስ፣ ያ አገልግሎት ህዝብን ጠራ:: ማስተማር፣ መፈወስ፣ መስበክ፣ አጋንንትን ማውጣት፣ በአምስት ቁራጭና በሁለት አሳ አምስት ሺዎችን መመገብ - ያደረገው ነገር ላይ ተጸኖ አላደረገም፤ ኢየሱስ የትኩረት ሁሉ ትኩረት ነበር! ስለ ደቀመዛሙርቱ ወይም ደቀ መዛሙርት ስለ ማድረጊያው ዘዴ አልነበረም:: ስለ አስገራሚዎቹ ተአምራት፣ ስለመሠረታዊው ትምህርት፣ ወይም ስለሌላ ነገር አልነበረም:: ስለ ኢየሱስ ነበር! ማንነቱና ሊያደርገው የመጣበት ነገሮች ነበሩ ዋና ቁም ነገሮች:: ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምንሻው ይህንን - ኢየሱስ ላይ ትኩረት ያደረገ የወጣቶች አገልግትን ነው:: የትኛውም ሌላ አይነት አገልግሎት ባዶና ያልተሟላን ያደርገናል:: ልክ እንደ ኢየሱስ፣ ለዘላለም የማይደመሰስ የዘላለማዊነትን አሻራ ለማሳረፍ ከፈልግን፣ ኢየሱስን ትኩረት እናደርገዋለን::

# ብርቱ ጥያቄዎች

የትጋ እንዳለን በትክክል መረዳት ለብዙዎቻችን ቀላል አደለም:: ነገር ግን የቱጋ እንዳለን ማወቅ መድረስ የምንፈልገውጋ ለመድረስ ብቸኛው መንገድ ነው:: ስለዚህ ምን ያህል ኢየሱሰ ተኮር እንደሆንክ ለማወቅ እነዚህን ጥያቄዎች ጠይቅ:: ከአንድ እስከ አስር በማለት መልስ:: 1 ዝቅተኛው ነው 10 ደግሞ ከፍተኛው ነው::

1. ከኢየሱስ ጋር ያለ ቅርበትን ለመከታተል የጊዜ መጠንንና የተነጣጠረ ትኩረትን ለመስጠት መጠንን የምትለካውእንዴት ነው?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10
2. አንተ፣ በጎ ፈቃደኞችህ፣ ወላጆች፣ እና ተማሪዎች መደበኛ ሰአትን የምትመድቡት እስከ ምን ድረስ ነው? ከሌሎች ጋር እርስ በርስና ኢየሱስን ለሚፈልጉ ተማሪዎች ለመጸለይ የምታጠፋው ጊዜ ምን ያህል ነው?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10
3. ከጎልማሳ በጎ ፈቃደኞች ጋር ለኢየሰስ፣ ለርስ በርስና ለተማሪዎች የህብረት አገልግሎት ምን ያህል የተሰጡ ናቸው?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10
4. በአገልግሎትህ ምን ያህል ፐርሰንቱ ናቸው ጥልቅ በሆነ፣ በተሰጠ፣ ቀጣይነት ባለው የደቀ መዝሙርነት ቡድን ውስጥ ያሉት?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10
5. በካምፓስ ውስጥ በጎ ፈቃደኞችህ እና ተማሪዎች ኢየሱስን በሰዎች ላይ እንደ ንቁ ተጽኖ አድራጊ ራሳቸውን የሚያዩት ምን ያህል ፐርሰንቱ ናቸው የማያምኑት?

   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10
6. በመጨረሻው የወንጌል ስርጭትህ የጠቅላላ ተማሪዎች ቁጥር ስንት ፐርሰንት ናቸው የማያምኑት?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

እነዚህን ጥያቄዎች በታማኝነት መመለስ የወጣቶች አገልግሎትህን የምር እንድታየው ያደርግሃል:: ውጤቱም እነዚህ ጥያቄዎች ለውጥን እንድትራብ ያደርጉሀል ብለን ተስፋ እናደርጋለን:: እያንዳንዱን ክፍለ ጊዜ እንድትከተል፣ ከዚያም ከተወሰነ ክፍለ ጊዜ ጋር በተያያዙ ተጨማሪ ጥያቄዎች ላይ ምላሽ እንድትሰጥ እድል ይኖርሃል::

# የወጣቶች አገልግሎት መርሆች

### ኢየሱስ ላይ ትኩረት ያደረገ የወጣቶች አገልግሎትን ራዕይ እንዴት ነው የምንጨብጠው?

## ራዕዩን አግኝ

ማቴ 9፡35-38ን ተመልከት:: በዚህ አውድ ውስጥ ኢየሱስ ላይ ትኩረት ያደረገ የወጣቶች አገልግሎትን ራዕይ እንድናገኝ የሚመራንን ፍንጭ እናገኛን::

> ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ፥ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ፥ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ፥ በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ይዞር ነበር። ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ፥ አረኛ እንደ ሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም ነበርና አዘነላቸው። በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን፦ መከሩስ ብዙ ነው፥ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤እንግዲህ የመከሩን ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት አላቸው።
>
> ማቴ 9፡35-38

በቁ 35 ውስጥ ኢየሱስ ከሰዎች ጋር እንዴት ዲል እንዳደረገ ምን ፍንጭ ትመለከታህ?

በቁ 37-38 ደቀመዛርቱን ሲያዛቸው ኢየሱስ ስለራሱ ራዕይ ምን ፍንጭን ሰጣቸው?

የአራቱ ወንጌላት ፈጣን ጥናት ወይም ጥልቅ ምርምር በክርስቶስ እንደተኖረ ወደምናየው ወደ መሠረታዊ አስፈልጎቶች ይወስዳል:: ማርቆስ 1-4ን ወይም አራቱን ወንጌላት አንብብ! ሁሉም መንገዶች ወደ ተመሳሳይ፣ ኢየሱስ ህይወቱንና አገልግሎቱን ባደረገበት ወደ መሰረታዊው መንገድ ይወስዳሉ:: እያንዳንዱም ገጽ ኢየሰስ ላይ ትኩረት አድርጓል::

## ወጣቱን ትውልድ ግለጽ

በማቴ 9፡37 ውስጥ ኢየሱስ በዙርያው የነበረውን “ህዝብ” እንዴት ነው የገለጸው?

እነዚህን ቃላት ከአሁን የወጣቶች ባህል አንጻር እንዴት ትገልጻቸዋለህ?

የተጠቁ

ረዳት አልባ

እረኛ የሌላቸው በጎች
ዛሬ ወጣቱን ትውልድ ኢየሱስ በራሱ ገለጻ በትክክል እንደሳላቸው ጥናት ያመላክታል።

---

# በየ24 ሰአቱ . . . .

17፣297 ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ያቋርጣሉ
7883 ተማሪዎች እንደተደፈሩና ቸል እንደተባሉ ሪፖርት ይቀርባል
4248 ተማሪዎች ይታሰራሉ
2861 ተማሪዎች ትምህርት ይተዋሉ
1329 ህጻናት ከታዳጊ ወጣቶች ይወለዳሉ
367 ተማሪዎች በድራግ መውሰድ የተነሳ ይታሰራሉ
180 ሰዎች በጭከና ወንጀል ይታሰራሉ
9 ተማሪዎች የግድያ ሰለባዎች ናቸው
5 ተማሪዎች ራሳቸውን ያጣፋሉ
1 ተማሪ በኤድስ ይሞታል
*በትምህርት ቀን ስሌት ላይ የተመሰረተ (ሰባት ሰአት በያዙ 180 ቀናት) © ቺልድረንስ ዲፌንድ ፊንድ

---

## ለቁጥሮቹ ስም ስጥ

ማቴ 9፡36 ውስጥ በዙሪያው ስላሉት ሰዎች ምን ተሰምቶት እንደነበር ለመግለጽ ስለ ኢየሱስ ጥቅም ላይ የዋለውን ቃል አግኝ።

የኢየሱስን ገለጻ የሚገጥም የአንድ ወጣት ሰውን ስም ጻፍ።

ያንን ሰው በህይወት ዘይቤው፣ በልማዶቹ፣ በምርጫዎቹ፣ እና በሚያደርጋቸው ድርጊቶች ግለጸው::

ልክ ኢየሱስ በዙርያው ስላሉት ሰዎች እንደተሰማው ስለዛ ተማሪ ይሰማሀልን? ለዛ ታዳጊ ወጣት ጸሎትን ጻፍ::

ኢየሱስ ላይ ትኩረት ያደረገ የወጣቶች አገልግሎት ላይ የተማርከውን እያንዳንዱን ነገር ያንተ ታዳጊ ወጣት፣ ወይም እርሱን / እርሷን የሚመስሉትን በክርስቶስ ለመድረስ ጥቅም ላይ አውል::

## እንዴት ልዩነት እንደምታመጣ ተመልከት።

ማቴ 9፡38ን በሚገባ ተመልከት:: ያለ እረኛ እንዳሉ በጎች ተጥለውና ተረስተው በነበሩ ሰዎች ህይወት ልዩነትን ለማምጣት ለደቀ መዛርቱ በመናገር ኢየሱስ በግልጽ ስልትን ያስቀምጣል:: የተጠቀመበትን መንገድ ግልጽነት ልብ በል::

| ኢየሱስ፡ "የመከሩን ጌታ ለምኑት . . . ሠራተኞችን እንዲልክ . . .ወደ መከሩ::" | | | |
|---|---|---|---|
| ድርጊት፡ | ጸሎት<br>ኢየሱስን<br>ለመከተል | ማሰልጠን<br>መሪዎችን<br>ለማብዛት | ማዳረስ<br>ሰዎችን<br>ለመድረስ |
| ስልት፡ | ከክርስቶስ ጋር ወደ ጠለቀ ነገር ሂድ<br>በፍላጎት ጸልይ | መሪዎችን ገንባ<br>ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር አድርግ | ባህልን ዘልቀህ ግባ<br>የመድረስን አጋጣሚዎች ፍጠር |

# ትልቁን ስእል መመልከት




ትልቁን ስዕል እንዴ ከተመለከትን፣ ከኢየሱስ ጋር ህይወት በሚቀይር ህብረት በሁሉም ትምህርት ቤት ሁሉንም ተማሪ የመድረስ ግብን እንዴት መከተል እንደሚቻልም ጭምር እንጂ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትን ለመገንባት ብቻ አይደለም በትክክል ማየት የምንችለው።

# በትልቁ ስዕል ላይ አስተያት ስጥ

ከማቴ 9:35-38 የተወሰደ ይህ ኢየሱስ ላይ ትኩረት ያደረገ ስልት በአራቱ ወንጌላት ውስጥ በወጥነት ኢየሱስ በገለጻቸው ስድስት አስፈላጊ ነገሮች ላይ የተመሠረተ ነው። እነዚህ ነገሮች በህይወትህና በአገልግትህ ላይ የበለጠ በጥልቀት እንዴት ኢንግሬይንድ መሆን እንደሚችሉ ሀሳብ ስጥ።

## ወደ ክርስቶስ ውስጠኛ ነገር ሂድ።

ከኢየሱስ ጋር ያለህን ህብረት እንዴት ነው ጥልቅ የምታደርገው? ከኢየሱስ ጋር የቀረበና የፍቅር ህብረትን ተከታተል ከዚያም በዙሪያህ ላሉ ሰዎች የርሱን ባህሪ በማንጸባረቅ ያንን ህብረት ክርስቶስን በመታዘዝ ኑረው፣ (ማር 1:7-8)

## በፍላጎት ጸልይ

የእግዚአብሄርን ህልውናና ሀይል ወዳገልግሎትህ በጸሎት የምትጋብዘው እንዴት ነው? ተማሪዎችን ለመድረስና ደቀ መዝሙር የማድረግ ልብና ችሎታ ያላቸውን ወጣቶች አሰልጥን። (ማር 1:16-20)።

## ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር አድርግ

እንዴት ነው ተማሪዎችን መንፈሳዊ ፍላጎትን እንዲያሳድጉና በጓደኖቻቸው ላይ መንፈሳዊ ተጽኖ አምጪዎች እንዲሆኑ ደቀ መዝሙር የምታደርጋቸው? በትናንሽ ደቀ መዝሙር የማድረግ ህብረቶች ወደ ብስለት እንዲሄዱ ተማሪዎችን ተገዳደራቸው (ማር 3:13-15)።

## ባህሉን ዘልቀህ ግባ

መሪዎችህን፣ ወላጆችንና ተማሪዎችህን የተማሪዎችን ባህል ዘልቀው እንዲገቡ የምታነሳሳውና የምታንቀሳቅሳቸው እንዴት ነው? በእነርሱ አለም ውስጥ ጊዜህን በማሳለፍ ተማሪዎች ወዳሉበት ሂድ ደግሞም በእነርሱ ባህል ጓደኞቻቸውን እንዲደርሱ አሰልጥናቸው (ማር 1:40-42)።

## የመድረስ አጋጣሚዎችን ፍጠር

ተማሪዎች ጓደኞቻቸውን እንዲደርሱ ለተማሪዎች የመድረስ አጋጣሚዎችን ዲዛይን የምታደርገው እንዴት ነው? የማያምኑ ጓደኞቻቸውን ኢየሱስን ወደ ማወቅ እንዲያመጡ ከባህል ጋር የሚገናኙ ተሞክሮዎችን ፍጠር። (ማር 4፡1-2)።

## ተግባራዊ እርምጃዎች

ኢየሱስ ላይ ትኩረት ያደረገ የወጣት አገልግሎትን ትልቅ ስዕል ማየት ማለት አጠቃላዩን ጽንሰ ሀሳብ አገኘህ ማለት ነው።
ትልቁን ስእል ለራስህ ራእይ ለመቸበጥ እነዚህን ተግባራዊ ርምጃዎች ውሰድ

- ማቴ 9:35-38ን በቃልህ አጥና። በአእምሮህ እና በልብህ እስኪቀረጽ ድረስ ደግመህ ደጋግመህ ተናገረው።
- በዚህ ኖት ቡክ ላይ ስለተደራሲዎችህ እንዲያስታውስህ “እረኛ እንደሌለው በግ የተጣለና የተረሳ” ስሙን የጻፍከውን ተማሪ ስእል አስቀምጥ።
- በአሁኑ አገልግሎትህ የትኞቹ ክንውኖች ኢየሱስ ላይ ትኩረት ላደረገ የወጣት አገልግሎት ንጥረነገሮች አስተዋጾ እንዳደረጉ እና የትኞቹ ደግሞ እንዳላደረጉ ለማወቅ ቀጥሎ ባለው ቻርት ላይ ሙላ። በገጹ ወደታች የክንውኖችህን ዝርዝር በመጻፍ ጀምር። ከዚያም በሚዛመዱአቸው ወይም “በማይዛመዱአቸው” ኮለም ላይ ምልክትን አድርግ።

ከ2-7 ያሉት ክፍለ ጊዜአት እያንዳንዱን ኢየሱስ ላይ ትኩረት ያደረገ የወጣቶች አገልግሎት ንጥረነገሮችን በጥልቀት ይመለከታል ደግሞም የኢየሱስን ራዕይ ለአግልግሎህ ይበልጥ በግልጽ እንድታይ ይመራሀል።

# የአሁን ክንውኖች ምርመራ

| የአሁን ጊዜ ክንውኖች ወይም አገልግሎቶች | ከክርስቶስ ጋር ወደ ጠለቀ ነገር ሂድ | በፍላጎት ጸልይ | መሪዎችን አስታጥቅ | ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር አድርግ | ባህሉን ዘልቀህ ግባ | የመድረስ አጋጣሚዎችን ፍጠር | አይገጥምም |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | |

# ከክርስቶ ጋር ወደ ጠስቀ ነገር ሂድ

## ግብ

ከኢየሱስ ጋር የቀረበ ህብረትን ለመከተል

ክፍለ ጊዜ 2

# ወደ ክርስቶስ ውስጠኛ ነገር ዘልቆ መግባት
ክፍለ ጊዜ 2

## ኢየሱስ ላይ ትኩረት

አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ወደ ውስጥ እድንገባ ይጠሩናል!

**እግዚአብሔር አብ፡፡** "በመጀመሪያ እግዚአብሄር . . ." በማለት መጽሐፍ ቅዱስ ይጀምራል፡፡ ከጊዜ በፊት እግዚአብሄር ነበር! ጊዜ ሲጀምር፣ ሁሉን ነገር ፈጠረ - "ሰማይና ምድርን" (ዘፍ 1፡ 1)፡፡ ከፍጥረት ጀምሮ፣ አሁን፣ በዚህ ጊዜ በፍጥረቱ ላይ ገዢ እግዚአብር ነው፡፡ ዘማሪው በዚህ መልክ ገልጾታል፡ "እግዚአብሔር ዙፋኑን በሰማይ አዘጋጀ፥ መንግሥቱም ሁሉን ትገዛለች፡፡" (መዝ 103፡19)፡፡ ያ ጭብጥ በአጠቃለይ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተደጋግሞ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ፣ ጳውሎስ በኤፌ 4፡6 "ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ፡፡ " እንደሆነ ይጽፈል፡፡ በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ወደፊትም እንደሚኖር ይናገራል፡፡ ለወደፊትም መግዛቱን ይቀጥላል፡፡ ሐዋርያው ዮሐንስ "በሰማይና በምድርም ከምድርም በታች በባሕርም ላይ ያለ ፍጥረት ሁሉ በእነርሱም ውስጥ ያለ ሁሉ፦ በረከትና ክብር ምስጋናም ኃይልም ከዘላለም እስከ ዘላለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው፥ ለበጉም ይሁን ሲሉ ሰማሁ፡፡" (ራዕይ 5፡13) ብሎ ይጽፋል፡፡ እግዚአብሄር በፍጥረቱና በፍጥረታቱ ላይ ይገዛል ይነግሳልም፡፡

**እግዚአብሔር ወልድ፡፡** እግዚአብሄር አብ ሥልጣን በሙሉ በኢየሱስ ላይ አስቀምጧል፡፡ "ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ፡፡ " አለ ኢየሱስ (ማቴ 28፤18)፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ በተደጋጋሚ የኢየሱስን የመጨረሻ ሥልጣን ገልጾአል፡፡ በኤፌሶን ደብዳቤው ላይ ያንን የባለሙሉ ስልጣን ሀይል እንዲህ ገልጾታል፡፡

በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለ ጠግነት ምን እንዲሆን ለምናምን ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው፤ ክርስቶስንም ከሙታን ሲያስነሣው ከአለቅነትና ከሥልጣንም ከኃይልም ከጌትነትም ሁሉ በላይና በዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሊመጣ ባለው ዓለም ደግሞ ከሚጠራው ስም ሁሉ በላይ በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ሲያስቀምጠው በክርስቶስ ባደረገው ሥራ የብርታቱ ጉልበት ይታያል፤ ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተ ክርስቲያን ሰጠው። ኤፌ 1፡19-22

የኢየሱስን ማንነት ሲገልጽ የእብራውያን ጸሀፊ በእብራውያን 1፤3 ወልድን እንዲህ ገልጾታል፡

- ወራሽ - አባቱ ኢየሱስን “ሁሉን ነገር ወራሽ” አድርጎታል
- ፈጣሪ - ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ኢየሱስ “አጽናፈ አለሙን ፈጥሯል”
- አንጸባራቂ - ኢየሱስ “የእግዚአብሄር ክብር ነጸብራቅ” ተደርጎ ተገልጾልናል። ኢየሱስ የእግዚአብሄር መልክ መስታወት ነው፡ “የማንነቱ ትክክለኛ ምትክ”
- ደጋፊ- “በስልጣን ቃል” ለእያንዳንዷ ደቂቃ የአጽናፈ አለሙን ሲስተም በሙሉ ኢየሱስ ደግፎ ይዟል
- ቀዳሽ- በመስቀል ላይ ራሱን ለሞት በማስገዛት ኢየሱስ “ለሀጢአት መንጻትን” ሰጠ።
- ገዢ- ከትንሳኤው በኋላ በሚገዛበትና በነገሰበት “በሰማይ በክብሩ ቀኝ ተቀምጧል”

ያለ ጥርጥር ኢየሱስ ጌታ ነው! አንድ ቀንም “ጉልበት ሁሉ ለስሙ ይንበረከካል ምላስም ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ይመሰክራል “ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፥መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው። ”
(ፊሊ 2፡10-11)።

**እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ::** ወልድ፣ በውስጣችን እንዲኖር በመንፈስ ቅዱስ አስተናገደን:: እግዚአብሄር ማን እንደሆነ፣ ኢየሱስ ለእኛ ምን እንዳደረገ እና በመንፈስ ቅዱስ ሀይል እንዴት መኖር እንዳለብን እንድናወቅ:: ሐዋርያው ጳውሎስ "ልጆችም ስለ ሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚጮኽ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ::" (ገላ 4፡6) በማለት ይነግረናል:: ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች ሳንሆን ልጆች ስለሆንን:: ይልቁን "አግዚአብሄር ወራሽም አድርጎናል" (ገላ 4፡7)::

መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ስለሚኖር ኢየሱስን እንድንከተል ፍላጎትን፣ እንደሚፈልገን እንድንኖር ሀይልን፣ እና ለዘላለም የሆነውን የተስፋ ቃል ይሰጠናል:: ይህ እውነት ስለሆነ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ "ነገር ግን እላለሁ፥ በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ:: በመንፈስ ብንኖር በመንፈስ ደግሞ እንመላለስ::" (ገላ 5፡16፣25) በማለት ይፈታተነናል::

አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በመላው አጽናፈ አለም ላይ እንደነገሱ መደምደም እንችላለን:: የእግዚአብሄር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ስለሆንን ከእርሱ ጋር ወዳለ ቅርብ ግንኙነት የገባን፣ ለእግዚአብሄር አገዛዝና ግዛት - ከክርስቶስ ጌትነት በታች ለመኖር ወስነናል:: በየለት ውሳኔዎቻችን "አንተ አምላክ ነህ እኔ አይደለሁም!" እያልን እውቅና እንሰጣለን:: ሀሳቦቻችንን፣ ስሜቶቻችንን፣ አመለካከቶቻችንን እና ድርጊቶቻችንን ለክርስቶስ ለማስገዛት እንሻለን::

**በእግዚአብሄር ጸጋ::** በህይወታችን የኢየሱስ ጌትነት ማለት የቅርብ፣ የግል ህብረትን ከእኛ ጋር እየተከተል ነው ማለት ነው:: በዛ ህብረት ውስጥ ተገቢ ስፍራችንን ለማግኘትና ከክርስቶስ ጋር በቀረበ ሁኔታ ለመኖር እንድናደርግ የሚፈልገውን ነገር ለማድረግ መወሰን አለብን:: በእያንዳንዱ ቀን ተስፋዎቻችንን፣ ህልሞቻችንን፣ መሻቶቻችንን እና ውሳኔዎቻችንን ለእርሱ ስንሰጥ በእርሱ እየተደሰትን ከጊዜ ወደ ጊዜ በእርሱ ህልውና ውስጥ መኖር እንችላለን!

ከኢየሱስ ጌትነት ስር መኖር ምን እንደሚመስል ሐዋርያው ጳውሎስ በጣም የጠራ ግልጽ ስእልን ይሰጣል:: ጳውሎስ "በስጋ ውስጥ

መውጊያ" ነበረው:: እኛ ሁላችን እነዚያ ነገሮች አሉን:: ምናልባትም ይህ አካላዊ ድካምን፣ አሳዛኝ ህብረትን፣ የሚወዱትን ማጣትን፣ ወይም የሀጢአተኝነት ልማድን ሊወክል ይችላል:: በክፍት ቦታው መሙላት እንችላለን:: እግዚአብሔር የጳውሎስን "መውጊያ" የማያቋርጥ ስብራትን ለመፍጠር ተጠቀመበት:: እግዚአብሔር እኛም ስብራትን እንድንለማመድ ይፈልጋል:: ለኢየሱስ ጌትነት መገዛት የምንችለው በስብራታችን ብቻ ነው:: ጳውሎስ መውጊያውን እንዲያነሳለት ለመነ:: እርሱ ግን አላነሳለትም:: ይልቁን "እርሱም፦ ጸጋዬ ይበቃሃል፥ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና አለኝ:: እንግዲህ የክርስቶስ ኃይል ያድርብኝ ዘንድ በብዙ ደስታ በድካሜ ልመካ እወዳለሁ::" አለው (2 ቆሮ 12:9)::

የክርስትናን ህይወት በራሳችን ብርታት አንኖርም:: በዚያ ፈንታ በእግዚአብር ጸጋ በመስቀሉና በትንሳኤው አማካኝነት በሱፐርናቹራል ችሎታው ነው የምንኖረው:: በስብራታችን አማካኝነት በእግዚአብሔር ጸጋ መኖርን እንማራለን:: በዚያ ጸጋ አማካኝነት በእኛ ውስጥ ሀይሉን ይለቃል:: ስለዚህ እንደጳውሎስ "እርሱም፦ ጸጋዬ ይበቃሃል፥ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና አለኝ:: እንግዲህ የክርስቶስ ኃይል ያድርብኝ ዘንድ በብዙ ደስታ በድካሜ ልመካ እወዳለሁ:: ስለዚህ ስለ ክርስቶስ በድካም በመንገላታትም በችግርም በስደትም በጭንቀትም ደስ ይለኛል፤ ስደክም ያን ጊዜ ኃይለኛ ነኝና::"

ማለት እንችላለን ( 2 ቆሮ 12:9-10)::
በስብራታችን አማካኝነት የክርስቶስን ህልውናና ሀይል እንለማመዳለን::

---

ኦ እግዚአብሄር ሆይ መልካምትህን ቀምሻለሁ ደግሞም አርክቶኛል ሌላ ተጨማሪ እንድጠይቅም አድርጎኛል። በህመም ተጨማሪ ጸጋ እንደሚያስፈልገኝ ተረድቻለሁ። መሻት በማጣቴ አፍሬአለሁ። ኦ እግዚአብሄር ሆይ፣ ስላሴ፣ ልፈልግህ እፈልጋለሁ፤ በመናፈቅ እንድሞላ እናፍቃሁ፤ አሁን የበለጠ የተጠማ ለመሆን እጠማለሁ።

ኤ. ደብሊው. ቶዘር

---

ለቅርብ ግንኙነት ጥሪ። በአጽናፈ አለሙ ላይ የሚገዛውና የነገሰው፣ ጥልቀት ባለው ፍቅር ይወደናል በእኛም ደስ ይለዋል። አሁንም እንኳን በፍቅር እየተካታተለን ነው። እንድንከተለው በክርስቶስ መንገድ ጠርጎልናል። እርሱን ለማወቅና ለመውደድ ሁሉንም ነገር ሰጥቶናል። እያንዳንዳችንን “ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ። ” (ማቴ 22፡37) እያለ ይጠራናል። ከኢየሱስ ጌትነት በታች ወደን እንድንከተለው በየለቱ ከእርሱ ጋር ወደ ቀረበ ህብረት እንድንገባ ይጠራናል። በእያንዳንዱ ቀን ወደርሱ ጥልቅ ነገር ለመግባት ስንመኝ ያን ጊዜ ኢየሱስን እንደ ጌታ እናውቀዋለን!

# የመተው ጸሎት

አባት ሆይ፣ ራሴን በእጆችህ ላይ እተዋለሁ፤
የምትፈቅደውን በእኔ አድርግ።
ለምታደርገው ነገር ሁሉ አመሰግንሃለሁ።
ለሁሉም ዝግጁ ነኝ፣
ሁሉንም እቀበላለሁ።
በእጆችህ ውስጥ ነፍሴን ላንተ እሰጣለሁ
ጌታ ሆይ ስለምወድህ
ራሴን ልሰጥህ ወደድኩ
ራሴን ለእጆችህ አሳልፌ ልሰጥ
ያለምንም ገደብ፣
እና ወሰን በሌለው መተማመን፣
አባቴ ነህና።
አሜን!
ቻርለስ ዴ ፎከልድ

## ብርቱ ጥያቄዎች

ከ1 -10 ስኬል ላይ ራስህን በመለካት እነዚህን ጥያቄዎች መልስ:: ከመልሶችህም የተነሳ፣ ከኢየሱስ ጋር ስላለህ ቅርበት ማድረግ ያለብህን እውነተኛ ግልጽ ውሳኔ የሚገልጽ አጭር አንቀጽ ጻፍ::

1. ለእግዚአብሄር ያለህን ፍቅር እንዴት ትለካለህ?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

2. ለአንተ ያለውን የእግዚአብሄርን ፍቅር እንዴት ትልካዋለህ?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

3. ስላንተ ከሚያውቀው ነገር ሁ፤ ጋርም ቢሆን እግዚአብሔር እስከመን መጠን ነው በትክክል እንደሚወድህ የምታስበው?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

4. አይምሮህ፣ ለብ፣ ህይወትህ እና ግንኙነትህ ምን ያህል ንጹህ ናቸው?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

5. ከእግዚአብሔር እይታ አንጻር ምን ያህል ነጹህ ነህ?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

6. አንተና እግዚአብሄር ያላችሁን ቅርበት ብምን ደረጃ ላይ ነው የምትለካው?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

በህይወቴ ስለ ኢየሱስ ጌትነት እውነተኛ ግልጽ ውሳኔዎች፡

# የወጣት አገልግሎት መርሆች

እርሱን በጥልቀት ለመውደድ ወደሚወስድ ከኢየሱስ ጋር በጣም
ቅርብ የሆነ ህብረትን የምንከተለው እንዴት ነው?

# ግቡ፡ ፍቅር

1 ጢሞ 1፤5ን 3 ጊዜ አንብብ። ማስታወሻ ውሰድ ደግሞም ከዚህ በታች ያሉትን ቃላት ተርጉም። ይህ ጥቅስ ለኢየሱስ የቅርበት መንገድን ለመፍጠር የሚያስፈልግህን ጥልቅ የግል ነገሮችን ይዟል።

> የትእዛዝ ፍጻሜ ግን ከንጹሕ ልብና ከበጎ ሕሊና ግብዝነትም ከሌለበት እምነት የሚወጣ ፍቅር ነው፤
>
> 1 ጢሞ 1:5

ፍቅር ከ . . . ይመጣል

- ከንጹህ ልብ
- ከበጎ ህሊና
- ከእውነተኛ እምነት

# ከኢየሱስ ጋር ወደ ጠለቀ ህብረት

በእነዚህ ጥያቄዎች ራስህን ፈትን ደግሞም ከኢየሱስ ጋር ወደ ቀረበ ግንኙነት መንገድን ለማጥራት በቅዱሳት መጽሀፍት ላይ ሀሳብ ስጥ።

## ንጹህ ልብ

1. ከተቃራኒ ጾታ ጋር የረከሰ ሀሳብ አለኝን? ( 2ጢሞ 2፡22)

2. እቃወማለሁ፣ አንጎራጉራለሁ ወይስ ክረቲካል አመለካከት አለኝ? (ፊሊ. 2፡14-18)

## በጎ ህሊና

3. ወላጆቼንና ቤተሰቤን አከብራለሁ ደግሞም አመሰግናለሁን? (ኤፌ 6፡1-4)

4. መራርነት ወይም ቂም ሌላን ሰው ይቅር ከማለት እየገደበኝ ነውን? (ማቴ 6፡14-15)

5. ሌላ ሰውን በተሳሳተ ሁኔታ ትሪት አድርጌአለሁን? (ማቴ 5፡23-24)

## እውተኛ እምነት

6. እዋሻለሁን፣ እሰርቃለሁን፣ ወይስ አታልላለሁን? (ቆላ 3፡ 9)

7. ኢየሱስ አንደኛ ያልሆነበት የህይወቴ ክፍል አለን? ( ማቴ 6፡33)

# ተግባራዊ እርምጃዎች

- ሀሳብ ለመስጠት 15 ደቂቃ ውሰድ ደግሞም እግዚአብሔር በአንተ የሚደሰትባቸውን ሁሉንም መንገዶች ጻፍ።
- ከባለፈው ገጽ በጣም እየታገልክበት ያለኸውን ነገር ውሰድና የመታዘዝ እርምጃዎችህን ጻፍ። በዚያ ጉዳይ ላይ መታዘዝ ከክርስቶስ ጋር ወዳለው ህብረትህ ጥልቅ ነገር ውስጥ ይወስድሃል።
- በአንድ ጉዳይ ላይ ርምጃ ከወሰድክ በኋላ እግዚአብሔር ምን የመታዘዝ እርምጃዎችን እንድትወስድ እንደሚፈልግ በመጠየቅ ወደ ሌላው ሂድ። እያንዳንዱን የመታዘዝ እርምጃ እስክትወስድ ድረስ ይህንን ሂደት ደጋግም።
- “በጣም የሚጠየቁ ጥያቄዎች” ክፍል ላይ “ወደ ክርስቶስ የጠለቀ ነገር ሂድ” በሚለው ላይ አምስቱን ጥያቄዎችና መልሶች አንብብ። ይቅርታን እንዴት እንደምትቀበልና እንደምትሰጥ፣ የተበላሸ ባህሪን እንዴት እንደምትቀይር፣ ህይወትን ከሚጫኑ የህይወት ችግሮች ጋር እንዴት ዲል እንደምታደርግ፣ እና ኢየሱስን የተሻለ እንዴት እደምታውቅ ትረዳለህ።
- በየለቱ ከእግዚአብሄር ጋር ለብቻህ ጊዜ ማሳለፍህን ቀጥል። በጊዜ ርዝመት ያ ልማድ ክክርስቶስ ጋር ያለህን ህብረት ጥልቅ ያደርገዋል።

---

ስመንፈሳዊ መረዳት ወርቃማው ህግ እውቀት ሳይሆን መታዘዝ ነው። ከመታዘዝ ድርጊት በስተጀርባ የሁሉን ቻይ እግዚአብሔር እውነታ አለ።

ኦስዋልድ ቼምበርስ


# ከክርስቶስ መሳሪያዎች ጋር ወደ ጥልቀት መሄድ




## ኢየሱስ እኩያ የለውም

ቤሪ ሴንት ክሌይር ከእግዚአብሄር ልጅ ወደ ፍቅር መጋጠምይመራሀል:: በእውነት ኢየሱስ ማን እደሆነ ታውቃለህ:: ኢየሱስ እኩያ

በሚለው የመጨረሻውን "የመንገድ ጉዞ" ትወስዳለህ:: ከኢየሱስ ጋር የተሸለ ጓደኛ በመሆን ደስ ትሰኛለህ:: ኢየሱስ እኩያ የለውም በሚለው ጋዜጣ/ ጆርናል፣ የመንገዱ ጉዞ በኢየሱስ ህይወት፣ ሞት፣ ትንሻኤ፣ እርገትና ዳግም መጻት ውስጥ ስትጓዝ ለ40 ቀናት ይቀጥላል:: ስለ ኢየሱስ የምታስበው ነገር ይፈተናል አንተም የሆንከው ነገር ይፈተናል!




## ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜን

ከኢየሱስ ጋር ያለውን ህብረትህን እንዴት ጥልቅ ማድረግ ትችላለህ? ጊዜ! እንደሌሎቹ ግንኙነቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ጊዜ ስታሳልፍ ኢየሱስን በቅርበት ታውቀዋለህ:: ወደ እርሱ ቀርበህ ስትጠጋ ኢየሱስም ወዳንተ መቅረብ ይፈልጋል! የሚከተሉትን ነገሮች ስታደርግ በየለቱ ከእግዚአብሄር ጋር ለብቻህ ጊዜ እንድታሳልፍ ይህ መጽሐፍ ይረዳሀል::

- መጽሐፍ ቅዱስን ስታጠና
- ቅዱሳት መጻህፍትን ስታጠና
- ጸሎትን ስትወድ
- በውዳሴ ስታከብረው
- ምስጋና ስታቀርብ
- ሀጢአቶችህን ስትናዘዝ
- ለራስህ ስትጸልይ
- ለሌሎች ሰዎች ስትጸልይ

## የጉዳዩ ማዕከል




ቡዝ እግዚብሔርን የመከተል የህይወት ዘመን ጥያቄ በዚህ መጽሐፍ እያንዳንዱ ገጽ ይዘላል። ከመሞቱ አራት አመት በፊት በመጻፍ ይህ መጽሐፍ ከ50፣000 ቅጂዎች በላይ ተሸጧል። አሁን በሚስቱ በሎዋና ተሻሽሎ እያንዳንዱ ምዕራፍ ከዚህ በፊት ታትመው በማያውቁ በዴቭ ጥቅሶች ተቀድመዋል። ጥቄዎች እንዲሁም ለጠጨማሪ ጥናት የውይይት ሀሳቦች ለሁሉም ዘመን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እርሱን ዋና በማድረግ እያንዳንዱን ምዕራፍ ይከተላሉ።

ዴቭ ቡስቢ ሚስጥር ነበር። ከሲስቲክ ፋይብሮሲስ፣ ከፖሊዮ፣ ከስኳር፣ ከልብ ህመም እና ከጉበት በሽታ የመጣ የአካል ድካም መካከል ሆኖ የ2 ቆሮ 12፤10፡ "ስደክም ያን ጊዜ ኃይለኛ ነኝና። " ህያው ማረጋገጫ መንፈሳዊ ብርታት ተገኘ። ኢየሱስ ብቸኛው የዴቭ ተስፋ እንደነበር መናገር አባባል ብቻ አልነበረም ነገር ግን የየእለት የሚታይ እውነታም ነበር። የነገሩን ልብ በጣም በእግዚአብሔር አማካኝነት በመረመርክ ጊዜ በእግዚአብሔር ህልውና ተጽኖ ከተደረግህ አትደነቅ።

እነዚህን ማቴርያሎች www.reach-out.org.

## ለሌላ ንባብ ጥቆማ

- የአብ ልጅ በብሬናን ማኒንግ
- እውነታኛ መልክ በቢል ትራል፣ ብሩስ ማክኒከል እና ጆን ሊንክ
- ኢሞሽናሊ ሄልዚ ስፒሪቹዋሊ በፒተር ስካዜሮ
- የተቀደሰ ፍቅር በብሬንት ከርቲስ እና በጆን ኤልድሬጅ

# የስራ እቅድ

አሁን . . . ወደ ክርስቶስ ጥልቅ ነገር ለመሄድ ምን እየደረግህ ነው?

ወደፊት መሄድ . . . ከዚህ ክፍል ጊዜ ግኝቶችህን ውሰድና ልዩ የሆነ የስራ እቅድህን ንደፍ፡፡

ስምንድን ነው ክክርስቶስ ጋር ወደ ጠለቀ ህብረት ለመሄድ ያስፈለግህ?

ምን ግብ ነው የምታስቀምጠው ክክርስቶስ ጋር ወደ ጠለቀ ህብረተ ለመንዝ ?

ማን ነው ክከርስቶስ ጋር ወደ ጠለቀ ህብረት ለመሄድ ተጠያቂ የሚያደርግህ ?

የት ነው ወደ ጠለቀ ህብረት ለመሄድ ከክርስቶስ ጋር የምትገናኘው?

መቼ ነው ወደ ጠለቀ ህብረት ለመሄድ ከክርስቶስ ጋር መቼ ነው ካርቭ አውት የምታደርገው?

ከክርስቶስ የስራ እቅድ ጋር ወደ ጥልቀት መሄድ

# በፍላጎት ጸልይ

## ግቡ

በፍላጎት ለመጸለይ ምቹ ሁኔታን መፍጠር

ክፍለ ጊዜ 3

# ኢየሱስ ላይ ትኩረት ያደረገ

ልጄ “በኢየሱስ እኔ የሰይጣን የግል ቅዠት ነኝ” የሚል ጽሁፍ በላዩ የተጻፈበት ቲሸርት ነበረው። በፍቅር መጸለይ ማለት ወደ ኢየሱስ መቅረብ ደግሞም የሰይጣንን የጨለማ መንግስት ወደ ኋላ ሲገፋ እና በኢየሱስ ብርሀን መንግስት እርሱን ሲተካ መመልከት ማለት ነው። ጸሎትን በፍላጎት ሳንከተል ስንቀር ሰይጣን የእኛ የግል ቅዠታችን ነው። የጨለማ መንግስት በመጥፎ ውጤቱ ብዙ ብዙ ልጆች አሉት። ሰዎችን ከጥልቅ ለማውጣትና እግራቸውን በአለት ላይ ለማቆም፣ ከጨለማ መንግስት እነርሱን አውጥቶ ወደ ብርሀን መንግስት ለማስገባት የፍላጎት ጸሎት ብቻ የእግዚአብሄርን ሀይል ለመልቀቅ ብቸኛ መሳሪያ ነው። ከዚያም የሰይጣን የግል ቅዠት ይሆናሉ!

የዕብራውያን ጸሐፊ የፍላጎት ጸሎት ለግል ህይወታችን፣ ለተማሪዎቻችን እና በዙሪያችን ላሉ ኢየሱስን ለሚሹ በሺህ ለሚቆጠሩ ታዳጊ ወጣቶቻችን ለምን የመጀመሪያው የመከላከያ መስመራችን መሆን እንዳለበት የሚያሳየንን ስእል ፈጥሯል።

> ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል።
>
> ዕብ 7፥25 (አር. ኤስ ቪ)

ኢየሱስ ይችላል! ያንን እውነት አለመረዳት የእኛ የፍላጎት ጸሎት እጥረት እውነታ ነው። የዕብራውያን ጸሐፊ ይህንን ተረድቷል። ወደ ዕብራውያን 1፥2-3 ስንመለስ፣ ኢየሱስ ቻይ እንደሆነ እንረዳለን ምክንያቱም፡

- “የሁሉም ነገር ወራሽ” ነው። ከቢልጌት ይልቅ ከአባቱ የበለጠ ሀብት ወርሷል - ከብዙ ትርፎች ጋር!
- እግዚአብሔር አለምን የሰራው” በእርሱ ነው። ከአንዱ ሚልኪወይ ወደ ሌላው ሚልኪወይ ለመሄድ 100፣000

የብርሀን አመታትን ስለሚወስድ፣ አንድ የብርሀን አመትም ደግሞ 5.88 ትሪሊዮን ማይልስ ስለሆነና አንድ ሚልኪወይ ከብዙዎቹ መካከል አንዱ ጋላክሲ ብቻ ስለሆነ ኢየሱስ ፍጹም ቻይ ፈጣሪ ነው፡፡

- እርሱ "የእግዚአብሄርን ክብር ያንጸባርቃል፡፡" ኢየሱስን መመልከት የእግዚአብሔርን ፎቶ እንደመመልከት ነው፡፡ እግዚአብሔር የሆነው ነገር ሁሉ ኢየሱስም ነው፡፡
- "ሁሉን ነገር በስልጣኑ ቃል ደግፎ ይዟል" በቃል ብቻ በሚልዮን የሚቆጠሩ ህይወት ያላቸው ነገሮች - ከቫይረስ እስከ ዝሆን ድረስ - በትሪሊዮን የሚቆጠሩ ሲስተሞች- ከጋላክሲ እስከ ኢኮሲስተም ተደግፈው ተይዘዋል፡፡
- "የሀጢአት ማንጻትን" አደረገ፡፡ - ከእርሱ ጋር ላለ ህብረትና ለሀጢአታችን ይቅርታ ደሙን በማፍሰስ፣ ለመንጻታችን መንገድን ከፈተ ፡፡
- "ከፍ ብሎ በክብሩ ቀኝ በመቀመጥ" ነግሷል፡፡ ከመስቀሉና ከትንሳኤው በኋላ ፣ ኢየሱስ አሁን በእግዚአብሄር ቀኝ በመላው አጽናፈ አለም ላይ በመግዛት ነግሶአል፡፡
  (ዕብ 7፡25)፡፡

ጸሎት እግዚአብሔር ወደ እርሱ "እንድንቀርብ" የሰጠው የመግባባያ መሳሪያ ነው፡፡ መቅረብ እንችላለን፡፡ (ዕብ 4፡14-16)
በፍላጎት በመጸለይ ወደ እግዚአብሔር በቀረብን መጠን፣ "ዘወትር ለእኛ ሊማልድ እንደሚኖር" እናውቃለን (ዕብ 7፡25)፡፡ ከኢየሱስ ጋር ስንነጋገር ካለበት ስፍራ ከአብ ቀኝ እርሱ ከእኛ ጋር ይነጋገራል፡፡ ሐዋርያው ዮሐንስ ጸሎታችን ለእግዚአብሔር ምን እንደሚመስል አስገራሚ ስእልን ይገልጻል፡፡

> **የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ። መልአኩም ጥናውን ይዞ የመሰዊያውን እሳት ሞላበት ወደ ምድርም ጣለው፤ ነጐድጓድና ድምፅም መብረቅም መናወጥም ሆነ።**
>
> **ራዕይ 8፡4-5**

ከምግብ በፊት ከማመስገን ይልቅ፣ እቅዳችንን ከሰጠነው በኋላ ስብሰባችንን እንዲባርክ እግዚአብሄርን ከመጠየቅ፣ ወይም የተለመደ የመክፈቻ ወይም የመዝጊያ ጸሎትን ከማድረግ ይልቅ - እግዚአብሄር "ወደ እርሱ እንድንቀርብ" ይጠራናል፡፡ ወደ እርሱ ስንቀርብ በጸጋው ዙፋን ምሪትን፣ መረዳትን ፣ አመለካከትን፣ ሀይልን ፣ብርታትን እና ድፍረትን ወይም የሚያስፈልገንን ሌላ ነገር እናገኛለን፡፡

# ብርቱ ጥያቄዎች

ከ1-10 ስኬል ላይ ራስህን በመለካት እነዚህን ጥያቄዎች መልስ። ከመልሶችህም የተነሳ በፍላጎት ስለመጸለይ ማድረግ ያለብህን እውነተኛ፣ ግልጽ ውሳኔ የሚገልጽ አጭር አንቀጽን ጻፍ።

1. ምን ያህል መጸለይ ትወዳለህ?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

2. በየለቱ ከእግዚአብሄር ጋር ለብቻህ ጊዜ ለማሳለፍ ራስህን ያስለመድከው እስከምን ድረስ ነው?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

3. ለተመሪዎችህ ለመጸለይ ከሌሎች የወጣት መሪዎችጋር በየምን ያህል ጊዜው ትገናኛህ?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

4. በአካባቢህ ባለ/ ላለ የትምህርት ቤት ካምፓስ ለመጸለይ ከሌሎች የወጣት መሪዎች በየምን ያህል ጊዜው ትገናኛለህ?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

5. የተማሪዎችህ ምን ያህል ተርሰንት ናቸው በየለቱ ከእግዚብሔር ጋር ጊዜ የሚያሳልፉት?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

6. የተማሪዎችህ ምን ያህል ፐርሰንቱ ናቸው በየሰማንቱ በትንሽ የጸሎት ቡድን ውስጥ የሚሳተፉት?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

በፍላጎት ስለ መጸለይ እውነተኛ፣ ግልጽ ውሳኔዎች፡

# የወጣት አገልግሎት መርሆች

ለጸሎት ያለንን ፍቅር እንዴት መጨመር እንችላለን ሌሎችም በፍቅር እንዲጸልዩ ምን ሁኔታን እንፈጥራለን?

## መጸለይ ትወዳለህን?

መጸለይ ትወዳለህን? ወይስ ተግባር፣ ግዴታ፣ ከእግዚአብሄር የምትፈልገውን የምታገኝበት ብቻ ነውን?

መጸለይ ውደድ። ብዙውን ጊዜ በቀኑ (ዱሪንግ ዘ ደይ) የጸሎት አስፈላጊነት ይሰማህ ችግርንም ለመጸለይ ተጠቀምበት። የእግዚአብሄርን ስጦታ መያዝ እስከሚችል ድረስ ጸሎት ልብን ያሰፋል። ጠይቅ ደግሞም ፈልግ እርሱን ለመቀበልና እርሱንም የራስህ እንደሆነ አድርገህ ለመጠበቅ ልብህም ይተልቃል።

**ማዘር ቴሬዛ**

## ኢየሱስ ጸሎትን ይወድ ነበር!

የኢየሱስን ህይወት በእንቅስቃሴ እንዳለ ከተመለከትን፣ እርሱ ኮከብ ነው ሌሎቹ ደጋፊ ምክንያቶች ናቸው ጸሎትም ከበስተኋላው ያለ ነገር ነው፡፡ እንዴት “የጸሎት እንቅስቃሴን” እንደቀጠለ ለማየት ከዚህ በታች ያሉትን ጥቅሶች ሙሉ ሀሳብ በመስጠት አንብብ፡፡

**በጸሎት ጀመረ::** (ሉቃስ 3:21-22)

**መጸለይ ቀጠለ** (ዮሐ 5:19)

- በየለቱ ጸለየ (ማር 1፧38)
- ከትላልቅ ውሳኔዎችና ክንውኖች በፊት ጸለየ

ሉቃስ 6:12-13 . . . ደቀ መዛሙርቱን ለመጥራት
ሉቃስ 9:16 . . . 5000 በመመገብ
ማቴ 15:36 . . . 4000 በመመገብ
ማቴ 14:22-23 . . . በውሀ ላይ በመራመድ
ዮሐ 11:41-42 . . .አላዛርን በማስነሳት
ማቴ 26:26-29 . . . የመጨረሻው እራት

- መላውን ህይወቱን እና አገልግሎቱን በጸሎ አደረገ (ሉቃስ 5፧16)

**በጸሎት አበቃ** (ሉቃስ 22:39-44፣ 23:46)

**መጸለይ ቀጠለ** (ዕብ 7:25)

---

ጌታ ኢየሱስ አሁንም እየጸለየ ነው። 30 የመኖር አመታት፣ 30 የአገልግሎት አመታት፣ አንድ ታላቅ የሞት ድርጊት። 2000 የጸሎት አመታት። በጸሎት ላይ የተደረገ እንዴት ያለ ትኩረት ነው!

ኤስ. ዲ. ጎርደን

---

ኢየሱስ ከአባቱ ጋር የመነጋገር ፍቅር ነበረው:: ከሰማዩ አባታችን ጋር እንድንነጋገር እኛም ያው አይነት ፍቅር እንዲኖረን ያስፈልጋል::

## የእግዚአብሄርን ሀይል ትለማመዳለህን?

## በብዙ ጥረታችን ውስጥ ሀይል የለም

በሚቀጥሉት ቃላት መሠረት ለማግኘት፣ ለማከናወን እና "እንዲሆን ለማድረግ" ያለህን መሻት ተመልከት፡
"ጸሎት ከፍተኛው በረከታችን እና የላቀው ደስታችን ብቻ ሳይሆን

. . . ስኬት የምናገኝበት ከፍተኛው ውጤታማ መሳሪያችንም ነው:: ሌላው ነገር ሁሉ በግራ መጋባት ውስጥ እንደ እውር ጓደኛ እንጂ ሌላ ነገር ሆኖ በፍጹም በማያውቅ በራስ ጥረት ባዶነት ውስጥ ይተወናል:: ሌላው ነገር ሁሉ ያለ አቅጣጫ፣ ያለ ኮምፓስ፣ ያለ መሪ (ፓይለት) በህይወት ወጀባማ በህሮች ላይ እንደ ደካማ ጩኸት ይተዋናል:: ሁሉንም ነገር በዘላለም እቅዱ በሚያዘው በልኡል አምላክ አቅጣጫ ሳናገኝ ከገነባን፣ ጥረታችን ምንም እንኳን አስደናቂ ቢሆን በስተመጨረሻ ወደ ባዶነት ይመጣል:: "(ኤፍ. ጄ.ሁኤግል" ጸሎት፣ ከፍ ያለው በረከታችን፣" ውሳኔ፣ ሰኔ፣ 1996)

# በእግዚአብሄር ትንሽ ጥረት ብዙ ሀይል

> የ "ሀይል/ ጥረት" መጠንን "ለመረዳት አስቸጋሪ አይደለም:: እግዚአብሄር በኤርምያስ አማካኝነት እንዲህ አለ፡ ወደ እኔ ጩኽ፥ እኔም እመልስልሃለሁ፤ አንተም የማታውቀውን ታላቅና ኃይለኛ ነገርን አሳይሃለሁ።
>
> ኤር 33፡3

ስንጸልይ("ጥራኝ")፣እግዚብሄርተስፋንሰጥቶናል("እመልስልሃለሁ") ስለእኛ ኀይሉን እንደሚልክ ("ደግሞም ታላቅ እና የማታውቀውን የማይመረመሩ ነገሮችን እነግርሃለሁ (አሳይሃለሁ"):: ቻርለስ ስፐርጅን፣ የ19ኛው ክፍለ ዘመን እውቅ መጋቢ፣ ከአገልግሎት በፊት ለቤተ ክርስቲያኑ ብዙ ጊዜ ጉብኝትን ያደርግ ነበር:: ሰዎችን ወደ ታች ወደ መሠረቱ መውሰድ ይወድ ነበር:: "እዚህ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን የሐይል ዘር እንድታዩ እፈልጋለሁ" አለ:: ስፐርጅን በፍጥነት በሩን ሲከፍት፣ ክፍል ሙሉ ወንዶችና ሴቶች በጉልበታቸው ተንበርክክከው በፍቅር እየጸለዩ ነበር::
የወጣቶች አገልግሎት ቡድንህን እንደዛ ሙሉ ክፍል ሰዎች አድርገህ ማሰብ ትችላለህን?

# በፍቅር መጸለይን የምትቀጥለው እንዴት ነው? ከእግዚአብሄር ጋር በየጊዜው ለብቻ በመሆን

ከእግዚአብሄር ጋር በየለቱ ለብቻ ጊዜ መውሰድ ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር ያሳያል ደግሞም ከእርሱ ጋር ያለንን ቅርበት ጥልቅ

ያደርገዋል። ከአብርሀመ እስከ ሙሴ እስከ ሐዋርያው ጳውሎስ እስከ እያንዳንዳችን ድረስ፣ ከእግዚአብሔር ጋር የብቻ ጊዜ የክርስትና ህይወት በጣም አስፈላጊው ብቸኛ ሥርዓት ነው። እግዚአብሄር በእርሱ ላይ እንድንሆን ይፈልጋል!

---

መጽሐፍ ቅዱስ የለም። ቁርስ የለም።

---

## ከሌሎች ጋር በመጸለይ

በሰማይ ያሉ የእግዚአብሄር ምንጮች በሙሉ በዚህ በምድር ላለን ከእርሱ በነጻ ተሰጥተዋል። ጸሎታችን መለቀቃቸውን ወይም አለመለቀቃቸውን ይወስናሉ። ያ ሀይል ነው!

> እውነት እላችኋለሁ፥ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል። ደግሞ እላችኋለሁ፥ ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል። ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና።
>
> ማቴ 18፡18-20

“ሁለት ወይም ሶስት” ሆነን ስንጸለይ ሀይል ይለቀቃል። ኢየሱስ እንድናደርግ እንዳበረታታን ከሌሎች ሁለት ወይም ሶስት ሰዎች ጋር በጸሎት የምንሳተፈው እንዴት ነው?

ከዚህ በታች ያለውን “አረፍተ ነገር” እና የኢየሱስን አባባሎች ተግባራዊ ሀይሎች ለመረዳት ሞክር፡ “ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በተሰበሰቡበት በዚያ እኔ ከእነርሱ ጋር ነኝ።”

# 3

## ክርስቲያኖችን አግኝ
## ክርስቲያን ላልሆኑ ጓደኞች ለመጸለይ ጊዜ በሳምንት ተገናኝ

ከሌሎች ሁለት ወይም ሶስት ጋር መተባበር እንችላለን - ልክ ኢየሱስ እንድናደርግ እንዳበረታታን - በሶስትዮሽ ጸሎት። በተግባራዊ እርምጃዎቹ፣ የሶስትዮሽ ጸሎት ስልትን ታቋቁማለህ።

---

በአንተ አማካኝነት ሰዎችን ለመለወጥ
ጸሎት የኢየሱስን ሀይል ይለቃል!

---

# ተግባራዊ እርምጃዎች

- ዮሐ 5፡19ን በቃልህ አጥና

- ልማድ እስኪሆን ድረስ ቢያንስ 20 ደቂቃ ከእግዚአብሄር ጋር በየቀኑ ለብቻህ ለማሳለፍ ራስህን ስጥ። "ወደ ብስለት ከመሄድ" ሲሪስ ውስጥ "ከእግዚአብሄር ጋር  የብቻ ጊዜ ኖት ቡክ"ን  እንደ መመሪያ ተጠቀም።

- ሌሎች ሁለት የወጣት መሪዎችን ጋብዝ- ከሌላ አብያተ ክርስቲያናት ወይም ቤተ እምነቶች ቢሆንም እንኳን - ከአንተ ጋር በሶስትዮሽ ጸሎት ለመጸለይ። የራስህን ጨምሮ 3 የስብሰባ ጊዜዎችን እና የምትጸልይላቸው 3 የማያምኑ ተማሪዎችን የሚከተለውን ቻርት በመጠቀም ፣ 3 ስሞችን ምረጥ።

**3**

**ክርስቲያኖችን አግኝ**

1______ 2 _______ 3 ______

**ክርስቲያን ላልሆኑ ጓደኞች ለመጸለይ**

1_______ 2_______ 3 _______


**ጊዜ በሳምንት ተገናኝ**

እ ሰ ማ ዕ ሐ አ ቅ

- ከእግዚአብሔር ጋር ለብቻቸው ጊዜ እንዲወስዱ በማስተማር በፍቅር እንዲጸልዩ ተማሪዎችህን አንቀሳቅሳቸው። ከእግዚአብሄር ጋር ለብቻ ጊዜ መውሰድ እና ከእግዚአብሄር ጋር ጊዜ ብቻ ኖትቡክን ከ "ወደ ብስለት መሄድ ሲሪስ" እንደ መመሪያ ተጠቀም።

- በ3ዮሽ ጸሎት እንዲጸልዩ በማስታጠቅ በፍቅር እንዲልዩ ተማሪዎችህን አንቀሳቅስ። እዚህ ላይ የተዘረዘረውንና ስመጸስይ አስደናቂ መንገድ ላይ ከተዘረዘረው የ3ዮሽ ጸሎት ስልትን ተጠቀም።

# በፍላጎት መሳሪያዎች ጸልይ





## ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ ብቻ ኖት ቡክ

ከእግዚአብሄር ጋር ጊዜን ለብቻህ ስታሳልፍ የምታደርገው ምንድን ነው? ማውራትና ማዳመጥ! ለእግዚአብሄር ተናገር እርሱም ለአንተ ይናገር። ለመነሳት፣ በድብርት ወይም ምን እንደ ምታደርግ ለማወቅ እየታገልክ ከሆነ፣ ይህ ኖት ቡክ ላንተ ነው።

- በማለዳ እንድትነሳና ከእግዚአብሄር ጋር እንድትገናኝ ያነቃቃሀል
- ከእግዚአብሄር ጋር ባለህ ጊዜ እንዲመራህ ተግባራዊ መሳሪያዎችን ይሰጥሃል
- በገዛ ራስህ መረዳት መጽሐፍ ቅዱስ ህያው ያደርግሃል
- በቀላል የጸሎት እቅድ ከእግዚአብሔር ጋር እንድትለካካ ያገናኝሀል

# የመጸለይ አስደናቂ መንገድ

ተማሪዎች ህይወትን ለመኖር፣ ጓደኞቻቸውን ለመውደድና በጸሎት ታሪካቸውን ለመንገር ሀይል ያገኛሉ። ይህ የስምንት ሳምንት ትኩረት ህይወታቸውን፣ ካምፓሶቻቸውን ይቀይራል፣ ደግሞም በጸሎት አማካኝነት የተማሪህን አገልግ ሎት ይቀይራል። ባለ 80 ገጽ የተማሪ ጆርናል ነጻና መውረድ የሚችል ነው። የመሪዎች መመሪያ ስምንት የተሟላ የቡድን ክፍለ ጊዜዎች መባዛት ከሚችሉ ሀንድ አውቶ ች፣ ከአስተያየቶችና ከክንውኖች ጋር ይሰጣል። እነዚህን ማቴርያሎች ከደብሊው ደብሊው ደብሊው ሪችአውት. ኦርግ እዘዝ



# የስራ እቅድ

በአሁኑ ጊዜ . . . በፍቅር ለመጸለይ ምን እያደረግህ ነው?

ወደፊት መሄድ . . . በፍቅር ክፍለ ጊዜ ያገኘሃቸውን ግኝቶች ውሰድና ልዩ የሆነ የስራ እቅድህን ንደፍ።

ለምንድን ነው - በፍቅር መጸለይ ላንተና ለሌሎች አገልግሎች አስፈላጊ የሆነው ?

ምን ግብን ነው በአገልግሎህ ለራስህና ለሌሎች በፍቅር ለመጸለይ የምታስቀምጠው?

ማን ነው በሶስትዮሽ ጸሎትህ አብሮህ የሚሆነው ደግሞስ በአገልግሎትህ ሶስትዮሽ ጸሎትን ማን ይጀምራል?

የት ነው ለመጸለይ የሶስትዮሽ ጸሎትህ የሚገኘው?

መቼ ነው - የሶስትዮሽ ጸሎት የሚገናኘው?

# መሪዎችን መገንባት

## ግቡ

ጥልቀት ላላውና ለረጅም ጊዜ አገልግሎት
ብቃት ያላቸውን ነሪዎች መገንባት

ክፍለ ጊዜ 4

# መሪዎችን መገንባት
## ክፍለ ጊዜ 4

## ኢየሱስ ላይ ትኩረት ያደረገ

በአመራር ውስጥ ቀላሉ መንገድ በመንገዱ ላይ የሚደናቀፈውን ማንንም መጠቀም ነው። እሱን ወይም እርሷን የሚመስል ማንንም ሰው ውሰድና ያንን ሰው በመሪነት ቦታ ላይ አስቀምጠው። ይህ ዘዴ ውድቀትን ያመጣል። ከኢየሱስ የአመራር ዘዴ እንዴት የተለየ ነው!

ኢየሱስ አስራ ሁለት ደቀ መዛሙርት አድርጎ የመረጣቸውን ሰዎች ስንመለከት፣ ስኬት የማይኖረው ከላይ ሲታይ እንግዳና አስቂኝ ስብስብ ይመስላል። አማካኙ ሰው ያላየውን የሆነ ነገር ኢየሱስ የተመለከተ መሆን አለበት። ካልሆነ፣ ለሮም የሚሰራ ቀራጭን (ማቴዎስን) ደግሞም የህይወት ተልእኮው ሮምን ማፍረስ የሆነውን ቀናተኛውን ስምኦንን ማን ይመርጠው ነበር?

በእነዚህ በሁለቱ ግኙነቶች የተፈጠረውን ግጭት አስቡ! ተጠራጣሪው ቶማስስ? ወይም ባለ ትልቅ አፍ ፈጣኑ ጴጥሮስስ? ከሀዲው ይሁዳም እዚያ ነበር። ታሪካዊ ማስረጃ አብዛኞቹ ተዳጊ ወጣቶች እንደነበሩ ያስረዳል። ዛሬ የትኛው ቤተ ክርስቲያን ነው በአመራር ውስጠኛ ክፍል የሚፈቅድላቸው? የኢየሱስ አስተሳሰብ ምን ነበር?

በርግጠኝነት መናገር አንችልም። አንድ ነገር ግን ግልጽ ነው። ከዚህ ከተመረጠ በታች ቡድን ጋር የሶስት አመት የአመራር ስልጠናውን ከጨረሰ በኋላ፣ "አለምን ገለበጧት"። እንዲሁ

የሚያደርጉ መሪዎችን ለመገንባት የሚያበረታታንን ከኢየሱስ ምን መማር እንችላለን?

**የተሰበሩ ቁርጥራጮች::** ኢየሱስ ወደ ጠራቸው ወደ እነዚህ አስራ ሁለት ሰዎች ልብ ሲመለከት፣ ትቢትን፣ እብሪትን፣ የራስ ብርታትን ተመለከተ:: ከሶስት አመት በኋላ ግን ወደ ህይወታቸው የተዘጉ ህልሞች እየተመለከቱ "አሁን ሁሉም ነገር አበቃ፣ የሚቀጥለው ነገር ምንድን ነው?" በማለት የጠየቁ የተሰበሩ ሰዎች ነበሩ:: በላይኛው ክፍል ለህይወታቸው ሰግተው ተደብቀው ነበር- ሁነታውን ለመቀየር ምንም ነገር ማድረግ አለመቻላቸውን ሙሉ በሙሉ በማወቅ:: ኢየሱስ እስከራሳቸው ማብቂያ ድረስ ወሰዳቸው:: ያ አመራር " . . . .በሀይልም አይደለም በብርታትም አይደለም በመንፈሴ ነው እንጂ/"(ዘካ 4፡6) መሆኑን እንዲመለከቱ:: ከዚያ በኋላ ነው ኢየሱስ "ሀይልን ትቀበላላችሁ" (ሐዋ ስራ 1፡ 8) ያለው:: ኢየሱስ እንዲሰብረን በመፍቀድ መስቀሉን ስንሸከም ከዚያም እርሱን የሚያንጸባርቁ ሰዎች አድርጎ ሲቀርጸን መሪነት በእኛ ውስጥ ያድጋል:: መሪዎቻችንም መስቀሉን ሲቀበሉ፣ ስብራትን ሲለማመዱና እግዚአብሄር እንዲቀርጻቸው ሲፈቅዱ ያድጋሉ:: በመሪነት ቡድን ውስጥ መሰበርና ቀረጻ እንዲካሄድ ፈቃድ ይሰጣል::

**ምሽቱን ሁሉ ማሳለፍ::** ኢየሱስ አስራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት መምረጥን እንደዋዛ አልወሰደውም:: ሉቃስ "በነዚህም ወራት ይጸልይ ዘንድ ወደ ተራራ ወጣ፥ ሌሊቱንም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ:: " በማለት ይነግረናል፡ (ሉቃስ 6፡12):: ያም በሚቀጥለው ቀን አስራ ሁለቱን ከመምረጡ በፊት ነበር:: የሆነ ሰው እንዲህ አለ፡ "አንድን ሰው ለማባረር ከሁሉም የተሸለው ጊዜ እርሱን ከመቅጠር በፊት ነው::" ያንን ጥቅስ በዚህ አውድ ውስጥ በመከተት፡ "ትክክለኛ ያልሆኑ መሪዎችን ለማስወገድ የተሸለው መንገድ ገና በመጀመሪያው እነርሱን አለመምረጥ ነው:: ትክክለኛ መሪዎች ይሁኑ አይሁኑ የማወቅ ብቸኛ መንገድ ውሳኔውን ወደ እግዚአብሄር ማምጣት ነው፤ ትኩረት ባደረገ ጸሎም እርሱ ይምረጣቸው:: የአመራር ቡድኑ ለትክክለኛ ሰዎች እግዚአብሄርን

በመፈለግ ትክክለኛ አመጣጠን ስኬታማ ይሆናል ከዚያም ከእነርሱ ጋር ምን ማድረግ እንዳለበት ለማወቅ እርሱን መከተል መቀጠል አለበት።

**ራዕይን ማስቀመጥ።** ኢየሱስ አስራ ሁለቱን መረጠ። ነገር ግን እነርሱ መረጡት በሚል ትርጉም። እንዲህ አላቸው፡ “ተከተሉኝ እኔም ሰው አጥማጆች አደርጋችኋለሁ” (ማቴ 4፡19)። አጠቃላይ ቡድኑን በአንድ ጊዜ ሳይሆን  በተናጠል ደግሞም ሁለት ለሁለት እንዳደረገ ልብ በል። ፊት ለፊት ተጋፈጣቸው። በግለሰብ ደረጃ በዚያ ነጥብ ላይ እርሱን በተመለከተ ምርጫ ማድረግ ነበረባቸው። እነርሱን የፈተነበት ፈተና ለእነርሱ ያለውን ራእይ ይዟል። አስቀድሞና አስበልጦ ደቀ መዛሙርቱ “እንዲከተሉት” ፈልጓል። ይህ የመንፈሳዊ አመራር ልብን ይዟል። ሰዎች ወንበርን እንዲሞሉ ማድረግ አይደለም ስለዚህ እነርሱን ለወጣት አገልግቶች ልንጠቀማቸው እንችላለን። ይልቁንም ከክርስቶስ ጋር ባላቸው ህብረት ሰዎችን ማበረታታት፣ ማነጽ እና መንከባከብ ነው። በሚገባ ተማሪዎችን ለመምራት ምን እንደሚያስፈልግ ያ ይሰጣቸዋል።ሁለተኛኛ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ሰዎች አጥማጅ እንደሚሆኑ ተስፋ ገብቷል። “የአሳ ጠባቂዎች” እንዲሆኑ አልጠራቸውም።፡ ለደቀ መዛሙርቱ የኢየሱስ ፊት ለፊ የአመራር ቻሌንጅ ድርጅት ለመገንባት ወይም ቁጥርን ለመጨመር ሳይሆን አለም ለመለወጥ ነበር! ራዕዩ ቀላልና ግልጽ ነበር። የአመራር ቡድናችንን ለተመሳሳይ ራእይ ቻሌንጅ ማድረግ እንችላለን።

**የግንኙነት ህግ።** ኢየሱስ የህብረትን ዋጋ አውቆአል። በመሠረቱ፣ ከአባቱ እና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ፍጹም በሆነ ህብረት ዘላለምን አሳልፏል። ( ያ ፍጹም የሆነ ትንሽ ቡድን ነው!)። ስለዚህ አስራሁለቱን ሰዎች ከአባቱና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተለማመደውን እንዲለማመዱ ጠራቸው። በሚቀጥሉት ሶስት አመታት ቀዳሚ ትኩረቱ በነዚህ ሰዎች ላይ ነበር። ሌሎች ህብረቶች ነበሩትን? በርግጥ። ትላልቅ ቡድኖችን ያነጋገር ነበረን? እንደተነጋገረ እናውቃለን። በያንዳንዱ ቀን መጨረሻ ላይ ግን ከአባቱ ጋር ካለው ህብረት ቀጥሎ ቀዳሚ ትኩረቱ ከአስራ ሁለቱ ጋር ነበር። ወጣት አገልጋዮች ልጆችን ይወዳሉ። ከእነርሱ ጋር ህብረት የማድረግ ችሎታችን ከነርሱ ጋር የምንሰራበት ተቀዳሚ ምክንያታችን ነው። ግን ስንት ጥራት ያለው ግንኙነቶች ሊኖሩን ይችላሉ? በርግጥ

ከ12 ያልበለጠ። የኢየሱስን አገልግሎት ከተመለከትንና የራሳችንን በእርሱ ሞዴል መቀጠል ከፈልግን ደግሞም ወጣቶች በግንኙነቶች እየተለወጡ እንዳሉ ካመንን፣ ልክ ኢየሱስ እንዳደረገው የመሪዎች ቡድንን ማስነሳት አለብን። ከዚያ ተነስተን በምናሰለጥናቸውና በምናስታጥቃቸው ወጣት መሪዎች አማካኝነት አገልግሎታችንን እናስፋፋለን።

**ሚዛን ያለው ድርጊት።** ኢየሱስ የመረጣቸውን ሰዎች መረጣቸው ምንያቱም የተለያዩ እንጂ አንድ አይነት ስላልነበሩ። የስብዕና ልዩነታቸው ለመብረር ብልጭታን አመጣ። ኢየሱስ ግን እንደዛ መሆኑን ወዶታል። ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ስጦታዎች ስላላቸውም መረጣቸው። ኢየሱስ ስብዕናቸውም ስጦታዎቻቸውም በቡድኑ ውስጥ ጤናማ ውጥረትን እዲፈጥር ፈለገ። እነዚህ ሰዎች ከዕርገቱ በኂላ ልትፈነዳ ላለቸው አዲስ፣ ወጣት ቤተ ክርስቲያን ሚዛን ያለው የመንፈሳዊ ስጦዎች ትክክለኛ ውህድ እንዳላቸውም አውቆ ነበር። ለምሳሌ ጴጥሮስ ሐዋርያ ነበር (“በዚህ አለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሰራለሁ፤ ፊልጶስ ወንጌላዊ ነበር። የትኛውም የወጣት መሪ ሁሉም ስጦታዎች የሉትም። ብዙ መሪዎች ለወጣት መሪዎች ሚዛን ያለው ነገር እንዲያደርጉ ይፈለጋል። እነዚህ ስጦታዎች ሲገለጡ ብቻ ነው መሪነት ሚዛን የሚያገኘው። በዚህ ሚዛን የኢየሱስን አገልግሎት ለመፈጸም መንፈሳዊ አቅም ይመጣል።

**ጊዜን ኢንቨስት ማድረግ።** ኢየሱስ አንዴ ደቀ መዛሙርቱን ከመረጠ በኂላ ከነርሱ ጋር የበለጠ ጊዜን ያሳልፍ ነበር። ኢየሱስ ከደቀመዛርቱ ጋር ያሳለፈውን ጊዜ እና ከህዝቡ ጋር ያሳለፈውን ጊዜ የሚያናጻጽር የሶስት አመት ግራፍ ቻርትን ብንሰራ የደቀመዛሙርቱ መስመር ወደ ላይ ይወጣል የህዝቡ መስመር ደግሞ ወደታች ይወርዳል። ብዙ ጊዜውን ከህዝቡ ጋር በማሳለፍ ጀመረ። ጊዜ በገፋ መጠን ግን የበለጠ ጊዜ ያጠፋ የነበረው ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ነበር። በምድር አገልግሎቱ መጨረሻ ላይ ከሞለ ጎደል ጊዜውን ሁሉ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አደረገ። ትላልቅ የቡድን ክንውኖችና ድርጊቶች የበለጡ የወጣት አገልግቶችን ይመራሉ። ልክ ኢየሱስ እንዳደረገው መሪዎችን ለማፍራት፣ ያ መለወጥ አለበት። በተማሪዎች ላይ ኢንቨስት የሚያደርጉ መሪዎችን ለማፍራት የበለጠ ጊዜ ማጥፋት አለብን።አገልግሎቱ ጥልቀትና እድገት እንዲኖረው መንገዱ ይሄ ብቻ ነው።

**እድገትን ማብዛት::** ኢየሱስ በደቀ መዛሙርቱ ላይ ጊዜውን ሲያጠፋ፣ በሃሳቡ ውስጥ የነበረው ታስቁ ተልዕኮ ነው።

> ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፦ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።
>
> ማቴ 28፡18-20

ይህ የማቴዎስ ትርጉም ነው:: ሁሉም ወንጌሎች እንዲሁም የሐዋርያት መጽሐፍም መዝግበውታል:: በሌሎች ወንጌሎች - በማር 16፡15-16፣ በሉቃስ 24፡47-49፣ በዮሐ 20፡21-22 ም ውስጥ ልታገኘው ትችላለህ:: ከኢየሱስ ስልጣን በታች ሲሄዱ፣ የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ደቀ መዝሙር ሊያደርጉ ነበር:: እነዚህ ደቀ መዛሙርት ሌሎች ደቀ መዛሙርትን እንዲያፈሩ ነበር:: ቤተ ክርስቲያን “ሁሉንም ህዝብ ደቀ መዛሙርት” እስከምታደርግ ድረስ ይቀጥላል::

በሁሉም ገንዘብ፣ ቴክሎጂ፣ ሥነ ጽሑፍ እና ባሉት የቴሌቪዥን ሰባኪዎች አሁን ያንን ስራ ጨርሰን መሆን ነበረብን:: ነገር ግን አልጨረስንም:: ለምን? ደቀ መዝሙር በማድረግ መሪዎችን

የማፍራትን የኢየሱስ ትእዛዝ መረዳት ስለሌለን:: ደቀ መዛሙርትን ከማብዛት ይልቅ የቤተ ክርስቲያንን አባላት እየጨመርን ነው:: በነዚህ ሁለት ዘዴዎች መካከል ያለውን ፈጣን ልዩነት እንድናይ ይህ ቻርት ይረዳናል::

| አመት | አባላት<br>አባላት ይደመራሉ | ደቀ መዛሙርት<br>ደቀ መዛሙርት ይባዛሉ |
|---|---|---|
| 1ኛ | 1 | 1 |
| 2ኛ | 2 | 2 |
| 3ኛ | 4 | 6 |
| 4ኛ | 8 | 18 |
| 5ኛ | 16 | 54 |
| 6ኛ | 32 | 162 |
| 7ኛ | 64 | 1458 |
| 21ኛ | 1048፣ 576 | 7,016,615,523 |

በ “አባላት” መደዳ አንድ አባል በአንድ አመት አንድን ሰው ቢጨምር ፣ በ21 አመታት ውስጥ 1048፣ 576 አዳዲስ አባላት ይኖሩ ነበር:: በሌላ በኩል፣ የ “ደቀ መዛሙርት” መደዳ አንድ ሰው አንድን ሌላ ሰው ደቀ መዝሙር ቢያደርግ፣ ከዚያ እነዚህ ሁለቱ በሚቀጥለው አመት ሁለት ሌሎችን ደቀ መዝሙር ያደርጋሉ ከዚያም እነዚህ ስድስቱ ሁለት በሚቀጥለው አመት ሁለት ሌሎችን ያደርጋሉ፤ እንዲህ እያለ ይቀጥላል:: በማባዛት ሂደት በ21 አመታት ውስጥ ከ7 ቢልዮን በላይ ይደርሳል - ከ6.8 ቢልዮን ከአለም ህዝብ ቁጥር በላይ:: ሁሉም የተጀመረው በአንድ የኢየሱስ ተከታይ ነው!

በአመራር ቡድንህ አማካኝነት ልክ እንደዛ ከአራት እስከ አስራሁለት ደቀ መዛሙርት አድርገህ ቢሆን ኖሮ ምን ይሆን ነበር?

ኢየሱስ ታላቁን ትእዛዝ (“እግዚአብሔርን ውደድ”) እና ታላቁን ተልዕኮ (“ሁሉንም ህዝብ ደቀ መዝሙር አድርጉ”) ለማሳካት የላቀው ዘዴ መሪዎችን ማፍራት እንደሆነ ያውቃል:: በሚገርምም ሁኔታ ይህንኑ እንድናደርግ ዕድልን ሰጥቶናል::

# ብርቱ ጥያቄዎች

ከ1-10 ስኬል ላይ ራስህን በመለካት እነዚህን ጥያቄዎች መልስ:: ከመልሶችህም የተነሳ የግልህን የአገልግሎት የአመራር አስፈልጎቶች በመግለጽ አጭር አንቀጽ ጻፍ::

1. በበጎ ፈቃደኞችህ፣ በወላጆችና በተማሪዎችህ ላይ ምን ያህል የተጽኖ ደረጃ አለህ?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

2. በበጎ ፈቃደኞችህለመሰልጠን ፈቃደኞች የሚሆኑት እስከም ደረጃ ድረስ ነው?
3. 
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

4. በጎ ፈቃደኞችህን ለማሰልጠን ፈቃደኛነትህ እስከም ድረስ ነው?
5. 
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10
6. ባጠቃላይ በበጎ ፈቃደኞችህ ያላቸው መንፈሳዊ ጥልቀት ምን ያህል ነው?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

7. በጎ ፈቃደኞችህ እርስበርስ ያላቸው ህብረት ጥልቀቱ ም ያህል ነው?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10
8. በጎ ፈቃደኞችህ ከልጆች ጋር ባላቸው ህብረት ደስ የሚሰኙበት የተሳትፎ መጠን ምንያህል ነው?

   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

የግሌና የአገልግሎቴ የአመራር አስፈልጎት :

# የወጣት አገልግሎት መርሆች

ጥልቀት ላለውና ለረጅም ጊዜ አገልግሎት ጥራት ያላቸውን መሪዎች ማፍራት የምንችለው እንዴት ነው?

## የአመራር ቡድን አላማ

በዮሀ 17:20-26 ኢየሱስ ስለ ደቀመዛሙርቱ ወደ አባቱ እነዚህን ልመናዎች ይጠይቃል። ኢየሱስ በነዚህ ጥቅሶች ውስጥ የተጠቀማቸውን ሐረጎች ከዚህ በታች ካሉት ከሶስት ሐረጎች ጋር አዛምድ።

- ለክርስቶ መሠጠት
- ለእርስ በርስ መሰጠት
- አለምን ለማገልገል መሰጠት

ከላይ ኢየሱስ ከተናገረው፣ የአመራር ቡድንህን አላማ እንዴት ተገልጻዋለህ?

---

መሪነት ተፅኖ ማድረግ ነው!

መሪ፡

- የት እንደሚሄድ ያውቃል
- የሚከተል ህዝብ አለው

---

# የአመራር ቡድን ግስጋሴ

የኢየሱስን የሶስት አመት የአገልግሎ ጊዜ ስንመለከት፣ብዘዉን ጊዜ ደረጃዎቹን በማጠላለፍና በማደራረብ፣ በአራት ደረጃዎች ውስጥ በማሳለፍ ኢየሱስ በሂደት ደቀ መዛሙርቱን እንዳፈራ እንረዳለን። ይሁን እንጂ ሁሉም ደረጃዎች የጋራ የሆነ አስደናቂ ነገሮች አሏቸው። ልታገኘው ትችል እንደሆነ በመመልከት በዚህና በሚቀጥለው ክፍል ውስጥ ያሉትን እያንዳንዱን ጥቅሶች መርምር።

የኢየሱስ አራት የአመራር ዕድገት ደረጃዎቸ

1. አደርገዋለሁ (ሉቃስ 4:31-37 እና 38-44)

2. አደርገዋለሁ እነርሱም ከእኔ ጋር ናቸው (ሉቃስ 5:1-11)

3. ያደርጉታል እኔም ከነርሱ ጋር ነኝ (ሉቃስ 10:1-17)

4. ያደርጉታል እኔም ለማበረታታት ከበስተኋላ ነኝ (ሉቃስ 24:44-49 እና ሐዋ ሥራ ባጣቃላይ)

# የ "ነገሩ" ሀይል

ከባለፈው ገጽ "ነገሩ" የሚለውን ቃል በማየት በሚቀጥሉት ክፍች በትንቢ ወደ ተነገረው ኢየሱስ፣ ስጋና ደም ወደ ሆነው ኢየሱስ፣ ደቀ መዘዝር ወደ ሚያደርገው ኢየሱስ እና መንፈስ ቅዱን ወደ ሚሰጠው ኢየሱስ ስንሄድ መርምርን "ነገሩን" እወቅ።

ኢየሱስ (ነገሩን) ሊያደርገው ይመጣል (ኢሳ 61፥1-3)
የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥
ለድሆች የምሥራችን እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶኛልና፤
ልባቸው የተሰበረውን እጠግን ዘንድ፥
ለተማረኩትም ነጻነትን ለታሰሩትም መፈታትን እናገር ዘንድ ልኮኛል።
የተወደደችውን የእግዚአብሔርን ዓመት አምላካችንም የሚበቀልበትን ቀን እናገር ዘንድ፥
የሚያለቅሱትንም ሁሉ አጽናና ዘንድ፤
እግዚአብሔር ለክብሩ የተከላቸው የጽድቅ ዛፎች እንዲባሉ
ለጽዮን አልቃሾች አደርግላቸው ዘንድ፥
በአመድ ፋንታ አክሊልን፥ በልቅሶም ፋንታ የደስታን ዘይት፥
በኀዘንም መንፈስ ፋንታ የምስጋናን መጐናጸፊያ እሰጣቸው ዘንድ ልኮኛል።

## እንደ መሲህ ኢየሱስ መጣ ደግም "ነገሩን" አደረገው (ሉቃስ 4፥18-19)

የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥
ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፤
ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፥
የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ
የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ

## ደቀ መዛሙርቱ "ነገሩን" አደረጉት (ማር 6፥12-13)

ወጥተውም ንስሐ እንዲገቡ ሰበኩ፥ ብዙ አጋንንትንም

አወጡ፥ ብዙ ድውዮችንም ዘይት እየቀቡ ፈወሱአቸው።

# አሁን “ነገሩን” እናደርገዋለን (ዮሐ 14፡12)

እውነት እውነት እላችኊለሁ፥ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል፥

## “ነገሩ” ምንድን ነው?

ኢየሱስ እርሱ ያደረገውን ነገር እኛ እንደምናደርግ ተናገረ። ኢየሱስ ሲያደርገው የነበረው ነገር ምንድን ነው ?

“ነገሩ” የኢየሱስ አገልግሎት፡-

- የምስራቹን ዜና የሚሰብክ
- በሽተኞችንና ልባቸው የተሰበረውን የሚፈውስና የሚጠግን
- በዲያብሎስ የታሰሩትን የሚፈታ
  ነው።

---

ኢየሱስን ከማወቅ ቀጥሎ፣ የወጣት መሪዎች ያላቸው ትልቁ በረከት የኢየሱስን አገልግሎት ለተራ፣ ለተጎዱ እና ተስፋ ለቆረጡ ወጣቶች ማምጣት ነው።

---

# ተግባራዊ እርምጃዎች

ወደ ኢየሱስ በመቅረብ፣ አብሮ በመጸለይ በተማሪዎች ላይ ህይወታቸውን ኢንቨስት በማድረግ የሚያድግ የአመራር ቡድንን አስብ። ከዚያ በላይ አንድ ርምጃ ሂድ። ይህ የአመራር ቡድን “ነገሩን” ለማድረግ እንደሰለጠነ አስብ። የምስራቹን ዜና መስበክ፣ የተሰበሩ ልቦችን መጠገን፣ እና የታሰሩትን ነጻ ማውጣት ይችላሉ። ዋው! እነዚህን ተግባራዊ ርምጃዎች እንዲሁ ስታደርግ ይህ ራዕይ እውን ይሆናል።

1. **ጸልይ**
   በአመራር ቡድንህ እንዲሳተፍ እግዚአብሄር ስለሚጠራው ሰው ለመጸለይ ትኩረት ያደረገ ጊዜን ውሰድ

1. **ምራ**
   ብዙ ስራዎች ሊሠጡ ይችላሉ ነገር ግን የአመራር ቡድንን መምራት ከእነዚህ አንዱም አይደለም። በመጀመሪያ የወጣቶች መሪ የአመራር ቡድኑን ምምራት አለበት። አንድ ጊዜ መሪዎቹ ከሰለጠኑ፣ ሌሎች የአመራር ቡድኖችን ማሰልጠን መቻል ብቻ ሳይሆን ለመሪነት ተማሪ ደቀ መዛርትንም ማሰልጠንና ማብዛትም ይችላሉ።

1. **ምረጥ**
   የአመራር ቡድንህን ከብዙ ህዝቦች መካከል- አሁን ካሉ የወጣት ሰራተኞች፣ የታዳጊ ወጣት ወላጆችን፣ የኮሌጅ ተማሪዎችን እና ተማሪዎችን የሚወዱ እና ከነርሱ ጋር ለመስራት የእግዚአብሔርን ጥሪ የሚረዱትን ሌሎችን መምረጥ ትችላለህ። ለአመራር ቡድኑ ለእያንዳንዳቸው የግል ፈተና ስጣቸው ።

1. **ተሰጥ**
   የግል ፈተናውን ስታቀርብ፣ በጽሁፍ ለወጣቶች አግልግሎት አስገዳጅ ራእይህን ግለጽ። ለአመራር ቡድኑ የሚኖረውን መሰጠት ተርጉም ደግሞም ግለጽ። ከመጀመሪያ መጠበቅ ያለባቸውን ማወቅ ይፈልጋሉ። (ገጽ 4 ላይ ከኢየሱስ ክርስቶ ጋር የግል አካሄድን ተመልከተ)።

## 2. ተዘጋጅ

መሪዎችን በማፍራት ሲሪስ አማካኝነት የአመራር ቡድንህን ውሰድ። ለእያንዳንዱ ሰው አንድ ቅጂ እዘዝ። ከእያንዳንዱ ስብሰባ በፊት በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ሂድ። ከዚያም መሪዎችን በማፍራት ሲሪስ ውስጥ በሚገኘው በእያንዳንዱ መጽሐፍ “የውይይት መመሪያው” የሚለውን ክፍል በማንበብ በጸሎት ስብሰባዎችን አዘጋጅ። የግል ዝግጅትህ ልዩነትን ያመጣል።

## 3. ተገናኝ

ለአብዛኛው ህዝብ ይበልጥ ምቹ የሚሆነውን ጊዜ እወቅ። ከተቻለ በአንድ ሰው ቤት ውስጥ ተሰብሰቡ። በቋሚነት ለ1 ½ ሰኣታት ተሰብሰቡ። 15 ዲቂቃ ለጸሎት፣ 45 ደቂቃ ለውይይት፣ እና 15 ደቂቃ ስለ ወጣት አገልግሎት ጉዳዮች ለማውራት ውሰዱ።


## 4. ኢንቨስት አድርግ

በየሳምንቱ  በነዚህ ሰዎች ላይ ራስህን ኢነቨስት ማድረግ ኢየሱስን፣ የሰጣቸውን ስጦዎች እና በተማሪዎች ህይወት ላይ እነዚህን ስጦዎች እንዴት ኢነቨስት ማድረግ እንዳባቸው እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል።

## 5. ለካ

ከእንዳንዱ ቡድን ስብሰባ በኋላ ያደረከውን ገምግም ደግሞም ማሻሻል እንደምትችል እወቅ። ችግሮችን ፍታ ደግሞም ማስተካከያዎችን አድርግ።

# ለበጎ ፈቃደኞች መሪዎችን የመገንባት መሳሪያዎች መሪዎችን የመገንባት ሲሪስ




መሪዎችን የመግባት ሲሪስ
በጎ ፈቃደኛ መሪዎችን
ለማሰልጠን መጽሀፍ
ቅዱሳዊ፣ተግባራዊ እቅድን ይሰጣል::
ማነቃቃትን፣ ራዕን እና
ግንኙነቶችን ከሌሎች ጋር
እንዲገነቡ ጥበብን ያገኛሉ፤
የሚያምኑት ተማሪዎችን ደቀ
መዝሙር ያደርጋሉ- እንዲሁም
ለማያምኑ ተማሪዎች ክርስቶስን
ይነግራሉ:: ይህ ለአጠቃቀም ቀላል፣
ኢንተርአክቲቭ፣ እያንዳንዱ
መጽሐፍ 12 ክፍለ ጊዜዎችን የያዘ
የ3 መጽሐፍ ስብስብን ይዟል ደግሞም ለቤተ ክርስቲያንህ የጊዜ መቁጠሪያ በቀላሉ አዳፕት መደረግ ይችላል::

ከክርስቶስ ጋር የግል አካሄድ
(መጽሐፍ 1) ከኢየሱስ ጋር መሪዎች በቅርበት እንዲያድጉ ይመራል

የህይወትና የአገልግሎት ራዕይ (መጽሐፍ 2)
የመሪዎችህን ራዕይ ለህይወታቸውና ለአገልግሎታቸው ያሰፋል

ተማሪዎችን ስመምራት ጠቃሚ መሳሪያዎች (መጽሐፍ 3) በተማሪዎቹ ላይ ውጤት ያለው ተጽኖ እንዲያመጡ ለመሪዎች የሚያስፈልገውን ክህሎት ይሰጣል::
መሪዎችን የመግንባት ሲሪስ (የ3 መጽሐፍ ስብስብ) ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የግል አካሄድ (መጽሐፍ 1)፣ ለህይወትና ለአገልግሎት ራዕይ (መጽሐፍ 2) እና ተማሪዎችን ስመምራት ጠቃሚ መሳሪያዎችን (መጽሐፍ 3) ን ያጠቃልላል::

የኦድዮ ስብስብ - በቤሪ ሴንት ክሌይር፣ ዴቭ ቡስቢ የተዘጋጁ 6 በነጻ የሚወርዱ መልእክቶችን ይዟል::

እነዚህን ማቴርያሎች ከደብሊው ደብሊው ደብሊው ሪችአውት. ኦርግ እዘዝ

# ለወላጆች የመሪዎች መሳሪያዎችን መገንባት

## የወላጅ ነዳጅ




ይህ መጽሐፍ # 1 የአለም መሪዎችን - ወላጆችን ያሰለጥናል! ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር ግንኙነት እንዴት እንደሚያደርጉ ያውቃሉ - ልብ ለልብ:: በዚህ መጽሐፍ ባለፉ መጠን ልጆቻቸውን እንዲሁ እንዲያደርጉ በመምራት እግዚብሔርን በሙሉ ልባቸው ይበልጥ መውደድ ይችላሉ ደግሞም ልጆቻቸውንና የልጆቻቸውን ጓደኞች በመንፈሳዊ ነገር ነገር ኢንቨስት እንዴት እንደሚያደርጉ ወላጆች ያውቃሉ፡

## የወላጅ የነዳጅ ሳጥን




የወላጅ የነዳጅ ሳጥን ወላጆችን ለማሰልጠን ለአብያተ ክርስቲያናት ቀላል፣ ተግባራዊ እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሳሪያን ይሰጣል:: የማቴርያሎቹ የተሟላ ስብስብ

- በወላጅ ነዳጅ አማካኝነት የወላጆችን ቡድን ለመምራት
- ቀላል ያደርጋል:: ይህ በጣም ግሩም የሆነ ካሪኩለም የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡
- አንድ መጽሐፍ አዲስ አመለካከትን የሚሰጥ ደግሞም ልጆቻቸውን ከእግዚአብሔር ጋር ለማገናኘት ወላጆችን የሚመራ
- አንድ ጆርናል በመጽሐፉ ያገኙትን ጥቅም ላይ እንዲያውሉ ወላጆችን የሚረዳ
- ኦዲዮ ሲዲዎች ከአነቃቂና ህይወት ካላቸው ፕረዘንቴሽኖች ዲቪዲዎች ችግራቸውንና ስኬቶቻቸውን ከሚገልጽ ከተለያዩ ወላጆች በሀይል ኢንተርአክቲቭ የሆኑ 6፣ የ55 ደቂቃዎች ክፍለ ጊዜአት የመሪዎች መመሪያ ለመጀመሪያና ትንሽ ቡድንን ለመምራት




## የወላጅ ፓክ

የፓረንት ፊዩል የፓረንት ፓክ የፓረንቶችን ፊዩል በቤተሰብ ላይ ተጽኖ እንዲያደርጉ ወላጆች የሚያስፈልጋቸውን 3 ማቴርያሎች (መጽሐፉን፣ሲዲዎቹንና ጆርናሉን) ያቀርባል። እነዚህን ማቴርያሎች ከደብሊው ደብሊው ደብሊው ሪችአውት.ኦርግ እዘዝ

# የስራ እቅድ

በአሁኑ ገዜ . . . መሪዎችን ለመግንባት ምን እደረግህ ነው?

ወደ ፊት መሄድ . . . ከዚህ ክፍለ ጊዜ ግኝትህን ውሰድና ልዩ የሆነ የስራ እቅድህን ዲዛይን አድርግ::

ስምንድን ነው መሪዎችን መገንባት አስፈላጊ የሆነው ?

ምን ግብ ነው  መሪዎችን ለማብቃት የምታስቀምጠው ?

እነማን ናቸው  የምታፈራቸው መሪዎች ?

የት ነው ከአመራር ቡድን ጋር ለመሰብሰብ የምትገናኘው?

መቼ ነው - ከአመራር ቡድን ጋር ለመሰብስብ የምትጀምረውና የምትቀጥለው ?

# ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር ማድረግ

## ግቡ

የህይወት ለውጥ የተለማመዱትን ተማሪዎች ህይወት ለዋጭ እንዲሆኑ ደቀ መዝሙር ማድረግ

ክፍለ ጊዜ 5

# ተማሪዎች ደቀ መዝሙር ማድረግ

ክፍል ጊዜ 5

## ኢየሱስ ላይ ትኩረት ያደረገ

በአጠቃላይ በታሪክ ውስጥ፣ እግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ ስራውን የሰራው በብዙ ነገር ሳይሆን በጥቂት ነገር ነው:: በጥቂት አመታት በደቀ መዛሙርት ትንሽ ቡድን ላይ የኢየሱስ ኢንቨስትመንት “አለምን ገለባበጠ” (ሐዋ ሥራ 17፡6):: በደቀ መዛሙርቱ ህይወት ላይ በኢየሱስ ተሳትፎ ላይ የተነጣጠረ እይታ ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር በማድረግ የላቀ አስፈላጊ ስራ ላይ እንዴት ማድረግ እንዳለብን የጠራ እይታን ይሰጠናል::

መምረጥ:: ደቀ መዝሙር የማድረግ ሂደት ደቀ መዛሙርቱን በመምረጥ በኢየሱስ ነው የተጀመረው:: በሉቃስ 6፡12-19 ኢየሱስ “ወደ እግዚአብሄር ለመጸለይ ሌሊቱን በሙሉ እንደሳለፈ” እናያለን (6፡12):: በሚቀጥለው ቀን ደቀ መዛሙርቱን ወደ እርሱ ጠራቸው” (6፡13):: ወደ እርሱ ቀርበው እንዲከተሉት የእርሱ የቅርብ ጓደኞች እንዲሆኑ ፈተናንም እድልንም ሰጣቸው:: “ሐዋርያት” ብሎ ጠራቸው (6፡13):: ከጅምሩ መልእክተኞቹ እንደሚሆኑ ግልጽ አድርጎ ነበር:: አስራ ሁለት ብቻ መረጠ ደግሞም እንዴት የተለዩና የተለያዩ ሰብስብ ነበሩ:: እርሱን መከተል አለምን እንዲለውጡ ያዘጋጃቸዋል በሚል እምነት ኢየሱስ የአገልግሎቱን አጠቃላይ (ፊዩቸር) ወደ ፊት በጣም ተራ በሆኑ አስራሁለት ግለሰቦች እጅ ላይ አደረገው:: እንደወረዱ ሳይበስሉና ሳይሰለጥኑ - ከአንተ ጋር እንዲሆኑ እነርሱን በመምረጥ የተማሪዎችን ቡድን መውሰድ እነርሱን መለወጥ ብቻ ሳይሆን ከጊዜ ብዛት አለምን ለመለወጥ የድርሻቸውን እንዲወጡም ያደርጋቸዋል::

መተባበር:: ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር አብሮ በመሆን የተመረጡ ደቀ መዛሙርቱን ደቀ መዝሙር ማድረግ ቀጠለ:: ስልጠና የተገኘው

ኮንፍራንሶችን በመካፈልና በትምህርት ቤት በመመዝገብ አይደለም:: ይልቁን፣ ኢየሱስ አብሮአቸው በመሆን ደቀ መዛሙርቱን አሰለጠነ (ማር 3:14):: ካሪኩለሙ ከእነርሱ ጋር በቅርበትና በቋሚነት አብሮ በመሆን፣ በኢየሱስ ህልውና (አብሮነት) ጊዜን ይዟል:: ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን "ወደ እኔ ኑ" "ከእኔም ተማሩ" አላቸው (ማቴ 11:28-30):: እነርሱም እንደዛ አደረጉ:: ያዩት ነገር አስገርሟቸው ነበር -ውሀ ወደ ወይን ጠጅ ተለውጧል፤ 5000 ሰዎች ጠግበዋል፤ የተቆጣው ወጀብ ጸጥ ብሏል:: ከኢየሱስ ጋር ትከሻ ለትከሻ በመነካካት እምነትን በስራ ተመልክተዋል:: ከእርሱ ጋር አብሮ በመሆን በእግዚአብሄር ላይ መታመንን ተምረዋል:: ካንተ ጋር ህብረት በማድረግ የተመረጠ የተማሪዎች ቡድን እምነትህን በስራ ሲመለከቱ በእግዚአብሔር መታመንን ይማራሉ::

መቀደስ:: ብዙ ሰዎች ኢየሱስን ተከትለውታል:: (ሉቃስ 14:25):: ተአምራትን ማየት፣ የኢየሱስ ዝና ሲወጣ መመልከትና በስኬቱ መደሰትን ይወዱ ነበር:: ነገር ግን ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በመለየት ደረጃውን ፈጥኖ አጠበበው:: በሉቃስ 14:25-34 ተራውን ተመልካች ከታመኑት ደቀ መዛሙርቱ ሲለይ እንመለከታለን:: ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ከሌሎች ግንኙነቶች በላይ እርሱን እንዲያስበልጡ (14፤26)፣ ከራሳቸው ፍላጎቶች በላይ ለእርሱ ዋጋ እንዲሰጡ (14:27)፣ ደግሞም ወደ መከራና እርሱን ለመከተል ወደ ግል መስዋእትነት እንዲገቡ (14:27) ተፈታተናቸው:: ዋጋቸውን በማወራረድ ነገር ላይ እንዲያንጸባርቁ እድል የሰጣቸውን ታሪክ ነገራቸው:: "እንግዲህ እንደዚሁ ማንም ከእናንተ ያለውን ሁሉ የማይተው ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም::" (14:33) በማለት አጠቃለለ:: ብዙዎቹ ተለዩት:: አስራ ሁለት ቀሩ:: ይህ የመለየት ባህሪ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ጣዕም በሌለው አለም ውስጥ የተለየ ጣዕም "ጨው" እንዲሆኑ አደረጋቸው (14:34)::

ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር ማድረግ ማለት ኢየሱስን ክግንኙነቶች፣ ከትምህርት ቤት ክንውኖች፣ መሻቶች፣ ክህይወት ከራሱ በላይ እንዲያደርጉ እነርሱን መምራት ማለት ነው:: ከዚያ በኋላ ተማሪዎቻችንን በአኗኗርና በአነጋገር ዘይቤአቸው ራሳቸውን ይለያሉ:: ሌሎች ተማሪዎች ጨውን ለመቅመስ ይፈልጋሉ::
ማስተላለፍ:: ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ባለው አብሮነት፣ ህይወትን ለእነርሱ እያካፈለ ነበር:: ያንን በሁሉም የህይወት

አቅጣጫ ላይ አደረገ:: "ዛሬ ስለ ጸሎት እየተማርን ነው" ብሎ በማስታወቅ ኢየሱስ የማይጨበጥ ትምህርት ወይም የክፍል ስራ ሰጥቶ አያውቅም:: ይልቁን ኢየሱስ ሲጸልይ በማየት ደቀመዛሙርቱ በጣም ተነሳስተው ነበር ስለ ጸሎት እንዲያስተምራቸው በመጠየቅ (ሉቃስ 11:1-4):: የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ያለማቋረጥ ከኢየሱስ ይቀበሉ ነበር:: አመለካከትን፣ እውቀትን፣ ማስተዋልን፣ እይታና እውነታን፣ ህይወትን ለላመጥቀስ- ህይወትን በእርሱ አገኙ (ዮሐ 1:4፣6:35):: ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር ማድረግ ህይወትን ስንኖር ሲያዩን - መልካሙን፣ ክፉውን፣ አስቀያሚውን የእውነታን መአዛ ይፈልጋል:: ኢየሱስ በእኛ አማካኝነት ራሱን ሲገልጥ ያያሉ::

ፍቅር:: ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ካለው ግንኙነት መውደድን ሰርዝ፣ ከሁሉም የበለጠው አስፈላጊነት ይጠፋል:: ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ወደዳቸው:: "ስለእርሱ መናገር ብቻ ሳይሆን ባልተለመደ መንገድም ገለጠው:: ዮሐንስ ከኢየሱስ ጋር በነበረው ህይወቱ ትልቁን ቀውስ አስታወሰ፣ ያስታወሰው ነገር ምንድን ነው? ኢየሱስ "የፍቅሩን ሙሉ መጠን እንዴት እንዳሳያቸው" (ዮሐ 13:1):: የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት የመለያ ምልክት ፍቅር ነው - ፍቅር ለኢየሱስና ፍቅር ለእርስ በርስ:: እንዴት ነበር ኢየሱስ ፍቅሩን የገለጠው? በዮሐ 13 ውስጥ እግራቸውን የማጠብን ዝቅተኛ ስራ በማድረግ:: የአገልጋይነት ፍቅር ድርጊት ነበር:: ደቀ መዝሙር የምታደርጋቸው ተማሪዎች ኢየሱስን እንዴት ያውቃሉ? በምታሳያቸው ፍቅር:: ያ ፍቅር የእውነት እንደሆነ እንዴት ያውቃሉ? እነርሱን በምታገለግልበት መንገድ::

ልዑክ:: ኢየሱስ ሁሉንም ስራ ለብቻው ለመስራት የሚያስፈልገው ነገር በርግጥ ነበረው:: ነገር ግን ያንን ስራ ለደቀ መዛሙርቱ ሲሰጥ እናያለን (ማቴ 10):: ከሞቱ በኋላ እንዲቀጥሉ ኢየሱስ እነርሱን በመላክ ደቀ መዛሙርቱን እያሰለጠነ ነበር:: እየሄደ ነበር:: እነርሱ እየቆዩ ነበር:: ማወቅ ያለባቸውን ነገሮች አስተማራቸው:: እነዛን ነገሮች ፊት ለፊታቸው ገለጠ:: አገልግሎቱንና ስልጣንን ሰጣቸው ነገር ግን ይህን ያደረገው በተግባር ካዩት በኋላ ነው (10:1):: ግልጽ የሆኑ መመሪያዎችን ሰጣቸው (10:5 ጀምሮ):: ለከባድ ጥላቻና ስደት አዘጋጃቸው (10:17 ጀምሮ):: የሚያስፈልጋቸው ነገር እንደሚኖራቸው ተስፋን ሰጣቸው (10:19-20):: እንዳይፈሩ ነገራቸው (10:26):: ሰማይ ግባቸው እንደሆነ እይታን ሰጣቸው

(10፡32-39)፡፡ አንዳንድ ሰዎች ምላሽ እንደሚሰጡ ኢየሱስ ተናገረ (10፡40-42)፡፡ ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር በማድረግ ሂደት የሆነ ጊዜ ላይ ለመላክ ጊዜው እንደሆነ እንረዳለን፡፡ በዚያ ጊዜ በማቴ 10 ላይ ለደቀ መዛሙርቱ የኢየሱስን ምክር በጥበብ መከተል እንችላለን፡፡

መማለድ፡፡ ኢየሱስ ብዙውን ጊዜ ሲማልድ ይገኛል፡፡ እንደ ዮሐ 17 ግን የትም ጊዜ ፍቅሩን በሀይል የገለጠበት ክፍል አልነበረም ወይም ግልጽ ያለ አልነበረም፡፡ በመስቀሉ አስፈሪነትና በደቀ መዛሙርቱ ግራ መጋባት፣ ለደቀ መዛሙርቱ የኢየሱስ ጸሎት በዚህ ክሪቲካል ጊዜ በእግዚአብሔር ጥንቃቄ የያዛቸውን የድጋፍ ሲስተም ሰጥቷል፡፡ በጸሎቱ ለረጅም ጊዜ ስለ ደህንነታቸውም ጸልዮአል፡፡ “እንዲጠብቃቸው” (11-12)፣ “ደስታን እንዲሰጣቸው” (13) እና “እንዲቀድሳቸው” (17-19) አባቱን ጠይቋል፣ ጥበቃ ፣ ስለ ደስታና ስለ ቅዱስ መለየት፡፡ ደቀ መዝሙር ለምናደርጋቸው ተማሪዎች የምንጸልይላቸው እንዴት ያለ ታላቅ ጸሎት ነው፡፡ በግልጽ ጸልይላቸው ደግሞም ዘወትር ጸልይ፡፡

መገምገም፡፡ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አንዱ የኢየሱስ ዋና ሚና እርሱን መገምገም ነበር፡፡ ኢየሱስ የሰጣቸው ግምገማዎች ለደቀ መዛሙርቱ የተሰጠ ጊዜአዊና እውነተኛ ግምገማዎች ናቸው፡፡ ጥበብ የሌለው ንግግርን (ሉቃስ 10፡17-20)፣ እውነተኛ ያልሆኑ አስተያየቶችን (ዮሐ 13፡36-38) እና ያልተስተካከሉ ግቦችን (ማር 10፡35-45) ያሉትን “እውቀት ማጣቶችን” እንዲያውቁ ኢየሱስ ረዳቸው፡፡ ገሰጻቸው (ሉቃስ 9፡51-56፣ ማር 8፡31-33)፡፡ ጥያቄዎችን መለሰ (ማቴ 18፡21-38፣ ማቴ 19፡23-26፣ ሌሎችም ብዙ ምሳሌዎች)፡፡ ተማሪዎች ደቀ መዝሙር ሲደረጉ ለእነርሱ ከዋና በረከቶች አንዱ በቡድኑ ያላችሁት አንተና ሌሎች የምትሰጧቸው የፍቅርና እውነተኛ ግምገማ ነው፡፡ “እውቀት ማጣታችንን” ሳናውቀውም እንኳን እንድንስት ያደርገናል፡፡ ተማሪዎችህን መገምገም ክርስቶስን ወደ መምሰል እዲያድጉ ያደርጋቸዋል፡፡

መባዛት፡፡ ኢየሱስ ደቀ መዝሙር ማድረግ በራሱ ፍጻሜ እዳልሆነ ያውቃል፡፡ ለመባዛት ፍጻሜ መንገድ ነው፡፡ በኢየሱስ አገልግሎት መጀመሪያ ላይ ደቀ መዛሙርቱ “ሰዎችን አጥማጅ” እንደሚሆኑ አበረታታቸው (ማር 1፡17)፡፡ በኋላ፣ “ደቀ መዛሙርት እንዲያደርጉ”

አዘዛቸው (ማቴ 28፡18-20)። ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ያደረገው ነገር የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የተገበረችበት መንገድ ሆነ። "መንፈሳዊ መባዛታቸው" ነው አለምን የገለበጠው። ኢየሱስ ባደረገው መንገድ ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር ማድረግ በእድሜ ከፍ ያሉ ተማሪዎች በእድሜ ያነሱ ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር እንዲያደርጉ በፍጠነት ይመራል ። ከዚያም ባልተወሰኑ አቅጣጫዎች አገልግሎትህ ወደ ከፍተኛው አቅም ያድጋል።*[1] ኢየሱስ በደቀ መዛሙርቱ ያደረገው ነገር ተግባራዊና ተጨባጭ ነው። ኢየሱስ ባደረገው መንገድ ተማሪዎቻችንን ስናሰለጥን፣ ከማስመስልና ካልበሰለ ቤተ ክርስቲን ሂያጅ የህይወት ለውጥን ወደሚለማመዱ ተማሪዎች እናሽጋግራቸዋለን ደግሞም ህይወት ለዋጮች ለመሆንም ሰልጥነዋል። ከዚያም ለኢየሱስ መሠረታዊ በሆነ መልኩ አለማቸው ላይ ተጽኖ ያመጣሉ።

---

1 * የዚህ ሀሳብ ቅደም ተከተል በሮበርት ኮልማን ከተጻፈ ዘ ማስተር ኦፍ ኢቫንጀሊዝም ከተሰኘ የደቀ መዝሙርነት ክላሲክ መጽሐፍ ነው። ሌሎቹ ሀሳቦች የመጡት የኮልንን ጽንሰ ሀሳብ ከሚያጠቃልሉ "ኢንሳይት ፎ ሊቪንግ" ቅደም ተከተል ነው።

# ብርቱ ጥያቄዎች

ከ1 -10 ስኬል ላይ ራስህን በመለካት እነዚህን ጥያቄዎች መልስ። ከመልሶችህም የተነሳ በራስህ ሁኔታ ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር የማድረግን አስፈላጊነትና የእርሱን ዋጋ የሚገልጽ አጭር አንቀጽ ጻፍ። ለትክክለኛ ፐርሰንቴጅ እያንዳንዱን ጥያቄ መርምር።

1. ከአጠቃላይ ተማሪዎceህ ውስጥ ምን ያህል ፐርሰንቱ ነው የየሳምንቱን ስብሰባዎች በመደበኛነት የሚሳተፈው?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

2. ከ9-12 ክፍል ምን ያህል ተርሰንቱ ነው ከወጣቶች አግልግት የወጣው?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

3. ክክርስቶ ጋር በፍላጎት ህብረትን የሚያደርገው ከአጠቀላይ ተማሪዎችህ ውስጥ ምን ያህል ፐርሰንቱ ነው?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

4. ከተማሪዎችህ ውስጥ ምን ያህል ፐርሰንቱ ነው በጠለቀ፣ በተሰጠ ደቀ መዝሙርነት ቡድን ውስጥ የሚተፈው?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

5. ከተማሪዎችህ ውስጥ ምን ያህል ተርሰንቱ ነው ወጣት ተማሪዎችን ደቀ መዝር ባድረግ የሚሳተፈው?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

6. ከተመራቂ ተማሪዎችህ ምን ያህል ተርሰንት ነው ኢየሱስን በሙሉ ልብ የሚከተለውና ለእረሱ የሚኖረው? (ሲንየሮቹን በሙሉ ዘርዝር ደግም ባለ ሙሉ ልቦቹን ቼክ አድርግ)

   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

በራሴ ሁኔታ ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር የማድረግ አስፈላጊነትና የእሱ ዋጋ፡

# የወጣት አገልግሎት መርሆች

## የህይወት ለውጥ የተለማመዱትን ተማሪዎች ደቀ መዝሙር የምታደርገውና ህይወት ለዋጮች የሚሆኑት እንዴት ነው?

ተማሪዎች አገልግሎትህን ሲተው፣ ሲመጡ ከነበረው ይልቅ ህይወታቸው የሚለየው እንዴት ነው? በቱቦው በዛኛው ቀዳዳ የሚመጣው ምንድን ነው?

## ደቀ መዝሙር የማድረግ መርሆች

2 ጢሞ 2፡1-2ን 6 ጊዜ አንብብ፡፡ በምታነብበት በእያንዳንዱ ጊዜ ማስታወሻ ወሰድ፡፡ በእያንዳንዱ ንባብ ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር ለማድረግ አንድ መርህን ለማግኘት ሞክር፡፡

እንግዲህ፥ ልጄ ሆይ፥ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ። ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ።

2 ጢሞ 2፡1-2

1.

2.

3.

4.

5.

6.

እያንዳንዱ መርህ ለአንተና ለአገልግትህ ምን ማለት እንደሆነ በአንድ አረፍተ ነገር ግለጽ፡፡

## 1. መቀበል

እንግዲህ÷ ልጄ ሆይ÷ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ

## 2. ግኙነቶች

. . . አንተ . . እኔ . . . (ጳውሎስና ጢሞቴዎስ)

## 3. ነጸብራቅ

. . . ስታመኑ

## 4. እውነታ

. . . ብዙ ምስክሮች ባሉበት . . .

## 5. አደራ መስጠት

. . የታመኑ ሰዎች . . .

## 6. መባዛት

. . . አንተ . . . እኔ . . .የታመኑ ሰዎች. . . .ሌሎች

---

ደቀ መዝሙር ማድረግ ሲተረጎም
ለተማሪዎች ትናንሽ ቡድን ፣ ከስርዓት ጋር ተጓዳኝ ልምድ፣ ተጠሪነት፣ መነቃቃትን፣ እድገትን፣ ድርጊትንና አገልግሎትን የሚያስከትል ብርታትን መስጠት

---

# ተግባራዊ እርምጃዎች

ክክርስቶስ ጋር ባላቸው ህብረት ወደ ብስለት መሄድ የሚሹ ከ3-12 ልጆች የያዘ ቡድንን ሳል። በዚህ ቡድን ምን እርምጃዎችን ትወስዳለህ?

## 1. ጸልይ

ማንን ደቀ መዝሙር እንደምታደርግና እንዴት ደቀ መዝሙር እንደምታደርግ እንዲያሳይህ ጌታን ጠይቅ። ለሌሎችም የሰለጠኑ የደቀ መዝሙርነት ቡድን መሪዎችም ጸልይ። በተማሪዎች ህይወት ውስጥ መነቃቃት፣ እድገት፣ ድርጊት እና አገልግሎት እንዲኖር እግዚአብሄርን ጠይቅ።

## 2. አልም

ደቀ መዝሙር የሆኑ ተማሪዎች የህይወት ለውጥን ከተለማመዱ ደግሞም ህይወት ለዋጭ ከሆኑ ምን ሊሆን እንደሚችል አስብ።

## 3. ምረጥ

ጌታ ደቀ መዝሙር እንድታደርጋቸው ወደ አንተ ካጣቸው ተማሪዎች ጋር በግል ተገናኝ። ራዕይን አካፍል። ፊት ለፊት ቻሌንጅ አድርጋቸው። ኢየሱስን በመከተል ገጽ 11 ላይ ያለው “ የግል መሰጠት” ላይ ስትደርስ ክፍሉን ከፍ አድርግህ አስቀምጣላቸው።

## 4. መሰጠት

ልዩ በሆነ ስብሰባ ላይ ምላሽ ለሚሰጡ ተማሪዎች (ኢየሱስን መከተል ገጽ 11) የግል መሰጠትን ግለጽ። በጊዜ ዋጋቸውና ቅድሚያ የሚሰጡት ነገር መለወጥ ላይ ቻሌንጅ አድርጋቸው። ከዚያም ክክርስቶስ ጋር ባላቸው አካሄድ፣ በግል እድገታቸው፣ በአመራር ክህሎታቸው፣ እና በትምህርት ቤት ላይ በሚያመጡት ተጽኖ ይህ ልምምድ እንዴት ትርፋማ እንደሚያደርጋቸው በመግለጽ አበረታታቸው።

## 5. ተዘጋጅ

በገዛ ራስህ መጽሐፍ እያንዳንዱን ሳምንታዊ ክፍለ ጊዜ አሟላ። ወደ ፍጽምና መሄድ ሲ.ረስ ላይ የመሪዎች መመሪያ ቡድንህን የመምራት ጥያቄህን ይመልሳል። የመሪዎችን መመሪያ ባጠቃላይ

ተመልከትና የርዕሱ ህያውና ጥልቅ ውይይት እንዲኖራቸው ተማሪዎችህን ለመጠየቅ ቁልፍ ጥያቄዎችን ፈልግ። ጥያቄዎቹን ለቡድን ስብሰባ በ3 x 5 ካርድ ላይ ጻፋቸው። የመሪዎች መመሪያህን ወደ ቡድኑ አትውሰድ። ተዘጋጅተህ ሂድ።

## 6. ምራ

አንተ መሪ ነህ። ለቀረው ቡድን ፍጥነትን አስቀምጥ! ክርስቶስን ለተማሪዎቹ የሚያንጸባርቅ መሪ እንዲያደርግህ ጌታን ጠይቀው። ግራ ከተጋ እርዳቸው፣ አበረታታቸው፣ ደውልላቸው፣ ተገናኛቸው ከሁሉም በላይ አብረሃቸው ጸልይ። የቀረው ህይወታቸውን በሙሉ አመራርህ ስር ነቀል በሆነ መልኩ በነርሱ ላይ ተጽኖ ያመጣል።

## 7. ኢንቨስት አድርግ

እነዚህን ተማሪዎች ደቀ መዝሙር ማድረግ ከቡድኑ ስብሰባ በላይ ነው። የግንኙነት ኢንቨስትመንት ነው። ይህን ቡድን በመምራት ጓደኛና አማካሪ ትሆናለህ። ከቡድን ስብሰባው ውጪ ራስህን ለተማሪዎች ስጥ።

## 8. ለካ

ከስብሰባህ በኋላ በየሳምንቱ፣ የሰራኸውን ነገር ገምግምና እንዴት ማሻሻል እንደምትችል ተመልከት። ችግሮችን ፍታ ደግሞም መሻሻሎችን አድርግ። ለመገምገም እንዲረዱህ በመሪዎች መመሪያ ውስጥ ያሉትን መሳሪያዎች ተጠቀም። እነዚህን የደቀ መዝሙርነት ቡድኖች ለማብዛት፣ የራስህን ቡድን ምራ ከዚያም የአመራር ቡድንህን ለሁለት ክፈለው ደግሞም እያንዳንዱን ቡድን የራሳቸውን ቡድን ለመጀመር ይህንን አይነት ሂደት እንዲከተሉ ተገዳደራቸው። በጊዜ ብዛት እያንዳንዱ ተማሪ ደቀ መዝሙር የመሆን እድል ይኖረዋል።

---

ታላቁን ተልዕኮ ለማሟላት ትልቁ
መንገድ በክንውን ሳይሆን በሂደት ነው
- ደቀ መዝሙር የማድረግ ሂደት።

# ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር የማድረግ መሳሪያዎች

# ወደ ብስለት የመሄድ ሲሪስ




ከ1 ሚልዮን በላይ በመሸጥ፣ ይህ የ8 መጽሐፍ የደቀ መዝሙርነት ሲሪስ ተማሪዎችን በክርስቶስ ወደ ማደግ ይወስዳል።

መጀመር አዳዲስ አማኞችን ክክርስቶ ጋር ያለ አካሄዳቸውን በተሳካ ሁኔታ እንዲጀምሩ ይረዳል፡፡

ኢየሱስን መከተል ከክርስቶስ ጋር የህይወት ለዋጭ ህብረትን የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ለመሆን ጽኑ መሠረትን ይገነባል፡፡

ከእግዚአብሔር ጋር ለብቻ ጊዜ መውሰድ ከእርሱ ጋር ጊዜን እንዴት ማሳለፍ እንዳለበት በመማር ከኢየሱስ ጋር ያለውን የተማሪውን ግንኙነት ጥልቅ ያደርጋል፡፡

ኢየሱስን ጌታ ማድረግ ኢየሱስን እንዲታዘዙና በየለቱ የሚገጥማቸውን ነገሮች እርሱ እንዲመራ ተማሪዎችን ይገዳደራል፡፡

እምነትህን ማካፈል ፍርሃታቸውን የማሸነፍ የዋይልድ አድቬንቸር ላይ ተማሪዎችን ይመራል ደግሞም በድፍረት ክክርስቶስ ጋር እንዲነጋገሩ አደጋውን እንዲወስዱ ያደርጋል፡፡

አስምህ ላይ ተፅኖ ማድረግ በዙሪያቸው ያሉ ሰዎችን ችግሮች በማገልገል ተማሪዎች ተጽኖ አምጪ መሪዎች መሆን እንደሚችሉ ያሳያል።

ከእግዚአብሄር ኖት ቡክ ጋር ለብቻ ማሳለፍ ከእግዚአብሔር ጋር ለብቻ ጊዜ ማሳለፍን እንዲመራቸው ለተማሪዎች ተግባራዊ መሳሪያዎችን ይሰጣል።

የመሪዎች መመሪያ ለቡድን መሪ ህያውና ህይወት ለዋጭ የደቀ መዝሙር ቡድንን ለመምራት የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶች በሙሉ ይሰጣል። ይህ መጽሐፍ ወደ ብስለት ለመሄድ ሲሪስ የተሟላ መጽሐፍት የመሪውን ማቴርያል ይዟል።

ወደ ብስለት የመሄድ ሲሪስ (8 መጽሐፎች ስብስብ) የተሟላ፣ ተማሪዎችን ከመለወጥ እስከማደግና አስከ አገልግሎት ወደ ፊት የሚያንቀሳቅስ ደረጃ በደረጃ የደቀ መዝሙርነት ሲሪስ ነው።

የኦድዮ ስብስብ በቤሪ ሴንት ክሌር፡ በዴቪድ ቡዝቢ፣ እና በጂም በርንስ የተዘጋጁ 6 በነጻ የሚወርዱ የሚሰሙ መልእክቶችን ይዟል - ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር አድራጊ እንደመሆንህ ዲዛይን የተደረጉ።

እነዚህን ማቴርያሎች ከደብሊው ደብሊው ደብሊው ሪችአውት.ኦርግ እዘዝ


# ኢየሱስ እኩያ የለውም




ቤሬ ሴንት ክሌር ከእግዚአብሄር ልጅ ጋር በፍላጎት ወደ መገናኘት ይወስድሃል። ኢየሱስ በትክክል ማን እንደሆነ ታውቃለህ። በኢየሱስ እኩያ የለውም የመጨረሻውን “የመንገድ ጉዞ” ትጓዛለህ። ከኢየሱስ ጋር የተሻለ ጓደኛ በመሆን ደስ ትሰኛለህ። በኢየሱስ እኩያ የለውም ጆርናል ውስጥ፣በኢየሱስ ህይወት፣ ሞት፣ ትንሳኤ፣ እርገትና ዳግም ምጻት ውስጥ ስትጓዝ የመንገድ ዞው ለ40 ቀናት ይቀጥ ላል። ስለ ኢየሱስ የምታስበው ነገርና አንተ የሆንከው ነገር ይፈተናል!

# ህይወት ይሰምራል!

## ታዳጊ ወጣቶችህ ዝግጁ እንዲሆኑ እርዳቸው




ኮሌጅ። ሙያ። የእድሜ ልክ ጓደኞች። የትዳር ጓደኛ። በሚቀጥሉት አምስት አመታት ታዳጊ ወጣቶችህ የህይወቱን/ቷን ወሳኝ ውሳኔዎች ሊያደርጉ ይችላሉ። በህይወት ይሰምራል ውስጥ ቤሬ ሴንት ክሌይር ልጆችህን በእነዚያ ውሳኔዎች እንድትመራቸው የመንገድ ማፕን ይሰጥሃል። ማንነታቸውንና ፍጻሜአቸውን - ለቀረው ዘመናቸው የሚጓዙበትን የራሳቸውን መንገድ ያውቃሉ። የመንገዱ ማፕ የታዳጊ ወጣቶችህን የስብዕና ባህሪዎች፣ መንፈሳዊ ስጦታቸውን፣ ችሎታቸውንና ተሞክሮአቸውን፣ መነቃቃታቸውን ፣ የህይወት ግባቸውን፣ እሴቶቻቸውን፣ አላማቸውን፣ የጊዜ አጠቃቀማቸውንና ውሳኔዎቻቸውን ያጠቃልላል። መሪ እንደመሆንህ ይህ መጽሐፍ የሚያስፈልግህን ነገር ለልጆችህ ደግሞ በዚህ መንገድ ወደታች ለመሄድ የሚያስፈልጋቸውን “ፍጻሜ ወሳኝ”
ዳውንሎዶችን ይሰጣል። እነዚህን ማቴርያሎች ከደብሊው ደብሊው ደብሊው ሪችአውት.ኦርግ እዘዝ

# የስራ እቅድ

በአሁኑ ጊዜ . . . ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር ለማድረግ ምን እያደረግህ ነው?

ወደፊት መሄድ -- ከዚህ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ያገኘሽውን ውሰድና ልዩ የሆነ የስራ እቅድህን ዲዛይን አድርግ

ለምንድን ነው ለአንተ ፣ ለበጎ ፈቃደኞችህ፣ እና ለወላጆች ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር ማድረግ አስፈላጊ የሆነው?

ምን ግቦችን ነው የምታስቀምጠው ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር ለማድረግ?

እነማን ናቸው ደቀ መዝሙር የምታደርጋቸው ተማሪዎች ደግሞስ ሌሎችን ደቀ መዝሙር የሚያደርጉ መሪዎች እነማን ናቸው?

የትነው የምትገናኙት ከደቀ መዝሙር ቡድን ጋር?

መቼ ነው ከደቀ መዝሙር ቡድን ጋር መሰብሰብ የምትጀምረውና የምትቀጥለው?

# ባህሉን ዘልቀህ ግባ

## ግቡ

ኢየሱስን ወደ ተማሪዎች ባህል እንዲያመጡ መሪዎችን፣ ወላጆችን እና ተማሪዎችን ማስታጠቅና ማንቀሳቀስ

ክፍለ ጊዜ 6

# ኢየሱስ ላይ ትኩረት ያደረገ

ኢየሱስ ሁልጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ ፍጥነትን ምሳሌን ነበር። “ከሀጢአተኞች” ጋር ህብረትን ሲከታተል ከነበረበት ጊዜ በላይ የትም አክቲቭ እና ሆን ብሎ ሲያደርግ የትም አናየውም። ኢየሱስ ስለ ራሱ እንዲህ አለ፡ “የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጣ” (ሉቃስ 19፡10)።

መሪ እንደመሆናችን፣ ተማሪዎቻችን ከማያምኑ ጋር ህብረትን ለመከታተል እንዴት መለኪያን እንደምናስቀምጥ ለማየት ጥርን አስብ። ኢየሱስ ከደቀ መዛሙቱ ጋር የጦር ጫፍ ነበር ደቀ መዛሙርቱ ደግሞ መያዣውን ነበሩ። መያዣው ጫፉን ይከተላል “ኑና፣ ተከተሉኝ” አለ ኢየሱ “እኔም ሰዎችን አጥማጆች አደርጋችኋለሁ” (ማቴ 4፡19)። በአገልግሎታችን እግዚአብሄር የማያምኑ ታዳጊ ወጣቶችን ለማጥመድና ተማሪዎችን እንዲሁ እንዲያደርጉ ለማሰልጠን ኢየሱስን እንድንከተል ይመራናል። መያዣው የጦሩን ጫፍ እንዲከተል ምሳሌአችንን ይከተላሉ።

ከማርቆስ 1-10 ኢየሱስ የማያምኑትን ሰዎች ባህል ዘልቆ የመግባት ልክን እንዴት እንደጀመረ 17 ምሳሌዎችን እገኛለን።

**1፡14 የእግዚአብሔርን መልካም የምስራች እያወጀ ኢየሱስ ወደ ገሊላ ሄደ**

**1፡21 ኢየሱስ ወደ ሲናጎግ በመሄድ ማስተማር ጀምሮ ነበር**

**1፡38 ኢየሱስ እንዲህ በማለት መለሰ — በቅርብ ወዳሉት ሌሎች መንደሮች እንሂድ - እዚያም ደግሞ እንድሰብክ“**

2፡1-2 . . . እርሱም ቃሉን ሰበከላቸው

2፡13 እንደገናም ኢየሱስ በባህሩ አጠገብ ሄደ። ብዙ ህዝብም ወደ እርሱ መጡ ያስተምራቸውም ጀመር

3፡1 ሌላ ጊዜ ወደ ምኩራብ ሄደ፣ የሰለለች እጅ ያለችው ሰውም በዚያ ነበር

4፡35 በዚያም ቀን በመሸ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን—ወደ ማዶ እንሂድ አላቸው“

6፡6ለ ከዚያም ኢየሱስ ከመንደር ወደ መንደር እያስተማረ ሄደ

6፡56 በገባበትም ስፍራ ሁሉ፥ መንደርም ከተማም ገጠርም ቢሆን፥ በገበያ ድውዮችን ያኖሩ ነበር፤ የልብሱንም ጫፍ እንኳ ሲዳስሱ ይለምኑት ነበር የዳሰሱትም ሁሉ ዳኑ።

7፡24 ከዚያም ተነሥቶ ወደ ጢሮስና ወደ ሲዶና አገር ሄደ። ወደ ቤትም ገብቶ ማንም እንዳያውቅበት ወደደ ሊሰወርም አልተቻለውም፤

7፡31 ደግሞም ከጢሮስ አገር ወጥቶ በሲዶና አልፎ አሥር ከተማ በሚባል አገር መካከል ወደ ገሊላ ባሕር መጣ።

8፡22 ሀ ወደ ቤተ ሳይዳም መጡ። ዕውርም አመጡለት፥ እንዲዳስሰውም ለመኑት።

8፡27 ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱም በፊልጶስ ቂሣርያ ወዳሉ መንደሮች ወጡ በመንገድም፦ ሰዎች እኔ ማን እንደ ሆንሁ ይላሉ? ብሎ ደቀ መዛሙርቱን ጠየቃቸው።

10፡1ሀ ከዚያም ተነሥቶ በዮርዳኖስ ማዶ ወደ ይሁዳ አገር መጣ፥

10፡17 እርሱም በመንገድ ሲወጣ አንድ ሰው ወደ እርሱ ሮጦ ተንበረከከለትና፦ ቸር መምህር ሆይ፥ የዘላለም ሕይወትን እወርስ ዘንድ ምን ላድርግ? ብሎ ጠየቀው።

10፡32ሀወደ ኢየሩሳሌምም ሲወጡ በመንገድ ነበሩ፥ ኢየሱስም ይቀድማቸው ነበርና

10፥46ሀ ወደ ኢያሪኮም መጡ። ከደቀ መዛሙርቱና ከብዙ ሕዝብ ጋር ከኢያሪኮ ሲወጣ የጤሜዎስ ልጅ ዕውሩ በርጤሜዎስ እየለመነ በመንገድ ዳር ተቀምጦ ነበር።

የኢየሱስ አገልግሎት እኛም እንድናደርገው ወደሚሻው ነገር ባህልን ዘልቆ ለመግባት ወዳደረገው ነገር ብርቱና ተግባራዊ እውቀትን ይሰጠናል። ለእኛ ያለውን መሻት በእያንዳንዱ ወንጌላትና በሐዋ ስራ ውስጥ ታላቁን ተልዕኮ በመግለጽ በግልጽና በተደጋጋሚ ገልጾአል (ማቴ 28፤18-20)፣ ማር 16፡15፣ ሉቃስ 24፡46-47፣ ዮሐ 20፡21፣ ሐዋ ሥራ 1፡8)። በማቴ 28፡19 የመሄድ ትእዛዝን ሰጠን። ለወጣት መሪዎች፣ እንዲህ እያለ ነው "እየሄዳችሁ ስለሆነ ተማሪዎ ወዳሉበት ሂዱ . . ." ለተማሪዎች እንዲህ ይላል፡ "ወደ ትምህርተ ቤት እየሄዳችሁ ስለሆነ፣ አቻዎቻችሁን ሂዱ ድረሱ።"

---

የኢየሱስ መልእክት በማያሻማ መልኩ ግልጽ ነው፡
"መልካሙን የምስራች ይዛችሁ ሂዱ!"

---

# ብርቱ ጥያቄዎች

ከ1-10 ሰኬል ላይ ራስህን በመለካት እነዚህን ጥያቄዎች መልስ:: ከመልሶችህም የተነሳ በምትኖርበት ቦታ በወጣቶች ባህል ዘልቆ ለመግባት የሚስፈልግህን የእውነተኛ ምርምር አጭር አንቀጽ ጻፍ::

1. ዛሬ በካምፓስ አልፈህ ከሆነ እዚያ ምን ያህል ምቾት ይሰማሃል?

   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

2. በከማፓስ የምታጠፋውን የጌዜ መጠን እንዴት ትለካዋለህ?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

3. ትምህርት ቤት በስም ከምታውቃቸው ተማሪዎች ምን ያህል ፐርሰንቱ ነው ከነርሱ ውስጥ የማያምኑት?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

4. ከበጎ ፈቃደኞችህ ምን ያህል ፐርሰነቱ ወደ ካምፓስ ይሄዳሉ?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

5. እንደ ኢየሱስ እንዲኖሩና በትምህርት ቤት ስን እንዲናሩ ለማዘጋጀት ለተማሪዎችህ የሰጠኸውን ስልጠና እንዴት ትልካዋለህ?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

6. በካምፓሶቻቸው ላይ ከተማሪዎች ውጥ ራሰቸውን እንደ አክቲቭ መንፈሳ ተጽኖ አምጪዎች የሚያዩት ምን ያህል ፐርሰንቱ ናቸው?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

   በምኖርበት ስፍራ የወጣቱን ባህል ዘልቆ ለመግባት የሚያስፈልገኝ እውነተኛ ኢንቨስትመንት፡

# የወጣቶች አገልግሎት መርሆች

## በተማሪዎች ባህል ውስጥ ኢየሱስን ለማምጣት በጎ ፈቃደኞችን፣ ወላጆችንና ተማሪዎችን የምናሰለጥነውና የምናንቀሳቅሰው እንዴት ነው?

ተማሪዎች ወዳሉበት መሄድ ብቻ ነው ትርጉም የሚሰጠው ነገር። በአሜሪካ ውስጥ ከአጠቃላይ ተማሪዎች 88 % ኢየሱስን አያውቁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጥቂተ ሰዎች ግን በዚህ ጉዳይ ምንም አያደርጉም። "የሚያስወጣን ብቸኛ ቀስቃሽ ነገር እግዚአብሔርንና ሌሎች ሰዎችን ከውስጥ ወደ ሩህሩህ አፍቃሪዎች ኢየሱስ ሲለውጠን ብቻ በኢየሱስ ውስጥ እንድንደሄድ የሚያስገድደን ምን ነገር አለ?

## የእግዚአብሄር ፍቅር ያነሳሳናል (ማር 6:34)

ኢየሱስ ለሰዎች ፍቅር አለው። በማር 6:34 "እረኛ እደሌላቸው በጎች ሆነው ነበርና ኢየሱስ አዝኖላቸው" እንደነበር እንመለከታለን። የኢየሱስ "ፍቅር" ወደኛ ሳበው። በተመሳሳይ መንገድ፣ ኢየሱስ ወደሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች እኛን ለማስጠጋት እግዚአብሔር "የኮምፓሽን ኮሽንታችንን" ሊጨምር ይፈልጋል። በማይገደው አለም ውስጥ ግድ እንዲለን ይጠራናል።

## ኢየሱስ ከምቾት ክልላችን እንድንወጣ ይጠራናል (ዮሐ 20:21)።

ኢየሱስ ከምቾት ቀጠናው ወደ ውጭ ወጣ። በአባቱ ቀኝ ተቀምጦ ደግሞም ወደ ማህጸን ለመምጣት ውሳኔን ሲያስርግ ፣ የሰው ውልደትን ሲለማመድ፣ በገላባ ላይ ሲተኛ፣ በሰው አካል ውስጥ ሲኖር፣ በነጠላ ጫማ ሲቆስል ፣ መጥፎ ምግብ ሲበላ አስቡት። ለዚያ በአባቱ አጠገብ ያለውን ምቾት ትቶ መጣ! አስቸጋሪ ውሳኔን አደረገና እኛንም እንዲሁ እንድናደርግ ይጠራናል።

ግድ በማይሰጠው አለም ውስጥ
እንደምንጠነቀቅ ፍቅር ያናገራል።

## ልጆች ወዳሉበት መሄድ አለብን (ዮሐ 1፡14)

ኢየሱስ በእኛ መካከል “ድንኳኑን ተከለ” (ኖረ)። ከእኛ ጋር አንድ ሆነ ከእርሱ ጋር አንድ እንድንሆን። አሁን እርሱን ስለምናውቅ፣ እነርሱም እሱን እንዲያውቁት ልጆች ወደተሰበሰቡበት እንሄዳለን።

## ታዳጊዎች የማይገመት ስቃይ አላቸው (ሉቃስ 15፡12-16)።

ኢየሱስ ስቃይ ምን ማለት እንደሆነ ያውቃል። ከዚያም ፈርቶ ዘወር አላለም። ይልቁን ተጋፈጠው እንጂ። ይህ ትውልድ በታሪክ ከየትኛውም ትውልድ በላይ የበለጠ ስቃይ አለው። ልክ እንደለምጻሙ የፈውስ መነካትን ይፈልጋሉ። የቆሰለ ፈዋሽ ይፈልጋሉ (ኢሳ 53፡ 4-6)። ብቸኛው ተስፋቸው እርሱ ነው። ልክ እንደ ኢየሱስ ለህመማቸው የፈውስ መነካትን ልንሰጣቸው እንችላለን።

## ልጆች የሆነ ሰው ግድ እንደሚለው ማወቅ አለባቸው (ሉቃስ 15፡1-2)

ኢየሱስ የሀጢአተኛ ወዳጅ የመሆን በጎ ምርጫ አደረገ። ምርጫ ከሀይማኖታዊ ተቋም እንደሚለይ ያውቃል። ይህ ግን እርሱን ያስቆመው አይመስልም። ለምን ቅድሚያ አሳጣጡን አስተካክሎ ነበር። የቤተ ክርስቲያን ሰዎች እንዲወዱት ከሚፈልገው በላይ ሀጢአተኞች እንደሚጠነቀቅላቸው እንዲያውቁ ፈልጓል። ልጆችማን ግድ እንደሚለው ማወቅ ይፈልጋሉ። ለተማሪዎ ግድ ስንሰኝ፣ ሀይማኖተኞች ይቆጣሉ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ “እንደዛ አይነት ሰዎችን” አይፈልጉም። ልክ እንደ ኢየሱስ መሆን ውድ ነገርን ይጠይቀናል፣ በተለይ ከሀይማኖት ሰዎች ጋር። ኢየሱስ ህይወቱን ጠይቆታል!

# ተማሪዎች ኢየሱስ ያስፈልጋቸዋል (ዮሐ 17፡3)

ተማሪዎች ህይወተን ይሻሉ፡፡ ነገር ግን ሊያገኙት እንደሚችሉ አያውቁም፡፡ የት መፈለግ እንዳለብን አናውቅም፡፡ የሚገኘው በኢየሱስ ውስጥ ነው ደግሞም የትም አይገኝም፡፡ ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ ―እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።“ (ዮሐ 17፡3)፡፡ ከመቼውም ይልቅ በግልጽ ተማሪዎች በእኛ አማካኝት በእርሱ ህይወትን ማግኘት ይችላሉ፡፡

---

በአንተ አማካኝነት ተማሪዎች ህይወትን ማግኘት ይችላሉ!

---

# ኢየሱስ በዚያ አለ (ማቴ 28፡7፣10)

ኢየሱስ ከሞት ተነስቷል፤ መልአኩም እንዲህ ብሎ ተናገሯል "ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል" (ማቴ 28፡7)፡፡ የተነሳው ክርስቶስ ወደ ተማሪዎች ባህል ለብቻችን አይልከንም፡፡ "ከፊት ቀድሟል" ደግሞም እዚያ ይጠብቀናል፡፡ ኢየሱስ በልጆች ህይወት እየሰራ ነው፡፡ እዚያ አብረነው እንድንሆን እየጠበቀን ነው!

አዲስ ኪዳን ሁለት አይነት ጊዜን ያመለክታል- ክሮኖስና ካይሮስ፡፡ ክሮኖስ የየለቱ የጊዜ ማለፍ ነው፡፡ ያ በየለቱ ለሁሉም ሰው ይሆናል፡፡ ካይሮስ ግን ልዩ ጠቀሜታ ያለው ታሪካዊ ጊዜ ነው፡፡ በሰው መልክ በቆየባቸው በሦስት አመታቱ ኢየሱስ በካይሮስ ጊዜ ነው የኖረው፡ "ጊዜው (ካይሮስ) በሙላት በደረሰ ጊዜ . . ." (ገላ 4፡4)፡፡ አሁን በእኛ ውስጥ በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ ፣ እኛም በካይሮስ ጊዜ ውስጥ ነው የምንኖረው፡፡ እኛን ካላወቁ በቀር ሊያገኙት በፍጹም የማይችሉ ኢየሱስን በጣም የሚፈልጉ ተማሪዎች እኛ ልንደርሳቸው በምንችልበት ክልል ውስጥ አሉ ፡፡ በዚህ ካይሮስ ጊዜ፣ እነዛን ወጣቶች በበህላቸው በኢየሱስ ስም እንድንደርሳቸው እንቅፋቶችን ሁሉ እንድናልፍ እግዚአብሄር እየመራን ነው፡፡ ጊዜው አሁን ነው!*2

---

ለዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን ትልቁ ፈተና ምናልባት ወጣቱ
ትውልድ ኢየሱስን እንዲከተል ለመጥራት ከ4ቱ ግድግዳዎችያስፈ መድረስ ነው።

---

2 *የዚህ አንቀጽ ኦሪጅናል ሀሳብ የተወሰደው በወዳጄ ሪቻርድ ከተሰጠ ለምን እግዚአብሔር ይህንን የተማሪዎች ትውልድ እንድንደርስ ይፈልጋል ከሚል ኢንስፓየሪንግ ንግግር ነው፡፡

# ተግባራዊ እርምጃዎች

በአጠገብህ ወዳለ መካከለኛ ትምህርተ ቤት ወይም ከፍተኛ ትምህርተ ቤት ካምፓስ ውጪ ወዳለ የእግረኛ መንገድ ላይ ሂድ። ተማሪዎች ሲገቡ ወይም ከትምህርት ቤት ሲወጡ ድረስ። ተመልከታቸው ደግሞም ማስታወሻ ውሰድ። ከዚያም ራስህን እነዚህን ጥያቄዎች ጠይቅ፡ ከነዚህ ውስጥ ስንቶቹ ኢየሱስ ክርስቶስን በግል ያውቁታል? ይህ አይን ከፋች ተሞክሮ ያለ ክርስቶስ ለሆኑ ተማሪዎች ከፍ ያለ ሸክም ይሰጥሀል። አሁን፣ ለተማሪዎች በጨመረ ሸክም በአካባቢህ ላለ ካምፓስ እነዚህን ርምጃዎች ለመውሰድ አስብ

1. ሞገስን ለማግኘት ጸልይ (ሐዋ ስራ 2:47)
   በፍላጎት መጸለይ ሴሽን ላይ የ3ዮሽ የጸሎት ስልትን መከተልheን ቀጥል። ከ3ዮሽ ጸሎትህ በተጨማሪ በጎ አድራጊዎችህን፣ ወላጆችን እና ተማሪዎችን በ3ዮሽ የጸሎት ስልት ላይ አሳትፋቸው። እንደመሳሪያ እንድትጸለይ እንዲመራህ አስደናቂ ዘዴን ተጠቀም።

2. ድልድይን ስራ - ትምህርት ቤቱን እወቅ (ሐዋ ስራ 17:16)

   ትምህርት ቤቱን ለማወቅ፣ ከነዚህ ተግባራዊ ጥቆማዎች መካከል ቢያንስ አንዱን ተከተል፡
   - የትምህርት ቤቱን ጋዜጣ/ አመታዊ አግኝና አጥናው
   - ስለ ትምህርት ቤታቸው በመጠየቅ የገዛ ልጆችህን ኢንተርቪው አድርጋቸው
   - ወደ ተማሪዎች ክንውኖች ሂድ፣ ተገናኝ ደግሞም ማስታወሻ ውሰድ
   - ካምፓሱን ዘልቆ በመግባት በትምህርት ቤቱ ሰርቬይ" ውስጥ እለፍ

3. ድልድዩን አቋርጥ- ከፕሪንሲፓሉ ጋር አውራ (ኤፌ 6:7)
   ወደ ፕሪንሲፓሉ ለመሄድ ድልድዩን ከማቋረጥህ በፊት

መሰረታዊ ውሳኔን ማድረግ አለብህ። በካምፓሱ ለህጋዊ መብትህ ትቆማለህ ወይስ ለትምህርቱ ቤቱ ራስህን ታስገዛለህ ደግሞም ታገለግላለህን ? በትምህርት ቤት አስተዳደር የረጅም ጊዜ ግንኙነት የማድረግ ብቸኛው መንገድ ማገልገል ነው። ልክ እንደ ኢየሱስ ለማገልገል ውሳኔ ከተደረገ በኋላ፣ ከፕሪንሲፓሉ ጋር ግኙነትን ለመመስረት መንገዱ ግልጽ ይሆናል።

ያንን ግንኙነት ለመመስረት እነዚህን ርምጃዎች ተከተል፡

- ኢንፎርማሊ ተገናኝ። የተማሪዎችህን አንዳንድ ወላጆች በማህበራዊ ትግበራ ላይ እንዲያስተዋውቅህ አግኛቸው
- ከተገናኝህ በኋላ፣ ለፕሪንሲፓሉ "የአመሰግናለሁ ማስታወሻ" ጻፍለት
- ፕሪንሲፓሉን ፎርማሊ በቢሮው ለመገናኘት ቀጠሮ ያዝ
- እንደገና ፕሪንሲፓሉን ለማመስገን ማስታወሻ ጻፍ በቋሚነት ከፕሪንሲፓሉ ጋር በመነጋገር ግንኙነትን መሥርት

## 4. ድልድዩን እንደተከፈተ አቆየው - ትምህርት ቤቱን አገልግል (ቆላ 3፡23-24)

እግዚአብሄር እንድታገልግልበት ከፈለገህ ትምህርት ቤት ውስጥ ስፍራ ለማግኘት

- የምትፈልገውን ክልል አግኝ ወይም እጥረት ያለበትን ስፍራ እወቅ
- አስተማሪዎች ወይም ተማሪዎች ችግር እንዳለ የሚያዩበትን ቦታ ጠይቅ
- ርግጠኛ ካልሆንክ፣ የተለያዩ የትምህርት ቤት ክንውኖችን በመሞከር በመርዳት ጊዜህን አጥፋ

## 5. ከተማሪዎች ጋር ህብረትን መሥርት (ዮሐ 4፡1-42)

ኢየሱስ ካላወቃትና እርሱን ከማታውቀው ጓደኝነትን እንዴት እንደጀመረ ለማወቅ በዮሐ 4 ውስጥ የኢየሱስን የንግግር ምሳሌ አጥና።

- ጥያቄዎችን ጠይቅ ደግሞም አዳምጥ፡፡ እነዚህን (ማን፣ ምን፣ የት፣ መቼ፣ ለምን እና እንዴት) የሚሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ማንንም ሰው ለ15 ደቂቃ ማነጋገር ትችላለህ፡፡
- ችግሮችን አንሳ ከነዚህ ችግሮች ውስጥም ማጽናናትንና ርዳታን ስጥ፡፡

## 6. በጎ ፈቃደኞችንና ወላጆችን አንቀሳቅስ (ቆላ 4፡7-15)

ልክ እንደ ኢየሱስ ጳውሎስ በደቀ መዛሙርቱ ላይ ኢንቨስት አድርጎ ነበር፡፡ በቆላ 4፡7-15 አንዳንዶቹን በስም ደግሞም የተጫወቱትን ልዩ ልዩ ሚና ይጠቅሳል፡፡ በጎ ፈቃደኞችህንና ወላጆችን በማሰልጠን ኢንቨስት ስታደርግ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ አገልግሎትና ልዩ ሚናቸውን እንዲያውቁ ልትረዳቸው ትችላለህ፡፡ አገልግሎታቸው በጊዜአቸው፣ በስጦዎቻቸው ፣ በጥሪአቸው እና በክህሎቶቻቸው ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይችላል፡፡


- የተወሰነ ጊዜአቸውን በመጠቀም፣ ከልጆቹ ጋር ለማውራት ከአንተ ጋር እንዲሄዱ በማድረግ የአመራር ቡድንህን አካትት
- በትምህርት ቤቱ ባለው ችግር በአመራር ቡድንህ አማካኝነት የሰዎችን የተወሰኑ ችሎታዎች ለማዛመድ መንገድን ፈልግ
- በእያንዳንዱ ሳምንት ለጥቂት ሰኣታት በተማሪዎችህ አንድ ቡድን ላይ መሪዎችህን ፎከስ አድርግ
- ወደቤታቸው የልቻቸውን ጓደኞች በመጥራት በመመገብ ወላጆች ከነርሱ ጋር ህብረትን እንዲገነቡ ወላጆችን እርዳ
- ለመስጠት ብዙ ጊዜ ያላቸውን የኮሌጅ ተማሪዎች ሀላፊነት ስጥ
- ለእያንዳንዱ ካምፓስ በበጎ ፈቃደኞችህ መሪዎች የጸሎት ቡድኖችን መስርት
- በካምፓሱ ላይ ከሌሎች ክርስቲያናዊ አገልግሎቶች ጋር ተጋመድ- ተሳሰር

## 7. ተማሪዎችን አንቀሳቅስ (ሐዋ ስራ 5፡ 41-42)

አሁንም ራስህን እንደ ጦሩ ጫፍ ተማሪዎችህን ደግሞ እንደ መያዣ ተመልከት። የአንተ ሚና ከመሪዎችህና ከተማሪዎቹ ፊት ፊት መሄድና እነርሱን ማስታጠቅ ክርስቶስንም ለጓደኞቻቸው እንዲያደርሱ መገዳደር ነው።

# ባህሉን ዘልቆ የመግባት መሳሪያዎች

## ካምፓሱን ዘልቆ መግባት





ዛሬ ተማሪዎች በትምህርት ቤት - ባሉበት በጣም መደረስ ይፈልጋሉ!

በመካከለኛ ወይም በከፍተኛ ትምህርት ቤት ካምፓሶቻቸው ከጉርምስናና ከህይወት ስሜታዊ፣ ማህበራዊ፣ እና መንፈሳዊ ፈተናዎች ጋር እንደሚጋፈጥ ተማሪ፣ ህይወታቸው ላይ ለውጥ ለማምጣት የወጣት መሪዎች “እዚያ መሆን” ይችላሉ::

በካምፓሱ ውስጥ ተማሪዎችን የመድረስ መሻትህን ለማካሄድ እንዲረዳህ፣ ካምፓሱን ዘልቆ መግባት ለወጣት መሪዎች፣ ለወላጆች እና ለበጎ አድራጎት ሰራተኞች ጥልቀት ያለው እይታና ተግባራዊ እቅዶችን ይሰጣል:: ለወጣቶች በግዛታቸው ላይ እንዲያዛምዱት እና ለነርሱ የእግዚአብሔርን ፍቅር ኮሙኒኬት እንዲያደርጉ ጥልቀት ያለውና ተግባራዊ ምክርን ይሰጣል:: ይህ መጽሐፍ በቤተ ክርስቲያንና በህዝብ ትምህርት ቤት መካከል ያለውን ክፍተት ለማጥበብ ይረዳል - ምናልባት ዛሬ በአሜሪካ ውስጥ በጣም አስፈላጊ የሚሲዮናዊ መስክ ነው::

## ካምፓስህን ለክርስቶስ መውሰድ




አሁን ይሄ መሠረታዊ ሀሳብ ነው! መሆን ይችላል:: ነገር ግን ጥቂት መሰረታዊ ፍቅር ያላቸውን መሠረታዊ ሰዎች ይጠይቃል:: መሠረታዊ ፍቅር:: የማያምኑ ተማሪዎች የሚያስፈልጋቸው ይህ ነው:: በዚህ መጽሐፍ ተማሪዎችህ እንዴት እንደሚኖራቸውና እንዴት እንደሚሰጡ ያውቃሉ:: እግዚአብሄር ትከሻቸውን መታ መታ ማድረግ ፣ ፊቱን እንያዩት ሊያደርጋቸው፣ እና በኢየሱስ ሃይል በመሰራታዊ መንገድ ጓደኞቻቸውን እንዲወዱ ይፈልጋል:: ተማሪዎች በትምህርት ቤቶቻቸው ልዩነትን ማምጣት ይችላሉ!

ካምፓስህን ለክርስቶስ መውሰድ በትምህርት ቤት ተማሪዎችህን እንድታሰለጥንና እንድታንቀሳቅስ ተግባራዊ ስልትን ይሰጣል::

እነዚህን ማቴርያሎች ከደብሊው ደብሊው ደብሊው ሪችአውት.ኦርግ እዘዝ

# የስራ እቅድ

በአሁኑ ጊዜ.. ባህሉን ዘልቀህ ለመግባት ምን እያደረግህ ነው?

ወደፊት መሄድ . . . ከዚህ ክፍለ ጊዜ ግኝቶችህን ውሰድና ልዩ የሥራ እቅድህን ዲዛይን አድርግ::

ለምንድን ነው ባህሉን ዘልቆ መግባት ለአንተና ለመሪዎችህ አስፈላጊ የሆነው?

ምን ግቦችን ነው ባህልን ዘልቆ ለመግባት የምታስቀምጠው?

ማነው የተወሰነ የታቀደ ተደራሲህ?

የት ነው ባህሉን ዘልቀህ የምትገባው?

መቼ ነው ባህሉን ዘልቀህ የምትገባው?

# የመድረስ አጋጣሚዎችን ፍጠር

## ግቡ

ተማሪዎች የማያምኑ ጓደኞቻቸውን በሚያመጡባቸው ከባህል ጋር ተያያዥነት ባላቸው የመድረስ አጋጣሚዎች ኢየሱስን ለማቅረብ

ክፍለ ጊዜ 7

# የመድረስ አጋጣሚዎችን ፍጠር

ክፍለ ጊዜ 7

## ኢየሱስ ላይ ትኩረት ያደረገ

ኢየሱስ ራሱን እንዴት ማቅረብ እንዳለበት ያውቅ ነበር። ዮሐንስ እንዲህ ይጽፋል፡

> ከበዓሉም በታላቁ በኋለኛው ቀን ኢየሱስ ቆሞ፦ ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ። በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ፥ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ።
>
> ዮሐ 7፡37-38

ሰዎች የማያምኑ ጓደኞቻቸውን በሚያመጡባቸው
ከባህል ጋር ተያያዥነት ባላቸው የመድረስ አጋጣሚዎች
ኢየሱስን እንዴት እንደምናቀርብ . . .
ጌታና መምህሩ ያሳየናል ::
ኢየሱስ ያንን ያደረገበትን መንገድ ቀርበን እንመልከት።

ኢየሱስን ማቅረብ። የዳስ በአል የእስራኤል ልጆች ውሃ ወድ በነበረበትና ለማግኘት አስቸጋሪ በነበረበት በምድረ በዳ ተቅበዝባዦች እንደነበሩ የማስታወሻ በአል ነበር። በበአሉ ወቅት፣ ካህኑ ወርቅ . . . ይወስድና ወደ ሰሊሆም መጥመቂያ ይወርዳል ደግሞም በውሀ ይሞላዋል። ኢሳ 12፡3ን " ከደህንነት ጉድጓድ ውሀን በደስታ ትቀዳለህ" ህዝቡ እየደገሙ ሳለ ውሃውን መልሶ ለዚህ በአል በተዘጋጀ በተለየ በር - የውሀ በር ይወስደዋል። ውሀውን ወደ መቅደስ ይወስደዋል ደግሞም በመሰዊያው ላይ ለእግዚአብሔር ቁርባን አድርጎ ያፈሰዋል።

ምናልባትም በዛው ጊዜ የኢየሱስ ንግግር ጮኸ፣ "ማንም የተጠማ ቢኖር ወደኔ ይምጣና ይጠጣ"። ማንም መልእክቱን ያልሰማ የለም። ኢየሱስ በበአሉ የተመለከተውን ህያው ውሀ እንደሆነዓ ራሱ አመለከተ። በዚህ ሞቃታማና አቧራማ ቀን ኢየሱስ እንዲመጡና ችግራቸው እንዲቀረፍ እርሱን እንዲጠጡ ጠራቸው። በርሱ የሚያምን የህይወት

ውሃ ወደርሱ ፣ በርሱና ከእርሱ እንደሚፈስ የተስፋን ቃል ሰጠ።

የወጣት መሪዎች ፈተና ተማሪዎች ኢየሱስ ማን እንደሆነ እንዲረዱና እርሱን መጠጣት እንዲፈልጉ ኢየሱስ ራሱን ባቀረበበት እንዲህ ባለ ድፍረት በተሞላበትና አስገዳጅ መንገድ ኢየሱስን ማቅረብ ነው። ፈጠራ ያለበት የመድረስ አጋጣሚዎች ተማሪዎች ህያውን ውሃ እንዲጠሙ በሚያደርግ መንገድ ኢየሱስን ያቀርባል።

ከባህል ጋር በተገናኙ አጋጣሚዎች አማካኝነት።

ሌዊ ኢየሱሰስን ተያያዥነት ባለው ሁኔታ ማቅረብ ያውቅ ነበር። ኢየሱስን ገና ማግኘቱ ነበር (ሉቃስ 5:27-28)። ያ ፍንጭ ነው ! ወዳልዳኑት ተማሪዎች አለም ተመልሶ ለመሄድ የላቀው መንገድ ከዚያ አለም በቅርብ ጊዜ በመጣ ሌላ ተማሪ በኩል ነው። ልክ እንደ ሌዊ አንድ ተማሪ “ሁሉንም ትቶ ሲከተለው” ጓደኞቹ እንደዛው እንዲያደርጉ ጽኑ ፍላጎት ይኖረዋል።

ሌዊ ጓደኞቹ ኢየሱስን እንዲያውቁ ፈልጎ ነበር። ሉቃስ እንዲህ ይገልጻል፡ “ሌዊም በቤቱ ታላቅ ግብዣ አደረገለት፤ ከእነርሱም ጋር በማዕድ ተቀምጠው የነበሩ ከቀራጮችና ከሌሎች ሰዎች ብዙ ሕዝብ ነበሩ።” (ሉቃስ 5፡ 29)። ሌዊ ድግስ አዘጋጅቶ ነበር! በኢየሱስ ያገኘውን አዲስ ህይወት ለማካፈል ፓርቲውን አዘጋጀ።

ኢየሱስ በርሱ ጓደኞች ዙሪያ ሆኖ ሌዊ ምቾት አግኝቶበት የነበረውን ጓደኞቹም በኢየሱስ ዙሪያ ሆነው ምቾት አግኝተውበት የነበረውን ሁኔታ እንደፈጠረ ልብ በል። ብዙዎቹ የወጣት አገልግሎቶች የሚገጥማቸው አንዱ ትልቁ ችግር ያንን አይነት አዎንታዊ ሁኔታ መፍጠር ነው። ክርስቲያን ተማሪዎች የማያምኑ ጓደኞቻቸው ኢየሱስን እንዲያገኙ ለማምጣት ነጻነት/ ምቾት ማግኘት አለባቸው። የማያምኑ ተማሪዎች ደግሞ በኢየሱስ ዙሪያ ለመሆን ነጻነት ሊሰማቸው ይገባል።

ሰዎች የማያምኑ ጓደኞቻቸውን ወደ ሚያመጡባቸው። ዘ ዌል ሚኒንግ ደቀ ዛሙርት የማያምኑ ሰዎችን ወደ ኢየሱስ እንዴት እንደሚያመጡ እውቀት አልነበራቸውም። በማር 10:13 ኢየሱስን ካልተገሩና ከሚረብሹ ህጻናት ሊከላኩት ፈልጉ። ኢየሱስ እንዲዳስሳቸው ሰዎች ልጆቻቸውን ያመጡ ነበር ደቀ መዛሙርቱ ግን ገሰጹአቸው። ብዙ ጊዜ የቤተ

ኢየሱስ ላይ ትኩረት ያደረገ የወጣቶች አገልግሎት

ክርስቲያን ሰዎች እንደ “ገሳጮች” ያገለግላሉ:: አማኞችን የሚያጠፉ እንቅፋቶችን ይፈጥራሉ:: ባልዳኑት ልጆች ላይ የሚንጸባረቅ የንቀት አመለካከት እንዳልተፈለጉ ወደሚያደርግ ስሜት ያመራል::

ያንን ሁኔታ ለመገልበጥ ኢየሱስ ምን እንዳደረገ ተመልከት::

> ኢየሱስ ግን አይቶ ተቈጣና፦ ሕፃናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተዉ አትከልክሉአቸው፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደነዚህ ላሉት ናትና። እውነት እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባባትም አላቸው። አቀፋቸውም እጁንም ጭኖ ባረካቸው።
>
> ማር 10፡14-16

በዘር በእድሜ፣ በሙዚቃ፣ በአመለካከት፣ በአለባበስ፣ እና በልምዶች መከፋፈል ለእኛ ቀላል ነው:: በእነዚህ የተሳሳተ አመለካከት የመድረስን አጋጣሚ ከፈጠርን፣ አውቀንም ይሁን ሳናውቅ ሰዎችን ከወንጌል እናወጣለን:: ከዚያም የማያምኑ ሰዎች ለምን እንደማይመጡ ወይም መጥተው ለምን ምላሽ እንደማይሰጡ እንጠይቃለን:: የእርሱ መንፈስ በውስጣችን እንዳለ እንደ ኢየሱስ ተወካዮች እንቅፋቶችን ማስወገድና በመድረስ አጋጣሚዎቻችን የማያምኑ ጓደኞቻቸውን ወደ ኢየሱስ ተማሪዎች  ማምጣት የሚችሉበትን መንገድ መፍጠር አለብን::

---

> በባህላችን ቤተ ክርስቲያን ስለማይሄዱ ህጻናት የሆነ ነገር ልብ ብያለሁ በሀይማኖታዊ ምርጫ ብዙዎቹ አደጋ ያለው የህይወት ዘይቤ ይከተላሉ። እንዲህ ሆኖ ሳለ የወጣት ቡድን ልጆቻችን በምቹ ዞን ተቆልፎባቸው ይቆያሉ ....
>
> ዛሬ ወጣት ሰዎች ክርስቶን ለመከተል ለአደጋ ህይወት መጠራት አለባቸው። ብዙዎቹ ቤተ ክርስቲያን የሆነ ትልቅ ነገር፣ ጥቅም ያለው ነገር፣ ለማድረግ ሪስክ ያለው ነገር እንድትሰጣቸው እየጠበቁ ነው።
>
> ፖል ቦርዝዊክ

---

# ብርቱ ጥያቄዎች

ከ1-10 ስኬል ላይ  ራስህን በመለካት እነዚህን ጥያቄዎች መልስ። ከመልሶችህም የተነሳ ከባህል ጋር ተያያዝነት ያላቸውን የመድረስ አጋጣሚዎች  ለመፍጠር የሚያስፈልጉህን ነገሮች  የሚገልጽ አጭር አንቀጽ ጻፍ።

1. በማህበረሰብህ ውስጥ በሚገኙ ካምፓሶች በሙሉ የሚገኙትን ተማሪዎች ለመድረስ ያለህን ሸክምህ እንዴት ትለካዋለህ?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

2. በግል ክርስቶስን ለተማሪዎች በመናገር ረገድ ውጤታማነትህን እንዴት ትለካዋለህ?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

3. ከተማሪዎህ ውስጥ ስንቱ ፐርስነት ነው የመድረስ አመለካከት ያላቸው?

   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

4. የመድረስ አጋጣሚዎችህ ምን ያህል “ፓጋን -ፍሬንድሊ” ናቸው?
   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

5. በመድረስ አጋጣሚዎችህ የሚሳተፉ የተማሪዎችህ አጠቃላይ ቁጥር ምን ያህል ፐርሰንት ናቸው? የማያምኑትስ?

   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

6. ከአሁን አክቲቭ ተማሪዎችህ ውስጥ በመጨረሻው አመት ኢየሱስን ወደ ማወቅ የመጡት ምን ያህል ፐርሰንቱ ናቸው?

   1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

በእኔ ሁኔታ ከባህል ጋር ተያያዝነት ያላቸውን የመድረስ አጋጣሚዎችን

የመፍጠር አስፈልጎት፡

# የወጣት አገልግሎት መርሆች

## ሰዎች የማያምኑ ጓደኞቻቸውን በሚያመጡባቸው ከባህል ጋር ተያያዝነት ባላቸው የመድረስ አጋጣሚዎች ኢየሱሰስን የምናቀርበው እንዴት ነው?

ልጆችን በህይወት ለዋጭ ግንኙነት ከኢየሱስ ጋር እንዲጀምሩ መጥራት ከፈልግን፣ ብዙውን ጊዜ ኢየሱስን በግልጽ እንደማናቀርብ ማወቅ አለብን፣ ስብሰባው ከባህል ጋር ተያያዥነት የለውም ልጆቻችንም ደግሞ የማያምኑ ጓደኞቻቸውን ለማምጣት ተነሳሽነት የላቸውም፡፡ ከላይ ያለውን ጥያቄ የአሁን ዘዴዎችን በሚለውጥ መንገድ መመለስ አለብን፡፡ ያን ለማድረግ የ “4-2-5” ዘዴን እንጠቀም፡፡

## 4 ባህርያት

እንዴት ኢየሱስ የወንጌል በሮችን እንደከፈተ ወደ ወንጌላቱ ስንመለከት፣ አራት ባህሪያትን እናገኛለን፡፡

### 1. ኢየሱስ የዋናው ነገር ትኩረት ነበር (ማር 1፡ 40-45)፡፡

ምንም እንኳን ለምጻሙ የነጻና ተአምር የተካሄደ ቢሆንም፣ ሰዎች ከየትኛውም ስፍራ እርሱን ለማየት እስኪመጡ ድረስ ኢየሱስ ሄሮ ነበር፡፡

### 2. ህዝቡ በናፍቆት ተሞልተው ነበር (ማር 4፡1)

ህዝቡ ኢየሱስን እስከ ውሃው ዳርቻ ድረስ ገፍተውት ነበር ወደ ጀልባው ዘሎ እንዲገባ፡፡

### 3. ኢየሱስን እንዲገናኙ አማኞች ጓደኞቻቸውን አምጥተው ነበር (ሉቃስ 5፡27-29)

ሌዊ፣ የተናቀ ቀረጥ ሰብሳቢ ኢየሱስን ተገናኘ። ጓደኞቹ ኢየሱስን እንዲገናኙ ደስታውን ለመያዝ ባለመቻል ሌዊ ሁሉንም ወደ አንድ ግብዣ ጠራቸው

### 4. ህይወቶች ለዘላለም ተለውጠው ነበር (ማቴ 20፡29-34)

ሁለት እውሮች ለምህረት ሲጮሁ ኢየሱስ በርህራሄ አይኖቻቸውን ዳሰሰ። ተፈውሰው ኢየሱስን ተከተሉ - ለዘላለም በመለወጥ።

## 2 አመለካከቶች

በተማሪዎች ህይወት ውስጥ የመድረስ ከፍተኛ ተጽኖ ረጅም ክለሳ ይኑርህ። እይታን ለማግኘት በጥንድ የባይናኩላር ሌንሶች ውስጥ መመልከትን አስብ። በርቀት ያለውን ነገር ያቀርባሉ። መድረስ ላይ ስንሰራ‹ “በዚህና በአሁን” የድርጊቱን ፍሰት በመያዝ በቀላሉ እይታን እናጠራለን። ይልቁንም በሁለቱ ሌንሶች ውስጥ በመመልከት በመጨረሻ ላይ አስፈላጊ በሆነው የባይናኩላር እይታ ላይ መጠበቅ አለብን።

## ሌንስ 1. ኢየሱስ ላይ አተኩር

አውትሪቹን በዚህ ላይ በማተኮር ተማሪዎች ኢየሱስን እንዲለማመዱ እርዳቸው። አስፈላጊው ነገር የክንውኑ መጠን እንደሆነ ስናስብ እይታ ይጠፋል። ስኬት በቁጥር አይለካም። ተማሪዎች ከኢየሱስ ጋር እንዲገናኙና ልባቸውን ለእርሱ እንዲሰጡ በመርዳት እንጂ።

## ሌንስ 2፡ አላማን ማወቅ

የአውትሪቹን አላማ በግልጽ እይታ ላይ ጠብቅ ሰዎች የማያምኑ ጓደኞቻቸውን ወደሚያመጡባቸው ከባህል ጋር ተያያዥነት ባላቸው

የአውትሪች አጋጣሚዎች ኢየሱስን ለማቅረብ። ከዚያም ለእያንዳንዱ አውትሪች ግልጽ አላማን ወስን። “አሁን እነርሱን ለማስደሰት ለማድረግ ምን ላይ ደረስኩ” አባዜን ለማስወገድ።

# 5 አማራጮች

አውትሪችን ለማዘጋጀት፣ ለማሰራጨትና ካለቀም በኋላ ለማጽዳት የግንኙነት ጊዜህን ትልቅ ጉማጅ ሊወስድ ይችላል። የአውትሪችን የጊዜ ብክነት ለመከላከል አስቀድመህ አማራጮችህን በሙሉ መርምርና ከዚያ ከሁሉም ይልቅ የጊዜ ውጤታማ እና በአንጻሩ ፍሬአማ የሆነውን አንዱን ምረጥ።

የትኛውንም አማራጭ ብትመርጥ ፣ የደቀመዝሙር ቡድኖችህን ማካተትህን ርግጠኛ ሁን። እያንዳንዱን የደቀ መዝሙርህን ቡድኖች አደራ መስጠት ትችላለህ የራሳቸውን አውትሪች በመፍጠር ሀላፊነት ወይም ለትልቅ አውትሪች ለእያንዳንዱ የደቀ መዝሙር ቡድን አንድ የሃላፊነትን ክልል መስጠት ትችላለህ። በየትኛውም መንገድ የአውትሪቹ ባለቤት ይሆናሉ በሂደቱም ደግሞ የአመራር ክህሎታቸውን ያሳድጋሉ። ለማዘጋጀት ጓደኞቻቸውን ለማምጣት፣ ፕሮግራምን ለማካሄድ በኋላም ለማጽዳት ኃለፊነትን ይወስዳሉ።

## 1. ተበደረው

እዚህጋ የሚመጣው መርህ “ከጸሐይ በታች ምንም አዲስ ነገር የለም” ነው (መክ 1፡9)። ባየኸው ሌላ አውትሪች ጥቂት ወይም ሁን ተበደር።

## 2. ፍጠረው

እዚህጋ የሚመጣው ሌላ መርህ “ሰዎች የፈጠሩትን ነገር የመደገፍ ዝንባሌ አላቸው” የሚል ነው። በርግጥ አስቸጋሪና ብዙ ጊዜ የሚወስድ ሊሆን ይችላል። የበጎ ፈቃደኞች፣ የወላጆችና የተማሪዎችን ቡድን ከመሰብሰብ የሚመጣውን የግንኙነት ግንባታ ብድራት ልብ በል።

አውትሪችን ብሬን ስቶም ለማድረግ፣ ለመትከል ከዚያም በአንድ ላይ ለማካሄድ።

## 3. ግዛው

ወደ ቤተ ክርስቲያንህ ማምጣት የምትችላቸው ዝግጁ ፕሮግራሞች አሉ - ሙዚቀኞች፣ ስፒከሮች፣ የትያትር ቡድኖች፣ ኮሜድያኖች፣ እና ሌሎችም። ዙሪያህን ተመልከት። ዋጋውን አስብ። ደግሞም ፕሮጋራሙን እንደገና ተመልከት ኮንትራት ከመፈረምህ በፊት።

## 4. ተከራየው

ብዙ ጊዜ ከመግዛት ይልቅ ለመከራየት ቀላል ነው። የመዝናኛ ፓርኮች፣ ትናንሽ ጎልፍ ማጫዎቻዎች ፣ የኳስ ጨዋታዎች፣ የመዋኛ ገንዳዎች፣ ጂምናዚየሞች፣የበረዶ ማንሸራተቻዎች እና ቲያትር ቤቶች ዝግጁ የሆኑ የአውትሪች አጋጣሚዎችን ይሰጣሉ።

## 5. ተቀላቀለው

የአውትሪች አላማህን - ኮንሰርቶችን - ፊልሞችን፣ ኮንፍራንሶችን፣ የወንጌል ክንውኖችን ለማሳካት የምትከታተለውን አካባቢያዊ እድል ፈልግ። ይህ ዘዴ አውትሪችን ከማቀድ ጋር አብረው የሚሄዱትን ግዙፍ እንቅስቃሴዎች ችግር (ሎጂስቲካል ሀስልስ) በሙሉ ያስወግዳል። ከዚያም በግንኙነትና በአገልግሎትህ በቀጥታ ተጠቃሚ በሚያደርግ ክትትል ላይ ትኩረት ማድረግ እንድትችል ጊዜህን እንድታጠፋ ይረዳሀል። “4-2-5” ( 4 ባህሪያት፣ 2 እይታዎች፣ 5 አማራጮች”) ሲጸለይባቸውና በሚገባ ሲታቀዱ፣ ታዳጊ ወጣቶች የማያምኑ ጓደኞቻቸውን ለማምጣት ቻሌንጆችን ወደሚወሰዱበት ከባህል - ጋር ተያያዥነት ባላቸው የአውትሪች አጋጣሚዎች አማካኝነት ኢየሱስን ለማቅረብ ጽኑ መሰረት ይኖርሃል።

---

**ልጆችን በፍጹም ወንጌል እንዲደብራቸው አታድርግ!**
**ጂም ሬይበርን**

---

# ተግባራዊ እርምጃዎች ሁሉም ነገርህ የተደራጀ ይሁን

የአውትሪች አላማህን ለማሳካት ከአመራር ቡድንህ፣ ከቁልፍ ወላጆች፣ ደቀ መዝሙር ከሆኑ ተማሪዎችህ ከተውጣጡ ሰዎች የአውትሪች የእቅድ ቡድንን ሰብስብ። ሃሳቦችን አሰራጭ።

ወደ አውትሪቹ የእቅድ ሂደት ተግባራዊ ፈጠራን ለማምጣት "ስቶሪ ቦርዲንግ" ተብሎ የሚጠራ አጋዥ ዘዴን ተጠቀም። የሚከተሉትን እያንዳንዱን ጠቃሚ ነገሮች ስታቅድ ለእያንዳንዱ ሰው ሃሳባቸውን እንዲጽፉበት የ4 በ6 ማጣበቂያ ያለው ማስታወሻ መጻፊያን ስጥ። ከዚያም ከሚዛመዱአቸው ነገሮች ስር ቦርድ ላይ አጣብቃቸው። ለተማሪ መሪዎች፣ ለአመራር ቡድንህ ለቁልፍ ወላጆች፣ እና ለተማሪ መሪዎች የዚህን ሂደት ባለቤትነት ስጥ።

1. አላማ፡ የዚህ አውትሪች የተወሰነ አላማ ምንድን ነው?
1. የታቀደ፡ የታቀዱ ተደራሲዎችህ እነማን ናቸው?
1. ጭብጥ፡ ግልፅ ጭብጡ ምንድን ነው?
1. ግብ፡ ግልጽ ግቦች ምን ምን ናቸው?
1. ሀሳቦች፡ ምን አይነት ግልጽ የፈጠራ ፕሮግራሞችን ነው የምትጠቀመው?

ሀሳቦችን ካሰራጨህ በኋላ ከሁሉም ለተሻሉት ለአምስቱ ቅድሚያ ስጥ። በምትከተለው በአንዱ ላይ ተስማማ። ለታቀዱት ተደራሲዎች ያንን ሃሳብ እንዴት እንደምታስረዳ እንደገና በቅደም ተከተል አስቀምጥ/ ስቶሪ ቦርዲንግ አድርግ።

1. ማቴርያሎች፡ ምን አይነት ሰዎችና ምን አይነት ማቴርያሎች ናቸው የሚያስፈልጉት

2. ምርት፡ ግልጽ ፕሮግራሙ ምን ይመስላል? ማን ለምን ሀላፊነትን ይወስዳል? በምን ጊዜ?

## አላማህን በተመሳሳይ አቅጣጫ ምራ

በአውትሪቹ ውስብስበነት ላይ ተመስርቶ ፣ ለመፈጸም እቅድህ አንድ ወይም በርካታ ስብሰባዎችህን ሊወስዱ ይችላል። ቡድንህ በተመሳሳይ አቅጣጫ መሄዱን እንዲቀጥል፣ ግስጋሴህን በመጠቃያ ማስታወሻዎች ኮሙኒኬት አድረግ። ሀንድ አውት አርጋቸው ወይም በነጭ ቦርድ ላይ ጻፋቸው። የተሳተፈው ሰው ሁሉ በተመሳሳይ አቅጣጫ መሄዱን እንዲቀጥል በአጠቃላይ ሂደቱ ወቅት እቅዶችህን የሚታዩ አድርገህ ጠብቅ።
በስኬት እስኪጠናቀቅ ድረስ ከአውትሪች የእቅድ ቡድን ጋር በጸሎት አውትሪችህን ተከተል። በሂደቱ ሁሉ ይህንን ጸሎት አብሮህ እንዲጸልይ ቡድንህን ጥራ፡

ጌታ ሆይ አንተን እንዲያውቁ
የማያምኑ ጓደኞቻችንን በሚስብ
ከባህል ጋር ተያያዥነት ባለው ዘዴ
ኢየሱስን ለማቅረብ እንሻለን።
አሜን።

እንደዚህ ባለ አውትሪች ኢየሱስ በቀላሉ መታወቅ ይችላል!


---

**የእግዚአብሄርን ግብ አስታውስ፡ ከኢየሱስ ጋር ባለ ህይወት ለዋጭ ግንኙነት በሁሉም ትምህርት ቤት ያሉ ተማሪዎችን በሙሉ ለመድረስ!**

# የአውትሪች እድል መሳሪያዎችን ፍጠር የማግኔቱ ውጤት

## ልጆችን ወደ ክርስቶስ የሚስቡ የአውትሪች ክንውኖችን መንደፍ

የማያምኑ ተማሪዎችን ወንጌሉን እንዲሰሙ መሳብ ትችላለህ:: ይህን እንዴት እንደምታደርግ የማግኔቱ ውጤት ያሳይሀል!




በማግኔቱ ውጤት ውስጥ፣ ቤን ሴንት ክሌይር ለአውትሪች ቀላል ነገር ግን ብርቱ ስልቶችንና መሳሪያዎችን ይሰጣል:: የወጣት መሪዎች ተማሪዎችንና ጓደኞቻቸውን ለክርስቶስ ለመድረስ የሚረዳቸውን የአውትሪች አጋጣሚዎች ለመሳተፍ እንዴት እንደሚያሰለጥኑ ያውቃሉ::

የፐብሊሲቲ እቅድን በማሳደግ፣ ተፈጻሚ በጀትን በማዘጋጀት፣ አውትሪቹን በማስተናገድና ውጤታማ ክትተልን በማድረግ የማግኔቱ ውጤት ወጣት በጎ ፈቃደኞችንና የተማሪ ቡድኖችን ለመምረጥና ለማዘጋጀት የደረጃ በደረጃ እቅዶችን ይሰጣል:: በአጠቃላይ ሂደቱ ወቅት መሪዎቹን የሚያራምድ አንድ የአውትሪች ክንውን እቅድ አውጪም ይካተታል::

እነዚህን ማቴርያሎች ከደብሊው ደብሊው ደብሊው ሪችአውት.ኦርግ እዘዝ

# የስራ እቅድ

በአሁኑ ጊዜ. . . የአውትሪች አጋጣሚዎችን ለመፍጠር ምን እየሰራህ ነው?

ወደፊት መሄድ . . . ከዚህ ክፍለ ጊዜ ግኝቶችህን ውሰድና ልዩ የስራ እቅድህን ንደፍ።

ለምንድን ነው ለአንተና ለመሪዎችህ የአውትሪች አጋጣሚዎችን መፍጠር አስፈላጊ የሆነው?

ምን ግቦችን ታስቀምጣለህ የአውትሪች አጋጣሚዎችን ለመፍጠር?

እነማን ናቸው ተማሪዎችህ ወደሚቀጥለው አውትሪችህ የሚጠሯቸው የተወሰኑ ኢአማኞች?

የት ነው የሚቀጥለውን የአውትሪች አጋጣሚህን የምታካሂደው?

መቼ ነው የሚቀጥለውን የአውትሪች አጋጣሚህን የምታካሂደው?

# ማጠቃለል

## ግቡ

ኢየሱስ ላይ ላተኮረ አገልግሎትህ
የእግዚአብሔርን ልዩ የስራ እቅድ ማግኘት

# ማጠቃለል

## እንዴት ነው ሁሉንም ኢየሱስ ላይ ትኩረት ያደረገ የወጣት አገልግሎት እቅድህን የምታጠቃልለው?

ኢየሱስ ላይ ያተኮረ የወጣቶች አገልግሎት ላይ ስታንጸባርቅ፣ ከኢየሱስ ህይወትና አገልግሎት  ጋር ለመመሳሰል ህይወትህና አገልግሎትህ ምን ያስፈልገዋል? ከመግቢያው (ለነዚህ አገልግሎት ንጥረ ነገሮች መጋለጥ) ወደ መተግበር (በነዚህ የአገልግሎት ነገሮች ላይ እርምጃ ለመውሰድ) ለመሄድ ምን ድርጊቶችን መውሰድ ትፈልጋለህ?

ይህንን ኖት ቡክ ለመከለስና በተለይም በስራ እቅድ ገጾች ላይ ትኩረት ለማድረግ አስፈላጊ የጊዜ ርዝመትን  ለይ:: ይህንን እንደ "የግል ራእይ ክለሳ" አስበው:: ከሚረብሽ ነገር ራቅ በልና ከእግዚአብሄር ጋር ለብቻህ ጊዜ ውሰድ:: አጠቃላይ የስራ እቅድህን የአገልግሎትህን ስልታዊ ጉዳዮችንም ጭምር በሚቀጥሉት ገጾች ላይ አስቀምጥ ::
የስራ እቅድ የማጠቃለያ ገጾችና ከእያንዳንዱ ክፍል ጊዜ የስራ እቅድ ገጾች ይበልጥ አንተን በሚረዳ መንገድ እንድትጠቀምባቸው ተካተዋል::

## የሥራ እቅድ ማጠቃለያ

ሁሉን የስራ እቅድ ገጾችህን በአንድ ገጽ ላይ ለማድረግ በሚቀጥለው ገጽ ላይ የስራ እቅድ ማጠቃለያን ተጠቀም:: እያንዳንዱን ክፍል

ጊዜ ስትከልስ፣ የምትከተላቸውን አንድ ቁልፍ መረዳትና ሶስት የስራ እርምጃዎችን እወቅ:: አንድን ድርጊት እንደ መጀመሪያህ አድርገህ አክብብ:: ልዩ ወደ ሆነ ራዕይህም እንዲመራህ ይህንን ማጠቃለያ በቀላሉ የሚያዝ አድርገው:: በተለይም . . .

- የስራ እቅድ ማጠቃለያህን ለአገልግሎትህ የየለት የጸሎቶችህ ክፍል አድርገው
- የስራ እቅድ ማጠቃለያህን ለመጻፍ ተጠቀም ከዚያም ለፓስተርህና ለመሪዎችህ የአገልግሎት ራዕይህን አቅርብ

ሁለት የስራ እቅድ ማጠቃለያዎች ተካተዋል::

## የስራ እቅድ ገጾች

ለአሁንና ለረጅም ጊዜ ኢየሱስ ላይ ላተኮረ የወጣት አገልግሎት እቅድህን በተጨማሪ ለመከለስና ለመቅረጽ፣ የስራ እቅድ ገጾችን እንደ ዎርክ ሽት/ መስሪያ ገጾች ተጠቀም:: የአገልግሎት ግቦችህን ለሚቀጥለው አመት እንደገና ስትመዝን እነዚህ ገጾች የተለየ ዋጋ

ይኖራቸዋል።

# የስራ እቅድ ማጠቃለያ

| ከኢየሱስ ጋር ወደ ጠለቀ ነገር መሄድ | |
|---|---|
| ቁልፍ መረዳት | የስራ እርምጃዎች<br>1.<br>2.<br>3. |
| **በፍላጎት መጸለይ** | |
| ቁልፍ መረዳት | የስራ እርምጃዎች<br>1.<br>2.<br>3. |
| **መሪዎችን መገንባት** | |
| ቁልፍ መረዳት | የስራ እርምጃዎች<br>1.<br>2.<br>3. |
| **ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር ማድረግ** | |
| ቁልፍ መረዳት | የስራ እርምጃዎች<br>1.<br>2.<br>3. |
| **ባህሉን ዘልቆ መግባት** | |
| ቁልፍ መረዳት | የስራ እርምጃዎች<br>1.<br>2.<br>3. |
| **የመድረስ አጋጣሚዎችን መፍጠር** | |

| | |
|---|---|
| ቁልፍ መረዳት | የስራ እርምጃዎች<br>1.<br>2.<br>3. |

## የስራ እቅድ ማጠቃለያ

| ከኢየሱስ ጋር ወደ ጠለቀ ነገር መሄድ | |
|---|---|
| ቁልፍ መረዳት | የስራ እርምጃዎች<br>1.<br>2.<br>3. |
| በፍላጎት መጸለይ | |
| ቁልፍ መረዳት | የስራ እርምጃዎች<br>1.<br>2.<br>3. |
| መሪዎችን መገንባት | |
| ቁልፍ መረዳት | የስራ እርምጃዎች<br>1.<br>2.<br>3. |
| ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር ማድረግ | |
| ቁልፍ መረዳት | የስራ እርምጃዎች<br>1.<br>2.<br>3. |
| ባህሉን ዘልቆ መግባት | |
| ቁልፍ መረዳት | የስራ እርምጃዎች<br>1.<br>2.<br>3. |
| የመድረስ አጋጣሚዎችን መፍጠር | |

ማጠቃለል

| ቁልፍ መረዳት | የስራ እርምጃዎች<br>1.<br>2.<br>3. |
|---|---|

# ከክርስቶስ ጋር ወደ ጠለቀ ነገር የመሄድ የስራ እቅድ

አሁን . . . ወደ ክርስቶስ ጥልቅ ነገር ለመሄድ ምን እየደረግህ ነው?

ወደፊት መሄድ . . . ከዚህ ክፍል ጊዜ ግኝቶችህን ውሰድና ልዩ የሆነ የስራ እቅድህን ንደፍ::

ስምንድን ነው ክክርስቶስ ጋር ወደ ጠለቀ ህብረት ለመሄድ ያስፈለግህ?

ምን ግብ ነው የምታስቀምጠው ክክርስቶስ ጋር ወደ ጠለቀ ህብረተ ለመጓዝ ?

ማን ነው ክከርስቶስ ጋር ወደ ጠለቀ ህብረት ለመሄድ ተጠያቂ የሚያደርግህ ?

የት ነው ወደ ጠለቀ ህብረት ለመሄድ ከክርስቶስ ጋር የምትገናኘው ?

መቼ ነው ወደ ጠለቀ ህብረት ለመሄድ ከክርስቶስ ጋር መቼ ነው ካርብ አውት የምታደርገው?

# በፍላጎት የመጸለይ የስራ እቅድ

በአሁኑ ጊዜ... በፍቅር ለመጸለይ ምን እያደረግህ ነው?

ወደፊት መሄድ . . . በፍቅር ክፍለ ጊዜ ያገኘሃቸውን ግኝቶች ውሰድና ልዩ የሆነ የስራ እቅድህን ንደፍ።

ስምንድን ነው - በፍቅር መጸለይ ላንተና ለሌሎች አገልግሎች አስፈላጊ የሆነው ?

ምን ግብን ነው በአገልግሎህ ለራስህና ለሌሎች በፍቅር ለመጸለይ የምታስቀምጠው?

ማን ነው በሶስትዮሽ ጸሎትህ አብሮህ የሚሆነው ደግሞስ በአገልግሎትህ ሶስትዮሽ ጸሎትን ማን ይጀምራል?

የት ነው ለመጸለይ የሶስትዮሽ ጸሎትህ የሚገኘው?

መቼ ነው - የሶስትዮሽ ጸሎት የሚገናኘው?

# መሪዎችን የመገንባት የስራ እቅድ

በአሁኑ ገዜ. . . መሪዎችን ለመግንባት ምን እደረግህ ነው?

ወደ ፊት መሄድ . . . ከዚህ ክፍለ ጊዜ ግኝትህን ውሰድና ልዩ የሆነ የስራ እቅድህን ዲዛይን አድርግ::

ለምንድን ነው መሪዎችን መገንባት አስፈላጊ የሆነው ?

ምን ግብ ነው መሪዎችን ለማብቃት የምታስቀምጠው ?

እነማን ናቸው የምታፈራቸው መሪዎች ?

የት ነው ከአመራር ቡድን ጋር ለመሰብሰብ የምትገናኘው?

መቼ ነው - ከአመራር ቡድን ጋር ለመሰብስብ የምትጀምረውና የምትቀጥለው ?

# ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር የማድረግ የስራ እቅድ

በአሁኑ ጊዜ . . . ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር ለማድረግ ምን እያደረግህ ነው?

ወደፊት መሄድ -- ከዚህ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ያገኘሽውን ውሰድና ልዩ የሆነ የስራ እቅድህን ዲዛይን አድርግ

ስምንድን ነው ለአንተ ፣ ለበጎ ፈቃደኞችህ፣ እና ለወላጆች ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር ማድረግ አስፈላጊ የሆነው?

ምን ግቦችን ነው የምታስቀምጠው ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር ለማድረግ?

እነማን ናቸው ደቀ መዝሙር የምታደርጋቸው ተማሪዎች ደግሞስ ሌሎችን ደቀ መዝሙር የሚያደርጉ መሪዎች እነማን ናቸው?

የትነው የምትገናኙት ከደቀ መዝሙር ቡድን ጋር?

መቼ ነው ከደቀ መዝሙር ቡድን ጋር መሰብሰብ የምትጀምረውና የምትቀጥለው?

# ባህልን ዘልቆ የመግባት የስራ እቅድ

በአሁኑ ጊዜ. . ባህሉን ዘልቀህ ለመግባት ምን እያደረግህ ነው?

ወደፊት መሄድ . . . ከዚህ ክፍለ ጊዜ ግኝቶችህን ውሰድና ልዩ የሥራ እቅድህን ዲዛይን አድርግ::

ስምንድን ነው ባህሉን ዘልቆ መግባት ለአንተና ለመሪዎችህ አስፈላጊ የሆነው?

ምን ግቦችን ነው ባህልን ዘልቆ ለመግባት የምታስቀምጠው?

ማነው የተወሰነ የታቀደ ተደራሲህ?

የት ነው ባህሉን ዘልቀህ የምትገባው?

መቼ ነው ባህሉን ዘልቀህ የምትገባው?

# የመድረስ አጋጣሚዎችን የመፍጠር የስራ እቅድ

በአሁኑ ጊዜ . . . የአውትሪች አጋጣሚዎችን ለመፍጠር ምን እየሰራህ ነው?

ወደፊት መሄድ . . . ከዚህ ክፍለ ጊዜ ግኝቶችህን ውሰድና ልዩ የስራ እቅድህን ንደፍ።

ለምንድን ነው ለአንተና ለመሪዎችህ የአውትሪች አጋጣሚዎችን መፍጠር አስፈላጊ የሆነው?

ምን ግቦችን ታስቀምጣለህ የአውትሪች አጋጣሚዎችን ለመፍጠር?

እነማን ናቸው ተማሪዎችህ ወደሚቀጥለው አውትሪችህ የሚጠሯቸው የተወሰኑ ኢአማኞች?

የት ነው የሚቀጥለውን የአውትሪች አጋጣሚህን የምታካሂደው?

መቼ ነው የሚቀጥለውን የአውትሪች አጋጣሚህን የምታካሂደው?

# ብዙ ጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## ግቡ

ኢየሱስ ላይ ላተኮረ አገልግሎትህ
የእግዚአብሔርን ልዩ የስራ እቅድ ማግኘት

# ብዙ ጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## ኢየሱስ ላይ ትኩረት ስላደረገ አገልግሎት ብዙ ጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ጥያቄዎች ሁሉ በህይወትህና በአገልግሎትህ የሚገጥሙህን አስቸኳይና አስፈላጊ ጉዳዮች ላይ ያተኩራሉ። ጥልቀት ያላቸው መልሶችና ዝርዝሮች ከ “መሳሪያዎች” ስራ በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ በተጠቀሙ ማቴርያሎች ውስጥ መገኘት ይችላሉ። እነዚህን ማቴርያች እዘዝና ተጠቀም።

ማቴርያሎቹን ለማዘዝ ወደ . . . ሂድ

## በክርስቶስ ወደሚገኝ ጥልቅ ነገር ሂድ/ በፍላጎት ጸልይ

### 1. ይቅር ተብዬ እንደሆነ እንዴት አውቃለሁ?

የይቅርታ እጥረት በእኛ ውስጥ የእግዚአብሔርን ፍቅር መፍሰስና ህይወትን ያግዳል። ብዙ ጊዜ ይቅርታን መቀበል አስቸጋሪ ነው። እግዚአብሔር ግን ይቅርታን በነጻ ይሰጣል። ኢየሱስ በድፍረት ሽባውን ሰው ሀጢአቱ ይቅር እንደተባለ ነገረው። ሀጢአትን ይቅር የማለት ስልጣን እንዳለው ለማረጋገጥ፣ ኢየሱስ ፈወሰው (ማር 2:1-13)። እግዚአብሄር ይህን የተስፋ ቃል ሰጥቷል፡ “በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።” (1 ዮሐ 1:9)። ይቅር መባል ከፈልግን ሀጢአታችንን እንናዘዛለን በመስቀል ላይ ኢየሱስ ስለ ሀጢአታችን በከፈለው ነገር እግዚአብሄርም ይደመስሳቸዋል።

ብዙውን ጊዜ ችግሩ ራሳችንን ይቅር ለማለት መቸገራችን ነው:: ሀጢአታችንን እንናዘዛለን ነገር ግን ጥፋታችንን እንይዛለን:: ክርስቶ ሲሞት ለሀጢአታችን ብቻ አይደለም ለጥፋታችንም ነው የሞተው:: ሀጢታችንና ጥፋታችን እንዲሄድ ማድረግ አለብን **“ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ፥ እንዲሁ ኃጢአታችንን ከእኛ አራቀ።”** (መዝ 103፡12)::

## 2. የሆነን ሰው ይቅር እንዲለኝ የምጠይቀው እንዴት ነው ደግሞስ የሆነን ሰው ይቅር የምለው እንዴት ነው?

**ይቅርታን መጠየቅ።** መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሄር እኛን ይቅር ስለማለቱ ይናገራል:: ይቅርታን ስንቀበልና ስንሰጥ ከእግዚአብሄር ጋር ብቻ አይደለም ህብረታችንን የምናድሰው የምናደርገው ከሌሎችም ሰዎች ጋር ያለንንም ህብረት ጭምር እንጂ:: ከሌላ ሰው ይቅርታ ለመጠየቅ፣ በማቴ 5፡23-24 የኢየሱሰን ትእዛዝ ተከተል::

- አስታውስ:: ወንድምህ በአንተ ላይ የሆነ ነገር አለውን? ጌታን ጠይቅ ደግሞም የተበላሸ ግንኙነት ካንተ ጋር ያለውን ሰው ያሳይሃል

- ታረቅ:: በትህትናና በንስሀ መንፈስ፣ ወደ ሌላ ሰው ሂድና ይቅርታ ጠይቅ:: ይቅርታን በተገቢ ሁኔታ መጠየቅና* መግለጽን በጣም አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ:: “አዝናለሁ” “ልክ ካልነበርኩ” ብሎ መናገር ተገቢ አይደለም እንዲሁ “ተሳስቻለሁ” በል:: በግልጽ የተሳሳትከውን ነገር ተናገር:: ከዚያም “ይቅር ትለኛለህን?” ብለህ ጠይቅ:: ያ ሌላው ሰው ምላሽ የሚሰጥበትን ጠንካራ መሠረት ይሰጣል::

**ይቅርታን መስጠት፡** የበደለህን ሰው ይቅር ለማለት ማቴ 7፡ 35 እና 18፡ 15-18 ውስጥ ያለውን የኢየሱስን ትዕዛዝ ተከተል:: የሆነ ሰው ሲጎዳህ በመጀመሪያ በውስጥህ ካለ ፍርሀት፣ ቁጣና መራርነት ጋር ዲል ማድረግህን ርግጠኛ

ሁን፡፡ ለሌላው ሰው ይቅርታን በመስጠት እግዚአብሔር “ከአይንህ ምሶሶ እንዲያወጣልህ” ጠይቅ፡፡ ያንን ለማድረግ ከወንበርህ ፊት ለፊት ባዶ ወንበር ላይ እንደተቀመጠ አስብ፡፡ ጉዳትህን በሙሉ ለዚያ ሰው ግለጥለት፡፡ ከዚያም “ይቅር ብዬሀለሁ ምክንያቱም . . .” በማለት ይቅርታን አድርግ፡፡ ከዚያም ስለጉዳዩ ለማውራት ወደዛ ሰው ስትሄድ ከውስጥህ በሚፈስ በክርስቶስ ፍቅር መሄድ ትችላለህ ምክንያቱም በልብህ ውስጥ ጉዳዩ ተቃሏል፡፡ ይቅርታን መቀበልና መስጠት ትንሽ ነገር አይደለም፡፡ ለእንዳንዶች፣ ማድረግ ያ ከባድና በጣም አስቸጋሪ ድረጊት ነው፡፡ ቢሆንም ግን እግዚአብሔር በኢየሱስ ይቅርታውን ሰጥቶናል፡፡ እርሱ ይቅር ስለሚለን፣ ከሌሎች ይቅርታ መስጠት ብቻ ሳይሆን ከነርሱም ለመቀበል አስደናቂ እድል አለን፡፡

## 3. በህይወቴ ልክ ያልሆነ ባህሪን የምቀይረው እንዴት ነው?

ራሳችንን አንለውጥም፤ እግዚአብሄር ብቻ ነው እኛን የሚለውጠን፡፡ ይህን ለመማር ለእኛ አስቸጋሪ የሆነው ለምንድን ነው? ገላ 2፡ 20-21 ጠባያችንን እንዴት ማየት እንዳለብን ትክክለኛ አቅጣጫን ያሳየናል፡፡ ቁ. 21 ብዙ ጊዜ ባህሪአችንን ለመለወጥ የምናደርገውን ነገር ያሳያል፡፡ “የእግዚአብሄርን ጸጋ” ወደ ጎን እናደርጋለን ምክንያቱም ጉዳዩን በገዛ ራሳችን መያዝ እንደምንችል እናስባለን፡፡ ያን ስናደርግ ግን እግዚአብሔርን “ክርስቶስ ለምንም አልሞተም” እያልን ነው፡፡ ባህሪን ለመለወጥ ዋናው ነገር “የእግዚአብሔር ጸጋ” ነው፡፡ ሲተረጎም በመስቀሉና በትንሳኤው አማካኝነት በአንተ ውስጥ የእግዚአብሄር ችሎታ ማለት ነው”፡፡ በተግባር ገላ 2፡20 እዚህ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ ጠባያችንን ለመለወጥ ሁለት ጠቃሚ እውነታዎችን እንቀበላለን፡

- ክርስቶስ ሲሞት እኔም ሞቻለሁ፡፡ “ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ፡፡”
- ክርስቶስ ሲነሳ፣ ተነስቻለሁ፡፡ ከሙታን በክርስቶስ መነሳትና በመንፈስ ቅዱስ መምጣት አሁን “ክርስቶስ በእኔ ይኖራል፡፡”

በውስጣችን በሚኖረው በመንፈሱ ክርስቶስ ከእኛ ጋር አለ፡፡

ስለዚህ አሁን ህይወታችንን እንዴት እንኖራለን፡፡ “በእግዚአብሄር ልጅ ባለ እምነታችን፡፡” መታመናችንን በእግዚአብሄር የተስፋ ቃል ላይ እናደርጋለን፡ እኔ ሞቻለሁ ስለዚህ ምንንም ነገር መቀየር አልችልም፡፡ ነገር ግን ክርስቶስ በእኔ ይኖራል ስለዚህ ሁሉንም ነገር ይለውጣል፡፡ በትክክል እንድንኖር ኢየሱስ “ጻድቃን” (ከርሱ ጋር በትክክል ህብረት የምናደርግ) ያደርገናል፡፡

## 4. በህይወቴ የኃላ ችግርን ማቃለል ካልቻልኩ ምን ይሆናል?

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ከዘር ማንዘር የመጣ “ህይወትን የሚጫኑ ችግሮች” ይኖራቸዋል፡፡ እንዲህ ያለ ምሽግ የሰራ ሀጢአት ችግሩን ለማቃለል የክርስቶስን ሀብቶች እንዴት መጠቀም እንዳለብህ እንዲረዳህ ሌላ ሰውን ይፈልጋል፡፡

የሚረዳህን ትክክለኛ ሰው ለማግኘት፡

- መንፈስ ቅዱስ የመጨረሻ አማካሪህ እንደሆነ አስታውስ (ዮሐ 14፡15-18)
- እንዲያማክርህ ትክክለኛ ሰው እንዲሰጥህ ጌታን ጠይቅ
- ሰዋዊ ሳይኮሎጂ ሳይሆን በትክክል ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ ዘዴ ያለውን አማካሪ ፈልግ
- ጌታን የተሟላ ተሀድሶን፣ ፈውስና ነጻነትን ጠይቅ (ዮሐ 8፡32፣36)

## 5. እግዚአብሔርን የተሻለ እንዳውቅ ምን ተግባራዊ እርምጃዎችን መውሰድ እችላለሁ?

ከክርስቶስ ጋር የቀረበ ህብረት የመጨረሻ ግባችን ነው፡፡ ውስጣዊ ህይወታችን ከህያው ውሀ ምንጭ ይረካል (ዮሐ 4፡13)፡፡ የምናደርገው ነገር ሁሉ ከሆንነው ነገር ነው የሚወጣው፡፡ በዚህ ምክንያት በኢየሱስ እና በእኛ ውስጥ ማን በመሆኑ ላይ ትኩረት ማድረግ አለብን፡፡
ከጊዜ ወደ ጊዜ በእግዚአብሔር ህልውና መኖርን ተለማመድ፡፡ ይህን የማድረግ አንድ መንገድ “በመንፈሳዊ አተነፋፈስ” አማካኝነት ነው፡፡

ልክ በመተንፈስ አየር ማስወጣትና ማስገባት በአካል በህይወት እንዳቆይን፣ ከክርስቶስም ጋር ያንን ህብረት ባለማቋረጥ በመንፈስ በመተንፈስ እናድሳለን:: ሀጢአታችንን እንናዘዛለን (ማውጣት):: በኤፌ 5፡18 መሠረት "መንፈሳዊ መተንፈስን" መለማመድ ብዙውን ጊዜ በእግዚአብሄር ህልውና እንዳለን እንድናውቅ ይረዳናል:: እነዚህ ስርአቶችና ልማዶች ኢየሱስን እንድናውቅና የእርሱ ህይወት ወደ ህይወታችን፣ በህይወታችን እና ከህይወታችን እንዲፈስ ይረዳናል::

- በየቀኑ ለብቻህ ቢያንስ ለ30 ደቂቃዎች ከእርሱ ጋር አሳልፍ
- በፍላጎት መጸለይ ክፍለ ጊዜ የ3ዮሽ የጸሎት ስልትህ አማካኝነት መከተልህን ቀጥል
- ቅዱሳት መጻህፍትን በቃል አጥና:: ይህንን ማድረግ የእግዚአብሄርን ሀሳቦች እንድታስብ ያደርግሃል:: በአንድ ሳምንት አንድ ጥቅስ በማስታወስ ጀምር:: ከዚያም ጥቅሶችን ወደ ማስታወስ ልማድ ስትገዝ እየጨመርክ ሂድ
- የምታስታውሳቸውን ጥቅሶች ወደ አግዚአብሄር ጸልይ
- ለጸሎትና ለጾም ግማሽ ወይም አንድ ቀን ለይ
- ከክርስቶስ ጋር ያለህ ህብረት ላይ የሚያነጣጥሩ በመንፈስ የተመሩ መጽሐፎችን አንብብ በተለይም እንደ ማይ አትሞስት ፎረ ሂዝ ሀየስት ያሉ ክላሲካሎችን:: በቀን አንድ ምዕራፍ የማንበብ ግብን በማስቀመጥ ሁልጊዜ ካንተ ጋር መጽሐፍን ውሰድ

## መሪዎችን አፍራ

### 1. ብቃት ላላቸው የወጣት መሪዎች ሀላፊነት የምሰጠው እንዴት ነው?

ብዙ መደበኛ ሰዎች ለመምራት ብቃት እንደሌላቸው በጣም ይሰማቸዋል በተለይም በወጣቶች አገልግሎት ውስጥ:: ብዙ ጊዜ ሀፍረት ይሰማቸዋል:: ሀላፊነት በመስጠት ጊዜ የሰዎችን ፍርሀት መተባበር አስፈለጊ ነው:: ከልጆች ጋር ለመስራት ኦልሬዲ የሰለጠኑና

ክህሎት ያላቸውን ሰዎች እየፈለግህ እንዳልሆነ ይወቁ:: ይልቁንም፣ የአመራር አቅምና ለመማር መሻት  ያላቸውን ሰዎች እየፈለግህ እንደሆነ እንጂ:: ፋት (FAT) ሰዎችን እየፈለግህ ነው - ፌዝፉል (የታመኑ)፣ አቬሌብል (የሚገኙ) እና ቲቼብል (መማር የሚችሉ):: ለወጣት አገልግሎት  ልታሰለጥናቸው እንደሆነ ይወቁ::
መሪዎችን ለመሾም  የላቀው መንገድ  እያንዳንዱን ሰው በተናጠል ማቅረብ ነው:: ለወጣት አገልግሎት የአመራር ቡድንን እየጀመርኩ ነው  ብለህ  ንገራቸው::  ከክርስቶስና  ከእርስ  በርሳችን  ጋር በህብረታችን ለማደግ እንዲሁም ኢየሱስ ችግሮችን በሚፈታበት መንገድ የልጆችን ችግር ለመፍታት በቋሚነት እንሰበሰባለን::

ከእኔ ጋር አብረህ ለመሆን ትጸልያለህን?  ይህ ስብሰባ ስለ ወጣት አገልግሎት ለማውራት  እንዳልሆነ በአጽኖት ተናገር:: በግልና በአገልግሎት እድገታቸው እነርሱን የመንከባከብ ጊዜ ነው እንጂ:: ምላሻቸውን ለማወቅ በጥቂት ቀን  አረጋግጥ::
ማስታወሻ፡ እንደ በጎ አድራጎት ሰራተኛ፣ ወላጆች ከሁሉም የበለጠ አቅም አላቸው:: ምክንያቱም በራሳቸው ልጆች ላይ የተሰጠ  ፋላጎት ስላላቸው:: የአመራር ቡድንህን ስታዋቅር ለወላጆች ሀላፊነት በመስጠት ላይ ትኩረት አድርግ::

## 2. ሁሉም የወጣት መሪዎቼ በአመራር ቡድን ውስጥ እንዲሳተፉ እፈልጋለሁን?

መጀመሪያ ላይ አትፈልግም:: በመጀመሪያ፣ የተነቃቁ  ሰዎችን-ከልብ  መሳተፍ  የሚፈልጉትን  ሰዎች  ብቻ  ትፈልጋለህ:: አጠቃላዩን የአገልግሎት ሁኔታ ይቋቋማሉ:: በአመራር ቡድን ላይ ያልተነቃቁ መሪዎች ካሉህ፣ ለቡድኑ የቀሩ ሰዎች የፍላጎቱን ደረጃ ያወርዱታል:: ይህ በአጠቃላዩ አገልግሎት ውስጥ ይጠራል:: ሰዎችን ግን ካነቃቃህ፣ ለልጆቹ አዎንታዊ ሁኔታን ያስቀምጣሉ:: በኋላ፣ ብዙ መሪዎችን ስትሾም፣ እንደገና የተነቃቁትን መሾም ትችላለህ:: በጊዜ ብዛት መሪዎችህ ሁሉም የተነቃቁና የሰለጠኑ ይሆናሉ:: በዚያን ጊዜ በዚያ የአመራር ቡድን ውስጥ መሳተፍ ከመስፈርት ይልቅ በረከት እንደሆነ ሰዎች ይሰማቸዋል::

### 3. የአመራር ቡድኑን ከጀመርን በኋላ አዲስ ሰዎች ሊቀላቀሉ ይችላሉን?

ስለ አመራር ቡድኑ ለመላው ቤተ ክርስቲያን ማስታወቂያን ከተናገርክና፣ የራእይ ክለሳ እና/ወይም ተቀዳሚ ስብሰባን ከያዝክ፣ ቡድኑ ከጀመረ በኋላ የሰው መቀላቀል ብዙም አይደለም። ከመጀመሪያው ወይም ከሁለተኛው ክፍለ ጊዜ በኋላ ቡድኑን ዝጋ።ከዚያ በኋላ የአመራር ቡድኑን ለመቀላቀል ከፈለጉ፣ ቡድኑን እየናፈቁ ከመሆናቸው የተነሳ፣ የመጀመሪያዎቹ 12 ሳምንታት እስኪፈጸሙ ድረስ እንዲጠብቁ ጠይቃቸው። በዚያ ጊዜ መሪዎችን በመገንባት ሲሪስ ውስጥ በመጀመሪያው መጽሐፍ ከኢየሱስ ጋር የግል አካሄድ አማካኝነት እንደገና ሀላፊነት ስጥ ደግሞም ሌላ ቡድንን ውሰድ። የመሪዎችን ቁጥር ለማሳደግ ይህንን በተደጋጋሚ ማድረግ ትችላለህ።

የሰፊ ቡድንን በአንድ አቅጣጫ የመሄድ ትርጉም ለመጠበቅ፣ በአንድ ስፍራ ከሁሉም መሪዎች ጋር ተሰብሰብ። ከዚያም በራስህ ክፍለ ጊዜ፣ በትናንሽ የቡድን ስብስቦች ልታስቀምጣቸው ትችላለህ። አጠቃይ ማስታወቂያዎችን እና ሁሉንም አቅጣጫዎችን ለመሸፈን በእያንዳንዱ ሳምንት ለጥቂት ደቂቃዎች በትልቁ ቡድን ውስጥ ሁሉን ሰው በአንድ ላይ ሰብስብ፣ ከዚያም ወደ ትናንሽ የአመራር ቡድን ክፍሎች ከፋፍላቸው፤ የበሰሉ መሪዎችህን አዲስ ቡድን እንዲመሩ አሰልጥናቸው። ሌላው አማራጭ እያንዳንዱ ቡድን በሳምንቱ በተለያየ ጊዜና ስፍራ መሰብሰብ ነው።

### 4. የሆነ ሰው ለአመራር ቡድኑ መሰጠቱን ባይከተል ምን አደርጋሁ?

ይህንን ችግር የማስወገድ ዘዴ ራዕዩንና አቅጣጫውን በግልጽ ፊት ለፊት ማቅረብ ነው። ሰዎችን በቡድን ሀላፊነት ከመስጠት ይልቅ በተናጠል ማድረግ ይህንን በውጤታማ መንገድ ማድረግ ትችላለህ። የግል መሰጠትን በሚገባ ግለጽለቸው (መሪዎችን በመገንባት ሲሪስ ውስጥ በእያንዳንዱ በ3 መፅሐፍ ገጽ 11 ላይ አግኝ)። ይህንን በማድረግ እያንዳንዱ ሰው ምን እንደተካተተ ያውቃል።

በቡድኑ ውስጥ የሆነ ሰው ወይም ቡድኑ በአጠቃላይ እየታገለ ከሆነ ግልጽ ሁን። ከቡድኑ መሀል ወይም ያንን ሰው ችግሩ ምን እንደሆነ ጠይቀው። ብዙውን ጊዜ ግለሰቦች በግል ህይወታቸው ናፍቆት ወይም ትኩረት እንዲያጡ ካደረጋቸው ነገር ጋር ዲል እያደረጉ ነው። በችግራቸው እርዳቸው። ምናልባት የሆነ ሰው ከመንገድ እየወጣ ነው። ጉዳዮቹ ምን እንደሆኑ እንዲወስን እርዳው ደግሞም ተመልሶ ወደ መስመሩ እንዴት እንደሚገባም እርዳው። ምናልባት ከቡድኑ ጋር ተቀላቅሎ ደግሞም ከልጆች ጋር መስራት እንደማይወድ ተረድቶ ሊሆን ይችላል። እንዲወጣ አድርገው። ብዘውን ገዜ ሰዎች የቤት ስራ ሳይሰሩ ሲቀሩ፣ ከቤት ስራ ጋር የተያያዘ ምንም ነገር የለም። ጉዳዩ የግል ጉዳይ ነው። መሪ እንደ መሆንህ መጠን አሳዳጊ መሪውን በዚህ ላይ እንዲሰራ እርዳው። በነርሱ ህይወት ውስጥ የግል ተሳትፎህ “ኦቨር ዘ ሀምፕ” / ከእድገቱ በላይ ያደርጋቸዋል ስለዚህም ወደፊት መሄድ ይችላሉ።

## 5. በጎ ፈቃደኛ ከልጆች ጋር በሚገባ ባይሰራስ?

አንድ ሰው ወደ ወጣት አገልግሎት ከተጠራና በጎ ፈቃደኛ ከሆነ፣ ያ ሰው እንዲያገልግል ቦታ ስጠው። በአመራር ቡድኑ አውድ ውስጥ ያንን ሰው፣ ጥሪውን፣ መንፈሳዊ ስጦታውን፣ ክህሎቱንና የግንኙነት ችሎታዎቹን ለመመልከት እድል ታገኛለህ። ያ ሰው በጣም ሊረዳ የሚችልበትን መንገድ አግኝ። ያ ሰው ያለ ቦታው ተቀምጦ ሊሆን ይችላል። እርሱ የሚወደው ቪድዮ መስራት ሲሆን እያስተማረ ሊሆን ይችላል። ችሎታውን ይበልጥ ሊጠቀምበት በሚችለው ቦታ ላይ አስቀምጠው። ሰውየው “ከውሀ የወጣ አሳ” ከሆነ ወደ ልጆች ሲመጣ፣ ከወጣቶች አገልግሎት በተጨማሪ በቤተ ክርስቲያን ሌላ ስፍራ ላይ እንዲሳተፍ ውሰደው።
ችግሩ የአመለካከት ከሆነ፣ ያ ሌላ ጉዳይ ነው። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች የሀይል ጌም ለመጫወት ወይም አንተን ለመጠምዘዝ ሊሞክሩ ይችላሉ። በዚያን ጊዜ ከቤተ ክርስቲያንህ አመራር ጋር ተነጋገርበት ደግሞም በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ ተጋፈጠው።
ለማጠቃለል፣ የአንተ ስራ እያንዳንዱ ሰው በክርስቶስ አካል ውስጥ የራሱን ትክክለኛ ስፍራ እንዲያገኝ መርዳት ነው።

# ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር አድርግ

## 1. የደቀ መዝሙርነትን ቡድን ማን ነው መምራት ያለበት?

ይህንን ጥያቄ የምትመልስበት መንገድ ለተማሪዎቸህ ያለህን አገልግሎት መነሳሳትና ጥልቀት ላይ በዋናነት ተጽኖ ያመጣል። በሁኔታህ የተለየ መሆን ላይ ተመስርተህ በጥንቃቄ መልስ። የሚከተሉት ተግባራዊ ሀሳቦች ይምሩህ።

በአመራር ቡድንህ ውስጥ ያሉ ሰዎች ቡድኖችን መምራት ያለባቸው ሰዎች እንደሆኑ በአእምሮህ አስቀምጥ። ያ ትርጉም ያለው ነገር ነው ምክንያቱም በአመራር ቡድኑ ስብሰባ ላይ “የደቀ መዝሙርነትን ቡድን” እየተለማመዱ ስለሆነ። ለእድገት ትክክለኛውን ሁኔታ መፍጠርን የሚያውቁ እነርሱ ናቸው።

በአመራር ቡድኑ ውስጥ ያሉ ሁሉም ሰዎች የደቀ መዝሙርነት ቡድንን እንዲመሩ አትገፋፋ። በወጣት አገልግሎት ውስጥ ያ ጥሪአቸው ላይሆን ይችላል። እያንዳንዱ ሰው አንድ ቡድንን እንዲመራ ልታበረታታ ትችላለህ ነገር ግን ከዚያ በኋላ ፍላጎት ላላቸውና ለበቁ ሰዎች ብቻ አንድ ቡድንን ስጥ።

በትንሽ ጀምር። በአንድ ወይም በሁለት ቡድን ጀምር - ምናልባት አንድ ቡድን ለወንዶች አንድ ቡድን ለሴቶች። ከቡድኖቹ አንዱን በኋላ ላይ የአመራር ቡድንን ልክ ለማስቀመጥ ምራ። ይህንን ማድረግ ብዙ የልጆችን ቁጥር እንድታካትት የደቀ መዝሙርነት አገልግሎትህን እንዴት ማዋቀር እንደምትፈልግ ጥቂት ጊዜና ተሞክሮ ይሰጥሃል። ጊዜ ከፈቀደ ትይዩ በሆነ የጊዜ ማህደር የደቀ መዝሙርነት ቡድንን እና የአመራር ቡድንን ምራ።
ለአሁንና ለወደፊት የደቀ መዝሙርነት ቡድኖች መሪዎችን ማፍራትህን ቀጥል። በአመራር ቡድን ሂደት ውስጥ እንደሚያልፉ ሰዎች ልጆችን ደቀ መዝሙር እንዲያደርጉ አበረታታቸው። አንድ ቡድን ስጣቸውና እንዲጀምሩ አድርግ። ይህንን ዘዴ በመጠቀም እየሰፋ የሚሄድ የወጣት መሪዎችን ቁጥር በክርስቶስ እያደጉ

የሚሄዱና ሌሎችን የሚመሩ የተማሪ መሪዎችን ታስፋፋለህ። እነዚህ ደቀ መዝሙር የሆኑ ወጣቶችና ተማሪዎች እንደ ዋናህ ሆነው ያገለግላሉ። በኋላ፣ እያደጉ ያሉ ተማሪዎችህ ወጣት ተማሪዎችን ደቀ መዝሙር ያደርጋሉ።
ማስታወሻ: ወላጆች # 1 የወጣት መሪዎችህ ናቸው። ተማሪዎችህን ደቀ መዝሙር ለማድረግ በተሳታፊ ወላጆችህ ዙሪያ ስልትህን ገንባ። የገዛ ልጆቻቸውንና የልጆቻቸውን ጓደኞች ደቀ መዝሙር እንዲያደርጉ ወላጆችህን አሰልጥን። የወላጆች ነዳጅ ሥልጠናውንና ወላጆችን በደቀ መዝሙርነት ለማሳተፍ የሚያስፈልገውን ማቴርያሎች ይሰጥሃል።

## 2. የደቀ መዝሙርነት ቡድን ክፍል እንዲሆኑ ተማሪዎችን የምፈታተነው እንዴት ነው?

ለደቀ መዝሙርነት ትክክለኛ እጩዎች ኢየሱስን የተራቡ ልጆች ናቸው። በጣም ከማይጠበቁ ልጆች ጥቂቶቹ ምላሽ እንደሚሰጡ ታያለህ። ብዙውን ጊዜ ኢየሱስን ለማወቅ ያላቸው መሻት በመልካቸው ወይም በጠባያቸው ይሸፈናል። እውነት ነው ብዙዎቹ የበሰሉ አይደሉም። ነገር ግን ለዛ ነው በቡድኑ ውስጥ የተገኙት - በክርስቶስ ለማደግ። ባሉበት ቦታ ላይ ተቀበላቸው ደግሞም መሆን ወደ ሚፈልጉበት ስፍራ ውሰዳቸው። ያ ደግሞ የሚጀምረው የደቀ መዝሙሩ ቡድን እንዲሆን እያንዳንዱን በመገዳደር ነው።

በቻሌንጆችህ ውስጥ እነዚህን አስፈላጊ ነጥቦች ከግንዛቤ አስገባ።

- ያለውን እድል ለሁሉም የወጣት ቡድን አቅርብ። ከዚያም ግለሰብን ወደ መቅጠር ሂድ። አቅም እንዳላቸው የምታያቸው አንዳንድ ልጆች ለአደባባይ ቻሌንጅ ምላሽ የሰጡ ላይሆኑ ይችላሉ። በተናጠል ወደ እነርሱ ሂድና ቻሌንጅ አድርጋቸው።
- ከእያንዳንዱ ተማሪ ጋር የግል የፊት ለፊት ስብሰባ አድርግ። ኢየሱስን መከተል ገጽ 11 ላይ ባለው የግል መስጠት ላይ በመሄድ ዋጋን አስቀምጥ።
- ደቀ መዝሙር የመደረግ ትሩፋቶችን ንገራቸው ደግሞም ከራስህ ህይወት ወይም ደቀ መዝሙር ከተደረጉ ሌሎች ልጆች ህይወት ጥቂት ምሳሌዎችን ስጣቸው።

- በመጀመሪያ ስብሰባህ፣ የግል መሠጠትን አስፈርማቸው:: ከዚያም መጽሐፍቶቹን ለሁሉም አስተላልፍ የእርስበርሳቸው መጽሐፍትም ላይ መፈረም እንዲችሉ:: ይህ ተጠሪነትን ይገነባል:: የጁኒየር ከፍተኛ ቡድን ካለህ ወላጆችም እንዲፈርሙ አድርግ ምክንያቱም ወደ ቡድኑ ስብሰባ ልቻቸውን ሊያደርሱ ስለሚችሉ::

## 3. ተማሪዎች የቤት ስራቸውን ባይሰሩስ

ልጆችህን ቻሌንጅ ለማድረግ ተገቢዎቹን እርምጃዎች ከተከታተልክ፣ ብዙዎቹ እነዚህን ጉዳዮች ከመጀመርህ በፊት ይቀበላሉ:: (ያለፈውን ጥያቄ ተመልከት):: ካልሆነ ግን ተማሪዎችን በሌላ መንገዶች ማነቃቃት ትችላለህ:: የነዚህ ዘዴዎች ውጤታማነት ከልጆቹ ጋር ባለህ የግል ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ይሆናል:: ከቡድኑ ውጪ ከነርሱ ጋር የምታጠፋው ጊዜ በቡድኑ ላይ ያላቸውን መነሳሳትና አሳይመንቶቻቸውን እንዲሰሩ በቀጥታ አፌክት እንደሚያደርጋቸው ማየቱ አስገራሚ ነው::

አሳይመንቶቻቸውን እንዲጨርሱ ልጆችህን ለማበረታታት እነዚህን ተግባራዊ ዘዴዎች መጠቀም ትችላለህ::

- በእያንዳንዱ ሳምንት ከስብሰባው በፊት ለሁለት ወይም ለ3 ቀናት ጥራቸው:: እንዴት እያደረጉ እንዳለ ጠይቃቸው ደግሞም በዚህ ሳምንት ቡድኑ ምን እንደሚሸፍን በጉጉት ንገራቸው:: ስለ አሳይመንቶቻቸው አስታውሳቸው፤ ከዚያም በስልክ ጸልይላቸው:: ይህ ከነርሱ ጋር ያህን ግንኙነት ይመሰርተዋል ደግሞም ስለምትጠብቀው ነገር አስተውሳቸው
- የተጠሪነት የጓደኝነት ዘዴን አስቀምጥ:: ስራቸው እንዲሰራ እርስበርስ የመረዳዳት ሀላፊነት አለባቸው:: ከሁሉም በላይ በጣም የተነቃቃ ልጅ በጣም ትንሽ የተነቃቃውን ልጅ ሊረዳ ይችላል::
- አንድ ተማሪ በተለየ ሁኔታ ግራ እየተጋባ ከሆነ፣ ስለርሱ በግልጽ ተናገር:: ለምን እየታገሉ እንደሆነ ግልጽ ሁን:: በአንድ ላይ በመሆን መፍትሄዎችን

ፈልጉ፡፡ ምንም ነገር ብታደርግ ከነርሱ ጋር ተስማማ፡፡ አሳይመንቶቹን አየሰሩ ስላልሆነ በነርሱ ላይ የማቆምን ሀሳብ አትስጣቸው፡፡

- እየተማሩ ያሉትን ነገር ወደ ተግባር ቀይር፡፡ ልጆች በጣም በችግር በማለፍና ከትምህርት ባለፈ የሚያስፈልጋቸውን ነገር የተማሩትን ወደተግባር የሚቀይሩበት ቦታ ነው፡፡ ከጓደኞቻቸው ከአንዱ ጋር ክርስቶስን እንዲካፈሉ ካንተ ጋር ውሰዳቸው ወይም ከቡድን ስብሰባው በኋላ በየሳምንቱ ወደ ህጻናት መኖሪያ ሂድ፡፡
  ምንም ብታደርግ ኢየሱስን መከተል አሰልቺ አይደለም የሚለውን ሃሳብ አጠናክር!

## 4. ወንዶችና ሴቶች በአንድ ቡድን ውስጥ መደረግ ይችላሉን?

አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር አይቻልም፡፡ በአመታት ብዛት የተለያዩ ጾታዎን ለየብቻ ማድረግ የተሻለ እንደሆነ ተረድተናል፡፡ ከህግ አጥባቂነት ጋር የተገናኘ ምንም ነገር የለውም ትላልቅ ወንዶች ወጣት ወንዶችን እንዳስተማሩና ትላልቅ ሴቶች ወጣት ሴቶችን እንዳስተማሩ መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ጉዳይ ላይ አቅጣጫን ይሰጠናል (ቲቶ 2፡1-8)፡፡

ሁለት ሌሎች ትክክለኛ ምክንያቶች ይህን ውሳኔ ያሳያሉ፡

- ወንዶችና ሴቶች በአንድ ላይ ሲሆኑ፣ ኢየሱስን የተሻለ ለማወቅ ከመፈለግ ይልቅ ከወንድ/ ከሴት ጓደኛ ጋር ለመሆን በመሻት ተነሳስተው ለደቀ መዝሙርነት ቡድን ይፈርማሉ
- ልጆች እንደ ሴክስ እና ማስተርቤሽን ያሉ ነገሮችን ለመወያየት እስኪፈልጉ ድረስ በደቀ መዝሙርነት ቡድኖች ላይ ጉዳዮችን ያነሳሉ፡፡ በተቀላቀለ ቡድን እነዚህን ነገሮች ለመወያየት አስቸጋሪ ነው፡፡ የተለያዩ ቡድኖች ግን ለጠለቀና ለተጨማሪ እውነተኛ ውይይት ይረዳሉ፡፡

5. የእኔ ልጆች መሰረታዊ ነገሮች አሏቸው ስለዚህ ወደ ብስለት መሄድ ሲሪስ ውስጥ አንዳንዶቹን መጽሐፍ ልዘላቸው እችላለሁን? መጽሐፎቹን በቅደም ተከተል መከተል አለብኝን?

ብዙ ጊዜ የወጣት መሪዎች ልጆቻቸው ከሚያውቁት በላይ እንደሚያውቁ ወይም ከሆኑት በላይ የበሰሉ እንደሆኑ ያስባሉ። ምንም እንኳን ልጆችህ ከመሰረታዊ ነገር በላይ ቢሆኑም የግድ በተግባር ላይ አውለውታል ማለት አይደለም። በተጨማሪም ከመጽሐፉ የትኛውንም ነገር መዝለል ጥሩ አይደለም ምክንያቱም ከመንገዱ በታች ትላልቆቹ ደቀ መዛሙርትህ አነስተኞቹን ልጆችህን ደቀ መዝሙር እንዲያደርጉ ቻሌንጅ ታደርጋለህ። በማቴርያሎቹ ውስጥ ካላለፉ፣ ቡድኑን እንዴት እንደሚመሩ አያውቁም።

መጽሐፉን በመደዳ መከተሉ ጥሩ ነው ኢየሱስን በመከተል ውስጥ ልጆቹን በደህንነት በሂደት ውስጥ በመውሰድ አለምህን ተጽኖ ለማድረግ ሌሎችን የማገልገል ጥበብን በማግኘት ፕሮግረሲቭሊ ስለተጻፉ። ይሁን እንጂ እንደዛ ለማድረግ የተለየ ምክንያት ካለህ ልታዟዙራቸው ትችላለህ። ለምሳሌ እየቀረበ ያለ የሚሽን ጉዞ አለህና ልጆችህን እምነታቸውን እንዲያካፍሉ ማስተማር ከፈለግህ እምነትህን ማካፈልን መጠቀም ትችላለህ - ምንም እንኳን በዚህ ሲሪስ ውስጥ ቀጣዩ መጽሐፍ ባይሆንም።

## ባህሉን ዘልቆ መግባት

1. ትምህርት ቤቶቹ ለውጭ ሰዎች ከተዘጉ ምን አደርጋለሁ?

- በመላው አሜሪካ ውስጥ ወደ ትምህርት ቤት ካምፓሶች መግባት አስከማይቻል ድረስ ዘ ወርድ ኢዝ አውት። እውነታው ትክክለኛ ዘዴ ካለህ የትኛውም ትምህርት ቤት ከካምፓሱ ውጪ አያደርግህም። ብዙውን ጊዜ የወጣት መሪዎች ይህንን ወደ ካምፓስ ላለመሄድ እንደምክንያት ያቀርቡታል። የወጣቶች አገልግሎት

ራዕይ ትክክለኛ ግንዛቤ ከተገኘ፣ በማህበረሰብህ ውስጥ ባሉ ካምፓሶች ሁሉ አገልግሎትን የመጀመር መሻትን ይገልጻል።

በተዘጉ ካምፓሶች ውስጥ ግንቦችን ለማፍረስ፡-

- ጸልይ ደግሞም ጨምርና ጥቂት ጸልይ። ከየትኛውም ድርጊት በላይ ይህ በጣም አስፈላጊ ነው። በአመታት ብዛት፣ ተዘግተው የነበሩ ብዙ ካምፓሶች በጸሎት ተከፍተዋል። ጥብቅ ጸሎት ልዩነትን ያመጣል። በካምፓሶቻቸው ከተማሪዎችህ ጋር የ3 ዮሽ የጸሎት ስልትን ተጠቀም።
- ፕሪንሲፓሉን አግኘው ደግሞም ይህንን ወሳኝ ግንኙነት አሳድግ
- ችግርን አገልግል/ፍታ። ትምህርተ ቤቱ ርዳታ የሚሻበትን ቦታ ፈልግና ፍላጎቱን ለማርካት ሪሶርሶችህን አንቀሳቅስ
- ከሌሎች ቤት ክርስቲያኖችና የካምፓስ ተቋማት ጋር ተደራጅ። ብዙ ጊዜ ሌላ የወጣት አገልግሎት ወይም ድርጅት በካምፓሱ ላይ ኦልሬዲ እየሰራ አለ። ካልሆነ ግን ጅማሬውን አስብ። በራስህ ለመግባት ችግር ሲያጋጥምህ ያ ወደ ካምፓሱ ለመግባት እድልን ይሰጥሃል።

## 2. የአመራር ቡድኑን በካምፓሱ ላይ እንዴት አሳትፈዋለሁ?

በአመራር ቡደንህ ውስጥ ወደ ካምፓስ በመሄድ ደስ የሚሰኙ ሌሎች ደግሞ በፍርሀት የሚንቀጠቀቱ ጥቂት ሰዎች ይኖሩሃል። በየትኛውም መንገድ ከቤተ ክርስቲያን ውጪ በሆነ መንገድ ከልጆች ጋር ለመገናኘት ሁሉም ይፈልጋሉ - ምንም እንኳን በሳምንት የሚሰጡት አንድ ሰአት ብቻ ቢኖራቸውም።

ለዚህ በጣም ጉጉት ያላቸውን ውሰድና ከአንተ ጋር ወደ ካምፓሱ አገልግሎት አስገባቸው እነርሱን ለማሰልጠን። አንዴ ከሰለጠኑ፣ በሌላ ካምፓስ አገልግሎት ለመጀመር እንዲቋቋሙ እርዳቸው። ለካምፓስ አገልግሎት አንዱ የላቀ ሀብት የኮሌጅ ተማሪዎች ናቸው። ለከፍተኛ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ነጻ ጊዜአቸውንና የእድሜ

እኩያዎቻቸውን ጥቅም ላይ በማዋል። ወደ ካምፓስ ቡድንነቶች አደራጃቸው- በማህበረሰብህ በሚገኙ በሁሉም ካምፓሶች ካሉ ልጆች ጋር ግነኙነቶችን ለመመስረት።

ካምፓሱን ዘልቆ መግባት ውስጥ አጠቃለይ ምዕራፉ ለዚህ ጥያቄ ተሰጥቷል።

## 3. በካምፓሱ ላይ ምን መብቶች አሉኝ?

ምንም። ንየት። ናዳ። ተማሪዎች በርካታ መብቶች አሏቸው አስተማሪዎች ደግሞ የተወኑ መብቶች። የአንድ ተማሪ ወላጅ ከሆንክ፣ ልክ እንደሌሎቹ ወላጆች አይነት ተመሳሳይ መብት አለህ። እንደ አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የወጣት መሪ ግን ምንም መብት የለህም። በዚህ ምክንያት የ "መብት መንገድን" ከመውሰድ ይልቅ "የአገልግሎት መንገድን" ለመውሰድ በመወሰን በካምፓሱ ላይ ያለህን ዘዴ አስቀድሞ መወሰን በጣም አስፈላጊ ነው። ወደ ትምህርት ቤቱ ሄዶ ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ለክለብ፣ ወይም በመማሪያ ክፍሎች እና ማህበሮች ለመናገር እድልን ጊዜን ከመጠየቅ ይልቅ ከፕሪንሲፓሉ ጋርና ካንዳንድ ኮቾች/ ፋካልቲዎች ጋር ግንኙነትን መሥርት። ከዚያም የትምህርት ቤቱን ችግሮች እንዴት ማገልገል እንደምትችል ወስን። ይህ ለሚመጡት አመታት ተማሪዎቹን ለማገልገል የሚረዳህን ከትምህርት ቤቱ ጋር የረጅም ጊዜ፣ አዎንታዊ ግንኙነትን ይሰጥሀል።

## 4. ከአካባዬ ከአንድ በላይ ካምፓስ ቢኖረኝስ?

የበለጠ ሲሆን የተሻለ ነው! በአካባቢህ ብዙ ካምፓሶች ካሉ፣ ብዙ ተማሪዎችን ለመድረስ አገልግሎትህ የበለጠ ጥቅም አለው ። ብዙ ካምፓሶችን እንደ አዎንታዊ እንጂ እንደ አሉታዊ አትመልከት። አዎንታዊ ዘዴን በመጠቀም እነርሱን ለመድረስ ምን ታደርጋለህ?

- መሪ እንደመሆንህ በአንድ ካምፓስ ላይ አንድ ውጤታማ አገልግሎትን አቋቁም
- በካምፓስ ላይ ከተማሪዎች ጋር እንዴት መገናኘት እና ለክርስቶስ እነርሱን መድረስ በሚቻልበት መንገድ ላይ የአመራር ቡድንህን ለማሰልጠን ያንን ካምፓስ እንደ

ማሰልጠኛ ግራውንድ ተጠቀም፡፡

- ካምፓሱን እንደአገልግሎታቸው የሚያዩትን በአመራር ቡድንህ ላይ የኮሌጅ ተማሪዎችን በመጠቀም የካምፓስ ቡድኖችን አቋቁም፡፡ ውጤታማ አድርጎ ለመሥራት አመራር ሲኖርህ ብቻ በሌላ ካምፓስ ላይ አገልግሎትን ጀምር
- ጓደኞቻቸውን ለክርስቶስ ኢንፍሉዌንስ ለማድረግ እያንዳንዱ የካምፓስ ቡድን ክርስቲያን ተማሪዎህን ያንቀሳቅስ፡፡ ካምፓስህን ለክርስቶስ መማረክ የሚለው መጽሐፍ ይህንን ለማድረግ የሚረዳውን ሀብት/ሪሶርስ ይሰጥሃል፡፡
- እያንዳንዱን ካምፓስ በራስህ ወይም በቤተ ክርስቲያንህ አማካኝነት መድረስ እንዳለብህ አታስብ፡፡ ከሌሎች የካምፓስ ክርስቲያን ድርጅቶች እና ከሌሎች ቤተ ክርስቲያኖች ጋር ተያያዝ ደግሞም ተባበር፣ አዎ ከሌሎች ቤተ እምቶችም ጋር ቢሆን በማህበረሰብህ ውስጥ በሚገኙ ካምፓስ ያሉ ልጆች በሙሉ ኢየሱስ ክርስቶስን የማወቅና የመከተል እድል ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ፡፡
-

## 5. ቤተ ክርስቲያኔ ወደ ካምፓስ እንድሄድ ባትፈቅድልኝስ?

ይህንን ጥያቄ መመለስ አሳሳች ነው ምክንያቱም ፓስተርህ ወይም መሪዎችህ የካምፓስ አገልግሎትን እንዳያበረታቱ ሊያደርጉ የሚችሉ በርካታ ነገሮች ስለሚኖሩ ወይም በአንተና በአመራሩ መካከል ማንም ሰው የሀይል ዘመቻ ላይ እንዳልሆነ ምንም ግጭት እንደሌለ በመገመት፣ እንዳትሄድ የፈለጉበትን ምክንያት ማወቅ አለብህ ምናልባት ስለሁኔታው አንተ የማታውቀውን ነገር ያውቁ ይሆናል፡፡ ወይም ጊዜው ገና ስላልደረሰ እግዚአብሄር እነርሱን እየተጠቀመባቸው ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ ባለስልጣኖችህ ልጆችን ለክርስቶስ በመድረስ ፍልስፍናና ራዕይ መካከል ልዩነት ካገኘህ ወይም እንደዛ አይነት ልጆች በቤተ ክርስቲያናቸው በመኖራቸው ደስ ካልተሰኙ ከባድ የሆነ ችግር አለህ፡፡ ችግሩን ለማቃለል፡

- ከእግዚአብሔር ዘንድ ለጥበብና ለምሪት ጸልይ
- የቤተ ክርስቲያን አመራርህ ራእይህን እንዲረዱ ጠይቅ፤ እንደገና እንዲያገናዝቡ ጠይቃቸው
- ሁለቱ ካልተስማሙ በአንድ ላይ መሄድ እንደማይችሉ

አስብ (አሞጽ 3፡3)።
ይህንን እንድታደርግ ካልፈለጉ ለረጅም ጊዜ መቀጠል ብቻ ትችላለህ። በዚያን ጊዜ ወደ ሌላ አገልግሎት መሄድን ማገናዘብ ያስፈልግሃል። በመንገዱ ላይ በልብህ ያለውን በተስፋ ልታነጋግራቸው ትችላለህ፤ ደግሞም ለኢየሱስ ክርስቶስ በትምህርት ቤቶች በሙሉ ያሉ ተማሪዎችን እንድትከታተል ጌታም ነጻነትን ይሰጥሃል።

## የመድረስ አጋጣሚዎችን ፍጠር

### 1. የመድረስ አጋጣሚዎችን ለመፍጠር ችሎታ፣ ገንዘብ ወይም ሰዎች ባይሩንስ?

ልክ ኢየሱስ አምስቱን እንጀራና ሁለቱን አሳ እንዳበዛ ያለህን ነገር በእምነት ለእግዚአብሄር ከሰጠህ ያበዛዋል ደግሞም ልታስበው ከምትችለው በላይ የሆነ ነገርን ፕሮዲዩስ ያደርጋል። ያለህን ሀብት እግዚአብሄር እንዲያበዛ የሚከተሉትን የስራ እርምጃዎች ተከተል

- ለተፈለጉት ሀብቶች አብዝተህና በርትተህ ጸልይ
- ራስህንና ቡድንህን ለመድረስ አጋጣሚ አዘጋጅ። ለአስተያየት የሚቀጥለውን ጥያቄ ተመልከት።
- ከአንተ ጋር እንዲሰሩ በአመራር ቡድንህ ውስጥ ሰዎችን ሃላፊነት ስጥ። አንዳንዶች በመድረስ አጋጣሚዎችህ ላይ በተለየ ሁኔታ ማተኮር ሊፈልጉ ይችላሉ
- መድረስን ለማካሄድ ከሌሎች ጋር ተያያዝ። በቤተክርስቲያንህ ወይም በማህረሰብህና እንዲሁም በሌሎች ቤተ ክርስቲያኖች ብዙ ሀብቶች ይኖራሉ። ( ክፍል ጊዜ 7ን ከልስ፣ "የመድረስ አጋጣሚዎችን ፍጠር")
- ዋጋ የመድረስ ውጤታማነትህን መወሰን የለበትም። እያንዳንዱ የደቀ መዝሙርነት ቡድን ሙሉውን ወይም ግመሽ መድረስ/ አውትሪችን ሲይዝ፣ ልጆች ጓደኞቻቸውን ያመጣሉ ደግሞም ኢየሱስ በዝቅተኛ ዋጋ መቅረብ ይችላል።

## 2. ጥራት ያለው፣ የፈጠራ የመድረስ አጋጣሚን እንዳሰራጭ ለመዘጋጀት ምን ይጠይቀኛል?

ይህን ጥያቄ መመለስ የማግኜቱ ውጤትን የመጀመሪያ 76 ገጾች የወሰደ እንዲህ ያለ ጠቀሜታ አለው! ይህ መጽሐፍ ለአገልግሎትህ የተልእኮ መግለጫህን እንዴት ማሳደግ እንዳብህ ያሳይሀል፤ ለወጣት አገልግሎትህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስልትን እንዴት እንደምትጥል፣ ለወንጌል የልጆችን ምላሽ አለመስጠት በጸሎት እንዴት እንደምትሰብር፣ የቤተ ክርስቲያንህን አመራር እንዴት እንደምታገኝ የአመራር ቡድንህን እና ከጀርባህ ያሉትን ዋና ዋና ልጆችን ያሳይሀል። ምንም እንኳን ይህ ሂደት ከፈለከው በላይ ጊዜ ሊወስድ ቢችልም ልጆችን በመድረስ ረገድ የመድረስ መንገድህን ውጤታማ ለማድረግ ቆይታው ይገባዋል። ። ለረጅም ጊዜ ፍሬ እንጂ ለአጭር ጊዜ ፍሬ እየሄድክ እንዳልሆነ አስታውስ።

## 3. ክርስቲያን ያልሆኑ ልጆች እንዲመጡ የማደርገው እንዴት ነው?

ክርስቲያን ያልሆኑ ተማሪዎችን በመድረስ ላይ ያተኮረች ቤተ ክርስቲያን በዚህ ትውልድ ውስጥ ከዘመኑ በላይ ትሆናለች። ይህን የማታደርግ ቤተ ክርስቲያን በአፈር ውስጥ ትጣላለች። የማያምኑ ልጆችን ወደ ወንጌል ለመሳብ ከእነርሱ ጋር ግንኙነት ማድረግ አስፈላጊ ነው። ስለዚህ ካምፓሱን ዘልቆ መግባት ለስርጭቱ መሳካት አስፈላጊ ነው።

ልጆች በፕሮግራሙ ግሊትዝ/ ሳቢነት አይመጡም ጓደኞች ስለሚያመጧቸው ይመጣሉ እንጂ በአጋጣሚ አይመጡም። ጓደኞቻቸውን ለማምጣት መሪዎችህንና ተማሪዎች የሚቃጠል መሻት ሊኖራቸው ይገባል። ያ ሲሆን የማያምኑ ሰዎች መምጣት ይኖርሃል።

ከአንዴ በላይ የማያምኑ ሰዎች እንዲመጡ ከጠበቅህ፣ ከ “ክሪስታናይዝድ” ነጻ የሆነና ለአለማዊ ልጆች ምቹ ሁኔታን መፍጠር አለብህ። ያ ማለት በልቀት ፕሮራሞችን ማድረግ ማለት

ነው። የማግኔቱ ውጤት ይህንን እንዴት ማድረግ ባለብህ መንገድ ውስጥ ይመራሃል።

## 4. በየሳምንቱ ወንጌሉን የሚያቀርብ አውትሪች ማድረግ ይገባኛልን?

ቀስ ብለህ ጀምር። ለመጀመር በሩብ አመት አንዴ ልዩ የተማሪህ ዋና ሲያድግ፣ በወር አንዴ ከዚያም በሳምንት አንዴ ማድረግ ትችላለህ። አንተንና መሪዎችህን ስለሚረዳ ወጥነት ቁልፍ ነው ልጆችህም ደግሞ በወጥነት አውትሪች እንደሚካሄድ ያውቃሉ። በየጊዜው ወንጌልን ማቅረብን በተመለከተ መልሱ አዎ ነው። መልእክቱን ግን ከፈጠራ ጋር አቅርብ። መድረስህን ከልጆች ፍላጎት ጋር ለማመሳሰል ዲዛይን አድርግ ከዚያም የወንጌልን መልእክት ለእነዚያ ፍላጎቶች አዛምድ። ይህንን ውጤት ባለው መንገድና በፈጠራ ለማድረግ፣ ፕሮግራምን በማቀድ ወደ ማግኔቱ ውጤት ምዕራፎች ሂድ።

## 5. አውትሪቹን በቤተ ክርስቲያናችን ወይስ ገልልተኛ በሆነ ስፍራ ማድረግ ነው የሚሻለው?

ትክክለኛው ነገር ልጆችን ክክርስቶስ የሚከለክሉ እንቅፋቶችን ለመጠራረግ ማድረግ የምትችለውን ሁሉ ማድረግ ነው። ያንን በሃሳብህ አድርገህ ወደ ራስህ ፋሲሊቲና በማህረሰብህ ወዳሉ ሌሎች ፋሲሊቲዎች ተመልከት፤ ከዚያም ለማያምኑ ሰዎች ለመምጣት ቀላል የሚሆነውን ምረጥ። ዋጋ ተምን፣ ጥረቶችን መስርትና ፈጽም፣ በማህበረሱ ውስጥ ያለው ርቀትና የፋሲሊቲው መረዳትህ ውሳኔህ ላይ ተጽኖ ያደርጋሉ። ይህንን ለመወሰን አንዱ የተሻለው መንገድ ለእነርሱ ይበልጥ የሚስማማውን ለማግኘት ልጆችህን እና ካምፓስ ላይ ያሉ ልጆችን ሰርቬይ ማድረግ ነው።